







# የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ

## አንደኛ መጽሐፍ

(፲፱፻ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም)

ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ

የመተርጎም፣ መልሶ የማሳተምም ኾነ የማባዛት መብቱ የጸሐፊው ነው።


ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ

የመልዕክት ሣጥን ቁጥር 22 27

አዲስ አበባ (ኢትዮጵያ)

E-mail = tamrin@telecom.net.et



የመጀመሪያ ዕትም ፲፱፻፺፯ ዓ.ም




ይህ መጽሐፍ ለአብሮ አደጌ፣ የትምሕርት ቤት
ጓደኛዬና፣ የልብ ወዳጄ ለነበረው
ለአቶ ሸዋቀና ዜና ይርዳው መታሰቢያ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

ምንም እንኳን ይህንን መጽሐፍ ሳሰናዳ ያበረታቱኝ በርካታ ቢሆኑም በይበልጥ ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው ለረዱኝ ለሚከተሉት ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ሀ) መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ ታላቅ ዕርዳታ ያደረጉልኝ:-

1ኛ አቶ በቀለ ተሰማ
2ኛ ሌ/ ኮሎኔል ቢፍቱ ጨፎ
3ኛ ኮሎኔል ተስፋዬ ፍርዴ
4ኛ አቶ ቴዎድሮስ ሰሎሞን
5ኛ ኮሎኔል መሠረት ገላው

ለ) አንዳንድ ሃሳቦች ላይ አስተያየታቸውን የለገሱኝ:-

1ኛቀኛ. አምኃ ሊበን ስብሐት
2ኛየተከበሩ አቶ ተስፋዬ መስቀሌ
3ኛ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም
4ኛ ክቡር አቶ ጌታቸው ብቁለ
5ኛ ዶክተር ሹመት ሲሻኝ
6ኛ ክቡር ዶ/ር ብርሃኑ አበበ
7ኛ አቶ ኃይለ ኪሮስ አበራ
8ኛ አቶ አረጋዊ ገብረ የሱስ

ገ) በኮምፒዩተር ሥራ የረዱኝ:-

1ኛ አቶ ዮሴፍ አባተ
2ኛ አቶ ዳንኤል አብርሃም

ደ) በቋንቋ አገባብና በፊደል እርማት ያገዙኝ:-

1ኛ አቶ ይልማ ሃብተየስ
2ኛ አቶ በኃይሉ አሰፋው
3ኛ አቶ ሄኖክ ዮሐንስ
4ኛ አቶ ጎሩይ በላይነህ ኢጋጅየለው

በተለይ አቶ ጎሩይ የሆሂያትን ትክክለኛ አገባብና አንዳንድ ጉዳዮችን በመጠቆም ከፍተኛ ዕርዳታ ለግሰውኛል።



# መቅድም

በጽሑፍ ተመዝግቦ ከተገኘው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ እክናሁስ ቀጥሎ በተከታታይ ከነገሡት ነገሥታት መካከል ስሟ 52ኛ የምትታወቀው ንግሥት አዜብ ወይም ማክዳ (ንግሥተ ሳባ) ነጋሢ ነች። እሷም በተራዋ መንግሥቷን ለልጅዋ ለቀዳማዊ ምኒልክ ስታስረክብ የንግሥና ሥርዓት አውጥታ በማለፏ ከጌታ ልደት በኋላ እስከ 4ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ተወላጆችዋ መቀመጫቸውን አክሱም ላይ በማድረግ አካባቢያቸውን ሲያስተዳድሩ ቆዩ። ከንግሥተ ሳባ አስቀድሞ የነበረው አምልኮት በፀሐይ፣ በጨረቃ፣ በግዙፍ ወንዞች ተራሮችና ምድራዊ ኃይል ጋር የተያያዙ ነበሩ። ከንግሥተ ሳባ በኋላ እስከ ንጉሥ ኢዛና ድረስ የአገሪቱና የነጋሢዎቹ ሃይማኖት የንግሥት ሳባን ጉብኝት ግምት ውስጥ በማስገባት የአይሁድ ሃይማኖትን ተቀብለው ነበር ተብሎ ይተረካል። አንዳንድ ታሪክ ተመራማሪዎች ግን ለአባባሉ ማስረጃ አላገኘንለትም ብለው በአስተሳሰብ ይለያሉ።እነዚህ ተመራማሪዎች አልፈው ተርፈው እስከ ክርስትና መግባት ድረስ የነበረው ዕምነት የጣኦት አምልኮ ነበር እስከ ማለትም ደርሰዋል። አማልክቶቹም ምድር፣ እግዚኦ፣ በዓልና ብሔር እንደነበሩ ማስረጃ አግኝተናል ይላሉ።

በ355 ዓ.ም የነበረው ንጉሥ ኢዛና ወይም አብርሃ የክርስትናን ሃይማኖት በይፋ ተቀብሏል። አዲስ ሃይማኖት በመጣ ቁጥር ተቃውሞ ስለሚያጋጥም ክርስትናንም ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት ለብዙ ዘመናት ደም አፋሷል። ይሁንና በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት ያገኘ ሃይማኖት ብዙውን ጊዜ የማሸነፍ ዕድል ስለሚኖረው አገሪቱ በቀን ብዛት የክርስቲያን አገር ለመባል በቃች። ከዚህም የተነሳ በ6ኛው ክፍለ ዘመን በየመን ክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰውን መጉላላት ለማስወገድ ጦር በማዝመት ችግሩን እስከ መፍታትም ደርሳለች።

በ7ኛው ክፈለ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት በዓረብ አገር ተስብኮ በተፋጠነ ሁኔታ መስፋፋት ሲጀምር የክርስቲያኒቱ ኢትዮጵያ መንግሥት በቀይ ባሕር ላይ የነበራት ግናኙነት እያደር መድከም ጀመረ። በ9ኛው ክፍለ ዘመን ዩዲት የምትባል የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ ነግሣ የክርስትናን ሃይማኖት ለማጥፋት አርባ ዓመት ሙሉ ደም ስታፈስና ንብረት ስታቃጥል ከቆየች በኋላ በክርስቲያን ንጉሥ ስትተካ፣ እሱም በተራው የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችን ለማጥፋት ብዙ ደም አፈሰሰ። በዚህ ግብግብ የአክሱም መንግሥት በመዳከሙ የአገው ባላባቶች መንግሥቱን ነጥቀው ላስታ ላይ ሆነው ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት ሥልጣኑን ወስዶ ሸዋ ላይ ተቀምጦ ማስተዳደር ጀመረ።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከምሥራቅ በኩል የተነሳው አጭሩና ደልደል ያለ ሰውነት ያለው አህመድ ኢብን ኢብራሒም ወይም ግራኝ አህመድ በእስልምና ሃይማኖት አገሪቱን ለመምራት በማሰብ፣ ተከታታይ ዘመቻ አድርጎ ብዙ ደም ከፈሰሰና የንብረት ጉዳት ከደረሰ በኋላ እንደገና ተሸነፈ። ንጉሡም መቀመጫውን ከሸዋ ወደ ጎንደር አዙሮ ሲኖር ኃይሉ የሳሳው የደገኛው ክርስቲያን ሕዝብ ከደቡብ አከታትሎ በሚስፋፋው በኦሮሞ ጎሣ መጠቃትና መተካት ጀመረ። በግራኝ ጦር ሲጠቃ ሊረዱት የመጡት ፖርቱጋሎች ከተመለሱ በኋላ ስለ አገሪቱ ወሬ ሰምተው የመጡ የወንጌል ሰባኪዎች በፈጠሩት የሃይማኖት መከፋፈል የእርስ በእርስ ጦርነት ተነስቶ መንግሥቱ እየደከመ ሄዶ በአራቱ ማዕዘናት ያሉ ግዛቶቹን መቆጣጠር አቃተው። በ18ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ንጉሡን እንደራሴው በሥልጣን ስለበሰጠው፣ ዘመነ መሳፍንት ተጀመረ።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ቴዎድሮስ የአካባቢ ግዛቶችን በመጠቅለል አገሪቱን በአንድ መንግሥት ሥር ለማስተዳደር ቢሞክሩም በነበረው ተደጋጋሚ ጦርነት ብዙ ሰው ስለተጎዳ፣ እየተጠሉ በመሄዳቸውና የፖለቲካ ስህተቶችም በመሥራታቸው፣ የእንግሊዝ ጦር በአካባቢ ባላባቶች ፈቃድ ገብቶ ተሸንፈው ሥልጣኑ ለሦስት ዓመት ወደ ላስታ፣ ቀጥሎም ለ18 ዓመት ወደ ትግራይ ከተዛወረ በኋላ ተመልሶ በዳግማዊ ምኒልክ አማካይነት ወደ ሸዋ በይኩኖ አምላክ ተወላጆች እጅ ገባ። ዘመኑ አውሮፓውያኖች ቅኝ ግዛት ለመያዝ የሚሯሯጡበት ወቅት በመሆኑ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ የተቻላቸውን



ያህል ወሰን ለማስከበርና የቅኝ ገዥዎችን ወረራ ለመግታት ሲከላከሉ ዘመናቸውን አሳልፈዋል። የ19ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ አመራር የአገሪቱን ጥቅም የሚያስቀድም ሆኖ መሪዎቹም ቀናና ጀግኖች እንዲሁም ሕዝቡ በጀግንነት የታነጸ ስለነበረ የቅኝ ግዛትን ኃይል ተቋቁመውና ድል አድርገው የአሁኒቱን ኢትዮጵያ ስለአወረሱን ባለውለታዎቻችንና የምንኮራባቸው ናቸው። አፄ ዮሐንስ በጦርነት ሲሞቱ፣ አፄ ምኒልክ ደግሞ በጦርነት ዕድል ስለቀናቸው በቀራቸው አጭር ጊዜ ውስጥ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማምጣት ሲታገሉ በጤና ማጣት ሳቢያ ሞቱ። ከእሳቸው በኋላ ሕዝብ ያመነበት ተተኪ ስላልነበራቸው የሥልጣን ሽኩቻ ተደረገ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ መንግሥቱን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጨብጠው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ይበልጡን ጊዜ ኢትዮጵያን አስተዳድረው፣ የታመነበት ተተኪ በሌለበት ሁኔታ ለዴሞክራሲም ዕድል ለመስጠት ባለመፈለጋቸውና እርጅናም ስለተጫናቸው ሥልጣናቸው በወታደሮች ተነጠቀ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የምዕራባውያን ሥልጣኔ ገፍቶ የመጣበት ወቅት ስለነበረ ኢትዮጵያ በሃይማኖት ጭቅጭቅ ምክንያት ዘግታው የነበረውን በሯን የምዕራባውያንን ሥልጣኔ ፍሊጋ ለመክፈት የተገደደችበት ዘመን ነበር። አፄ ምኒልክ የከፈቱትን የሥልጣኔ በር መልሶ ለመዝጋት ባይቻልም በተከፈተው በር የሚፈለገው ሥልጣኔ በአመርቂ ሁኔታ ገባ ወይስ አልገባም? ትልቁ ጥያቄ እንግዲህ ይህን ይመስላል። ለዚህ መልሱ ደግሞ እንደየግለሰቡ ይለያያል። አንዱ ወገን አመርቂ ነው ብሎ ሲያመሰግን ሌላው ወገን በተቃራኒው ሲነቅፍ ይታያል። ስለሆነም በወቅቱ የነበረው የአገሪቱ ሁኔታና የመሪው ታሪክ ጉራማይሌ ነበር ማለት ይቻላል። ለመሆኑ ከአፄ ምኒልክ በኋላ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ድረስ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ታሪክ ምን ይመስላል?

የ20ኛው ክፍለ ዘመንን የኢትዮጵያ ታሪክ ከሌሎች ክፍለ ዘመናት ለዩት የሚያደርገው የመጣው ለውጥ አጣዳፊና ኃይለኛ ከመሆኑም ለየት የሚያደርገው የመጣው ለውጥ አጣዳፊና ኃይለኛ ከመሆኑም በላይ ብዙ ሥር ነቀል ጉዳዮችም የታከሉበት ስለነበረ ነው። ከዚህም ሌላ ለብዙ ዓመት ሲካሄድ የነበረው ደም መፋሰስና የተንሰራፋት የተለያዩ ሃይማኖቶች ያስከተሉት ሥነ ልቡናዊ አስተሳሰብ ከለውጡ ጋር የሚፈጥሩት ቁርኝትና ግጭት ቀላል አልኾነም። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ላይ የነበረ መሪ ከግሉ ሥነ ልቦናዊ ቅርጽ ጋር አዋሕዶ

የመጣውን የተፋጠነ ለውጥ በኢትዮጵያ ሁኔታ እንዴት እንዳስተናገደውና መሰናክሎቹንም እንዴት እንዳለፉቸው መመርመር ለምሥጋናም ኾነ ለወቀሳ ያበቃል።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያውን ረዥም ወቅት የመሩት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደ መሆናቸው መጠን በመጽሐፉ ውስጥ የእሳቸው ታሪክ ገዝፎ ይገኛል።

❄❄❄





# መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ የኢትዮጵያ አዲሱ ትውልድ ማንነቱን በቅድሚያ እንዲያውቅ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። የራሱን ታሪክ በቅድሚያ ባለማወቁ ለጥራዝ ነጠቆች መጫሪያነት እንደዋለ አይተናል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ቀደም ባለው ዘመን አባት ልጁን ሲያስተምርበት የነበረው ልማድ ልጆችን ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት መላክ ሲጀመር በመቋረጡ ነው። አባት ልጁ ተምሯል፣ ያውቃል ሲል ልጅ ደግሞ አለማወቁን እንኳን ሳያውቅ ቀረና ክፍተት ተፈጠረ። የራሱን ማንነት የሚነግረው በማጣቱ በቅን ልቡና ለአገሩ የከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ ኾኖ ቀረ። በዚህ ሥርዓት የተማሩ ሰዎች የአገራቸውን ታሪክና ሁኔታ ጠንቅቀው ለማወቅ ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም። ምክንያቱም የትምሕርት አሰጣጡ የአገርን ታሪክና ሁኔታ ጠለቅ አድርጎ የሚያስገነዝብ ባለመሆኑና በሌሎችም ተጨማሪ ምክንያቶች ነው።

ይህ መጽሐፍ አዲሱ ትውልድ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን የአገሩን ሁኔታ መርምሮና አውቆ የሌላውንም ዓለም አካሄድ አገናዝቦ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ራዕይ ድርሻውን ለመወጣት እንዲዘጋጅ የሚረዳ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በታሪክ መጽሐፎች የተደገፉ ዕውነታዎች ሲዘረዘሩ በተለያዩ ምክንያቶች አቅልሎ በማየት የተዘለሉ አፈ-ታሪኮችም እንዲካተቱ ተደርገዋል። አፈ-ታሪኮቹን በመመርመር ተአማኒነት የሌላቸውን በማለፍ፣ አንዳንዶቹ ላይም ትችት በማቅረብ፣ እንዲሁም ሌሎቹን ለአንባቢ የኀሊና ፍርድ በመተው ከየታሪኩ ጋር ተዛምደው ታክለዋል።

በኢትዮጵያ ለረጅም ዘመን በኖረው የአጻጻፍ ልምድና በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በነበረው ሳንሱር ጸሐፊዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚዘግቡት ምሥጋና ብቻ ነበር። ታሪኩን ትክክለኛ ቅርጽ ለመስጥት የግድ አንዳንድ ጉዳዮችን ከአፈ-ታሪክ መውሰድ ያስፈለገበትም ለዚሁ ነው። በአገራችን ዝምታ እንደ ጨዋነት ስለሚቆጠር ወይም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ብዙ የሚያውቁ ሰዎች ሳይናገሩዋቸው በማለፋቸው በርካታ ሃቆች እንደተደበቁ መቅረታቸው የሚያስቆጭ ነው። ሆኖም በሕይወት ካሉት አንዳንድ ሰዎች የተቻለኝን ያህል መረጃዎች ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ።

በግልጽነትና በድፍረት አንዳንድ ጉዳዮችን ሳብራራ ትኩረቴ ታሪኩ ላይ እንጅ የባለታሪኩን መልካም ዝና ለማድመቅ ወይም መጥፎ ጎኑን ለማጉላት አይደለም። ስለ ባለታሪኩ መልካም ወይም መጥፎ ሥራ ተመስጋኝ ወይም ተወቃሽ ራሱ ባለታሪኩ ብቻ ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምንም በዘመናቸው በርካታ ሥራዎችን የሠሩ፣ ተወዳጅና የተከበሩ ቢሆኑም ፍጡር እንደመሆናቸው መጠን የሚደነቁባቸውን ተግባራቸውንና በአንጻሩም የፈጸሙዋቸውን ስህተቶችና ነውርም ካለ ታሪክ ነውና መጥቀሱ ደግሞ ተገቢ ነው። ሆኖም ሌሎች መጽሐፎች ላይ የተደጋገሙ ታሪኮችንና ዙፋናዊ ንግግሮችን እንዳይሰለቹ በማለት ሳልጠቅስ አልፌያቸዋለሁ።

የታሪኩን ቅደም ተከተል ከዘመን ጋር ለማጣጣም ጥረት የተደረገው በተቻለ መጠን አንባቢን ከጊዜው ጋር እንዲጓዝ ለማድረግ ታስቦ ነው። እንዲሁም በየምዕራፎቹ ላይ አንዳንድ ጉዳዮች ተደጋግመው ሲገለጹ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባልቃ የገቡ ማብራሪያዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ቀርበዋል። ይህም የኾነበት ምክንያት እያንዳንዱ ምዕራፍ የተሟላ ታሪክ እንዲያቅፍ ስለተፈለገ ነው።

የልዩ ልዩ ሰዎች ማዕረግ የዘመኑን እንጂ በኋላ የደረሱበትን አያገናዝብም። ሁሉንም ሰው አንቱ ብሎ መጻፍ ቢቻልም የጥንት ሰዎችን፣ ወጣት ልሁላንን አንተ እያልኩ መጻፌ እንደ ድፍረት አይቆጠርብኝ። በተለይ አቤቶ ኢያሱ ለደረሰበት ማዕረግ አንቱታ ቢገባውም የሕዝቡን ቋንቋ ለመናገር ብቻ በሚታወቅበት አጠራር እሱ እያልኩ ገልጫለሁ።



ለባሉ ደግሞ ቀ.ኃ.ሥ፣ ጃንሆይ ወይም ንጉሠ ነገሥቱ ተብሎ የተጠቀሰው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚለውን ላለመደጋገም በማሰብ ነው። እንዲሁም ለአንድ አገር ዜጎች መጠሪያ የተጠቀምኩት ቃል "ሕዝብ" የሚለውን ሲሆን "ጎሣ" የሚለውን ቃል ደግሞ ለልዩ ልዩ ማኅበረ ሰቦች ነው። በአንድ ጎሣ ውስጥ ኾነው በየባላባቶቻቸው ተቧድነው ለሚንቀሳቀሱት ግን "ጎጥ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ።

አንድ ሰው ማንነቱ የሚታወቀው በአዕምሮው ትዕዛዝ የሠራ አካላቱ በሚያከናውነው ድርጊት ነው። የሥነ ልቡናው ሁኔታ የሚቀረጸው በውልደቱ፣ በአስተዳደጉ፣ በትምሕርቱ፣ በሃይማኖቱና በኑሮው በሚገጥመው ሁኔታ ስለኾነ ስለ አንድ ሰው ታሪክ በምጽፍበት ጊዜ እግረ መንገዴን ከታሪኩ ጋር እነዚህንም ሁኔታዎች አነሳሳቸለሁ።



አለቃ ገብረ ሃና

የአንዳንድ ሰዎችን ታሪክ በምመረምርበት ጊዜ የታላላቅ ሰዎችን ውልደት ከነጋሢያን ጋር፣ በሃይማኖትም በኩል ከእሥራኤል ወይም ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር ለማያያዝ የሚደረጉት ሙከራዎች ሁኔታዎችን እየቀየሩ ታሪክን ማፋለሳቸው ሥር የሰደደ ችግር ቢሆንም እኔ ግን በተቻለ መጠን የተነገረውን ሁሉ እያበጠርኩ ለመግለጽ ሞክሬያለሁ።

በየወቅቱ እየተነሱ የወደፊቱን እንተነብያለን የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የኖረ ሃቅ ቢሆንም ለማገናዘብ ያህል አንዳንድ ትንቢቶችን ከየታሪኩ ጋር በማዛመድ ለአንባቢ አቅርቤያለሁ። በተለይ ከ1811 እስከ 1908 ዓ.ም የኖሩት ሼህ ሁሴን ጅብሪል ስለ ተፈሪ፣ ኢያሱና ሌሎችም ምን ብለው እንደነበረ ከየታሪኩ ጋር በንጽጽር እናያለን። ሰው አንዳንድ ቀልዶችን በአለቃ ገብረ ሃና እንደሚያላክክ ሁሉ አንዳንድ ትንቢቶችን ደግሞ ምናልባት በሼህ ሁሴን ጂብሪል አላክኮ ይሆናል። ይሁንና እኔ ትንቢቶቹም ኾኑ ቀልዶቹ

የደረሱኝ በእነሱ ስም እንደመሆኑ መጠን የሌላ ሰው ስም ለመጥቀስ አልቻልኩም። በቅርብ ጊዜ እንኳን ብላታ ሲራክ ኅሩይና ልጅ ይልማ ዲፉሩ የተናገሯቸው ናቸው እየተባለ በሕዝብ ዘንድ ብዙ ቀልድ ይነገራል።

በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ ሕዝብ እየደጋገመ የሚናገራቸው ትንቢቶች እንዳሉ ይታወቃል። ትንቢቱን መጀመሪያ ማን እንደተናገረው መጥቀስ ቢያዳግትም ሕዝብ ደጋግሞ መናገሩን ብቻ መሠረት በማድረግ ትንቢት ነበረ በማለት በብዙ ቦታ ላይ ገልጫለሁ። እንዲሁም ሕዝብ የገጠማቸው ግጥሞችና ቅኔዎች የዘመኑን ታሪክና አስተሳሰብ ስለሚያንጸባርቁ አብረው ከየታሪኩ ጋር ተጠቅሰዋል። የተፈጥሮ ቋንቋንም ትርጉም እንመረምራለን።

አንድ ምስል ከአንድ ሺህ ቃላት ይበልጥ መግለጥ ይችላል እንደተባለው በተቻለ ከየታሪኩ ጋር የተሟላ ምስል ለማቅረብ ሞክሬአለሁ።

ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ



# ማውጫ


| ምዕራፍ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፩ | የንግሥና ሥርዓትና የነገሥታት ዘር ሐረግ | 1 |
| ምዕራፍ ፪ | የተለያዩ ግዛቶች | 19 |
| ምዕራፍ ፫ | የአፄ ምኒልክ ፍጻሜ | 59 |
| ምዕራፍ ፬ | መናኙ ራስ መኮንን | 66 |
| ምዕራፍ ፭ | መካኗ እቴጌ ጣይቱ ብጡል | 75 |
| ምዕራፍ ፮ | ደጃች ታየ ጉልላቴ | 80 |
| ምዕራፍ ፯ | ጎረምሳው አቤቶ ኢያሱ | 84 |
| ምዕራፍ ፰ | ምስኪንዋ ንግሥት ነገሥት ዘውዲቱ | 114 |
| ምዕራፍ ፱ | የተፈሪ ውልደትና ዕድገት | 121 |
| ምዕራፍ ፲ | ድብቋ ወይዘሮ የሺ እመቤት | 128 |
| ምዕራፍ ፲፩ | ተፈሪ በደጃዝማችነት ዘመን | 134 |
| ምዕራፍ ፲፪ | ድንገተኛው የተፈሪ ጋብቻ | 138 |
| ምዕራፍ ፲፫ | ራስ ተፈሪ በአልጋወራሽነት ዘመን | 142 |
| ምዕራፍ ፲፬ | የራስ ተፈሪ አነጋገሥ | 148 |
| ምዕራፍ ፲፭ | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | 153 |
| ምዕራፍ ፲፮ | ጃንሆይ እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ | 156 |
| ምዕራፍ ፲፯ | የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ | 171 |
| ምዕራፍ ፲፰ | የማይጨው ጦርነት | 176 |
| ምዕራፍ ፲፱ | ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ዘመን | 193 |
| ምዕራፍ ፳ | የጣሊያን ወረራ | 203 |
| ምዕራፍ ፳፩ | የጣሊያን ጊዜ | 208 |
| ምዕራፍ ፳፪ | የድል ጉዞ ወደ አገር ቤት | 222 |
| ምዕራፍ ፳፫ | ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት መልስ | 226 |
| ምዕራፍ ፳፬ | አዲስ ዘመን | 239 |
| ምዕራፍ ፳፭ | የኤርትራ ታሪክ ዳሰሳ | 247 |
| ምዕራፍ ፳፮ | የሕዝብ ቅሬታዎች | 261 |
| ምዕራፍ ፳፯ | ራስ ተፈሪያን | 271 |
| ምዕራፍ ፳፰ | ሃይማኖትና ንጉሠ ነገሥቱ | 275 |
| ምዕራፍ ፳፱ | ያለፉትን ማስታወስ | 281 |

ማውጫ


| ምዕራፍ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፲ | ሙስና | 291 |
| ምዕራፍ ፲፩ | መሠረተ ልማት | 298 |
| ምዕራፍ ፲፪ | ጃንሆይና ዲሞክራሲ | 323 |
| ምዕራፍ ፲፫ | የጃንሆይ ተቃዋሚዎች | 328 |
| ምዕራፍ ፲፬ | የጃንሆይ ወዳጆች | 343 |
| ምዕራፍ ፲፭ | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባሕርይና ትክለ ሰውነት | 355 |
| ምዕራፍ ፲፮ | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጆች | 363 |
| ምዕራፍ ፲፯ | የውዳሴ ከንቱ አስተዳደር | 383 |
| ምዕራፍ ፲፰ | ሁለት ሉሉዎች በቤተ መንግሥት | 392 |
| ምዕራፍ ፲፱ | ንጉሠ ነገሥቱ በአጠቃላይ ዕይታ | 395 |
| ምዕራፍ ፳ | ተፈጥሮና የሰው ልጅ | 397 |
| ምዕራፍ ፳፩ | ሪፑብሊክና ሞናርኪ | 402 |
| ምዕራፍ ፳፪ | የምሁራን አስተዋጽዖ | 408 |
| ምዕራፍ ፳፫ | የተማሪ ንቅናቄ | 411 |
| ምዕራፍ ፳፬ | የሕዝብ እንቅስቃሴ | 416 |
| ምዕራፍ ፳፭ | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መጨረሻ | 423 |




# ምዕራፍ ፩

## የንግሥና ሥርዓትና የነገሥታት ዘር ሐረግ

ከኢትዮጵያዊው ንጉሥ ተዋስያንና ከእናቷ ከእቴጌ ኤስሜኒ የተወለደችው ንግሥተ ሳባ ተብላ የምትታወቀው የኢትዮጵያ ንግሥት ከክርስቶስ ልደት በፊት 1013 ዓመት (በ3,987 ዓመተ ዓለም) ላይ የነገሠች ስትሆን በጽሑፍ ከተገኙት መረጃዎች የኢትዮጵያ ነገሥታት ተርታ 52ኛዋ በጠቅላላው ከነገሡት ነገሥታት ተርታ ደግሞ 98ኛዋ ነበረች። ስሟ ገንኖ የሚታወቅበት ምክንያት ንጉሥ ሰሎሞን የእሥራኤል ንጉሥ በነበረበት ዘመን ዝናውን ሰምታ ታምሪን በሚባለው ኢትዮጵያዊ ነጋዴ አማካኝነት ልትጎበኘው በመሄዷና ከተመለሰችም በኋላ ከንጉሥ ሰሎሞን እብነ እልኪምን ስለወለደች ነው ተብሎ ስለሚነገር ነው። እብነ እልኪም ትርጉም የብልሃተኛ ልጅ ማለት ነው።

ንግሥተ ሳባ ለ31 ዓመት ስታስተዳድር ቆይታ መንግሥትዋን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ዓመት (በ3,518 ዓ.ም.) ለልጇ ለእብነ እልኪም አውርሳ ቀዳማዊ ምኒልክ ወይም ዳዊት ተብሎ ነገሠ። ንግሥተ ሳባ ሥልጣኗን ከመልቀቋ አስቀድሞ የንግሥና ሥርዓት አውጥታለች። ሥርዓቱም "የኢትዮጵያን ዘውድ ጭኖ በትረ መንግሥት ጨብጦ መግዛት ያለበት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የተወለደ እንዲኾን፣ መንግሥትም ከእሱ ዘር እንዳይወጣ" ብላ ከማስወሰኗም በላይ ከንግሥተ ሳባ (ንግሥት ማክዳ ወይም አዜብ) በኋላ "ከወንዱ ወገን እንጂ ከሴት ወገን የቀዳማዊ ምኒልክን ሥርወ መንግሥት ዘውድ እንዳይጭኑ" ስትል በሕግ እንዲከለከል አደረገች[1]።

[1] ባለታሪክ ኢትዮጵያ ገጽ 31

ንግሥት ሳባ ያወጣችው ሕገ ደንብ መነሻ ያደረገው የዳዊት ልጆች የእግዚአብሔር ኪዳን እንደማይለያቸው በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 131 ከቁጥር 11 እስከ 12 የተጠቀሰውን ያገናዝባል። በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 5 ቁጥር 5 የይሁዳ አንበሳ አሸናፊ መሆኑ ሲገለጽ የኢትዮጵያ መንግሥት ንጉሣዊ አስተዳደር ከመሆኑም በላይ የንጉሡ ዘር በንጉሥ ሰሎሞን ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች አማካይነት በኪዳኑ መሠረት እየተፈጸመ ነው ተብሎ ይታመን ነበር።

በዚህም ምክንያት ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ሲተረክ ሦስት ሺህ ዓመት የሚባለው ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ ለመጥቀስ ሲባል ነው። ከሦስት ሺህ ዓመት በፊት በፅሑፍ 51 በቃል 47 በጥቅሉ 98 ነገሥታት የነገሡበት ዘመን ለአገሪቱ የነፃነት ዕድሜ ቆጠራ እንኳን ሳይካተት ነው። ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2800 ዓመት ጀምሮ የምትታወቅና በጠቅላላው የ4800 ዓመት ዕድሜ ያላት መሆኑ በታሪክ ይደገፋል። በመጀመሪያ ፑንት ቀጥሎም ደማቴቴ አስከትሎም አክሱማዊ በመባል ትታወቅ ነበር። በኋላ ላይ ንጉሦቹ የዚህና የዚያ አገር ንጉሥ እየተባሉ የአካባቢውን ቦታ ስም ሁሉ መደርደር ጀመሩ። መጨረሻ ላይ በጎረቤት አረቦች ሃበሻ የሚል ስም ሰጥተዋት የነበረች አገርና ከ5ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ ተብላ የምትታወቅ አገር መኾን ጀመረች። ንግሥተ ሳባም ኾነች ቀዳማዊ ምኒልክ የነገሡት በዚችው አሁን ኢትዮጵያ ብለን በምንጠራት አገር ነገሥታት ተወላጅነት እንጂ በእሥራኤል ነገሥታት ተወላጅነት ምክንያት አልነበረም። ስለሆነም ኢትዮጵያ ታሪክ መመዝገብ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በነፃነት የምትኖር አገር ናት ማለቱ ትክክል ይመስላል። የተባበሩት መንግሥታትም የመዘገበው ይኽንኑ ነው። ስለዚህ የአገሪቱን የነፃነት ዕድሜ ከቀዳማዊ ምኒልክም ሆነ ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ መቁጠር ስፖለቲካ ጥቅም ካልሆነ በቀር በታሪክ ሂደት ትክክል አይደለም።

ይሁንና ንግሥተ ሳባ ከልጅዋ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ያወጣችው ሕገ ደንብ እንዲጸና ካደረገው ምክንያት ዋንኛ የኾነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውና በነብዩ ሳሙኤል ለንጉሥ ዳዊት የተሰጠው ቃል ኪዳን ነው። አንድ ንጉሥ በሞተ ጊዜ የሚቀጥለው ንጉሥ በሕገ ደንቡ መሠረት ይነግሥ ነበር። መቀመጫውም በአክሱም ቤተ መንግሥት ሲሆን፣ ከጊዜ ብዛት መንግሥቱ እየደከመ ሄዶ በ842 ዓ.ም ዮዲት የምትባል ንግሥት ነግሣ ጭራሹኑ አጠፋችው። ቀጣዩ አልጋ ወራሽም



ወደ ሸዋ ሸሸ። የቀሩት የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች ንጉሡን እንዳይቀናቀኑ በወቅቱ ደብረ ዳሞ መታገት ልማድ ስለነበረ እዚያው እንዳሉ በሙሉ ፈጀቻቸው።

ከዮዲት ዘመነ መንግሥት ቀጥሎ በ882 ዓ.ም አንበሳ ውድም ከሸዋ ተመልሶ የአክሱምን መንግሥት እንደገና ለሃያ ዓመት አጸና። ቀጥሎም ድል ነአድ ማዕደይ ለአንድ ዓመት ገዛ። በ902 ዓ.ም. መራ ተክለ ሃይማኖት ከአንበሳ ውድም ልጅ ከድል ነአድ ማዕደይ መንግሥቱን ቀምቶ የዛጔ ሥርወ መንግሥትን በላስታ መሠረተ።

በ12ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት በዛጔ ሥርወ መንግሥት ጊዜ ንጉሥ አርማህ በሚገዛበት ወቅት ኢትዮጵያ በየጊዜው ከግብጽ ሊቀ ጳጳስ ማስመጣቷን ስላልወደደ ከእኛ ውስጥ ሰው ሹሙልን ብሎ ግብጾችን አጥብቆ ጠይቋቸው ነበር። ይህንንም ሊያሳስበው የቻለው•

1) ከግብጽ የሚመጣው ሊቀ ጳጳስ ቋንቋ ስለማይችል ሥራው በአገሪቱ ዋና ከተማ ተቀምጦ ቅስናና ዲቁና መስጠት ብቻ ነው።

2) አንዱ ሊቀ ጳጳስ ሲሞት ሌላ እስኪመጣ ብዙ ጊዜ ያለ ጳጳስ መኖር ግድ ኾነ።

3) በየጊዜው ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ለማስመጣት የኢትዮጵያ ነገሥታት ለግብጽ መንግሥትና ለኮፕት ቤተ ክርስቲያን ወርቅ፣ ብር፣ ዕንቁ፣ አልማዝ፣ እንዲሁም እንስሳት ገጸ በረከት ይልካሉ።

4) ክርስቲያን ያልሆኑ አጭበርባሪዎች ተሹመናል እያሉ የመጡበትም ጊዜ ስለነበረ።

5) በግብጽ መሪዎች እየታዘዙ የሚመጡ ጳጳሶች መስጊድ እስከማሠራት የደረሱበትም ጊዜ ስለነበረ ነው።

ስንክሳራችን ይህንን ሲያብራራልን ንጉሥ አርማህን ስሙን እንኳን ሳያነሳ ኢትዮጵያዊ ኤጲስ ቆጳሳት እንዲሾሙ በመጠየቁ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በአገሩ በኢትዮጵያ ላይ መቅሠፍት አወረደበት[2] ይላል። ግብጾች

---

[2] የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 40

ይህን የመሳሰሉ በርካታ ጽሑፎችን ጊዜ ፈጅተው በመጽሐፍ ጽፈው፣ የኢትዮጵያን ታሪክ አዛብተው፣ አንዳንድ ነገሮች ላይ ዋሽተው፣ አዘጋጁ። በኒቂያ ላይ በተደረገው የአብያተ ክርስቲያን ጉባዔ ላይ በሃሰት በ325 ዓ.ም "ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ እንዳይሾም" ተወስኗል አሉ። ንጉሥ ላሊበላ የአርማህን አስተሳሰብ ለውጦ ከግብጽ ሊቀ ጳጳስ ስላስመጣ ግብጾች ቅዱስ ላሊበላ እያሉ አሞካሽተውታል።

ግብጾች የዛጌ ሥርወ መንግሥት ላይ ቂም ስለነበራቸው እሱን ለማጥፋትና በምትኩም የቀድሞውን ሥርወ መንግሥት በእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑን ለማስረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ በማያያዝ የኢትዮጵያን ታሪክ በጽሑፍ አቀረቡ። ፍትሐ ነገሥት የተጻፈው በዚያን ወቅት በግብጾች ነው።

መንግሥቱን የዛጌ ሥርወ መንግሥት በሚያስተዳድርበት ጊዜ ከሃይማኖት ሰዎች ለሚደርስባቸው ተቃውሞ መከላከያ 'እኛም ሙሴ ያገባት ኢትዮጵያዊት ሴት ከምድማዊቷ የሙሴ ሚስት ከጺፋራ (ዘፀ.2-21) ሐረግ ትውልድ አለን' በማለት መልስ ይሰጡ ነበር።

የዛጌ የመጨረሻው ንጉሥ ሀርቦይ በአፄ ይኩኖ አምላክ ጦር ድል ሆኖ ሲሞት ንግሥናው በ1253 ዓ.ም ወደ ቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት ተዛወረ። የቤተ ክህነት አለቆች በተለይ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ይፈሩና ይከበሩ ስለነበረ ወደፊት ደም እንዳይፈስ ሕዝቡን አረጋግተው የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት ትክክለኛ መንግሥት መሆኑን እንዲቀበሉ አሳመኑ። የዛጌ ሥርወ መንግሥት ወራሾችም ተከብረው ዋግሹም በሚል ማዕረጋቸው ባላባትነታቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ ኾነ። ይህ ስምምነት ለቤተ ክርስቲያንም ሲሦ መንግሥትን አስገኘ። በዚህም ምክንያት ከመንግሥት መሬት አንድ ሦስተኛው ለቤተ ክርስቲያን ይሰጥ ጀመር።

የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት በተለያዩ ወቅቶች ጠላቶች ቢነሱበትም ግብጾች በአስተማሩት ታሪክ ምክንያት ሥልጣኑን ሳይለቅ ከ1253 ዓ.ም አንስቶ አገሪቱን ማስተዳደር ቀጠለ።



ከነዚህ የተለያዩ ተቃውሞዎች መካከል ዋንኛው በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተነሳው የግራኝ አሕመድ ጦርነት ነዓር። የንጉሡ ወታደሮች የታጠቁት የጦር መሣሪያ ገና ጦርና ጎራዴ በነበረበት ወቅት የግራኝ ወታደሮች ግን የታጠቁት ከቱርክ የመጣላቸውን ነፍጥና መድፍ ነበር። ወታደሮቹም ተቀጥረውና በፈቃዳቸው የመጡ የአረብና የቱርክ የጦር አሠልጣኞችና አማካሪዎች ነበሯቸው። የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት በወቅቱ በሸዋ ተቀምጦ የነበረውን የአፄ ልብነ ድንግልን ኃይል የአሕመድ ግራኝ ጦርነት እያዳከመውሲመጣ ንጉሡም ወደ ስሜን ሸሸ። በኋላም ደብረ ዳሞ ተሸሽጎ እያለ በ1530 ዓ.ም ሞተ። ከዚያም ልጁ አፄ ገላውዴዎስ እንደ ነገሠ በክርስቶፎር ዳጋማ መሪነት የፖርቱጋል ወታደሮች የፖርቱጋል ቅኝ ከነበረችው ከጎዋ (ህንድ) አዲስ የጦር መሣሪያ ይዘው ስለደረሱለት መልሶ በማጥቃት የግራኝን ኃይል መቋቋም ቻለ። ሆኖም የጠላቱን ኃይል መደምሰስ ስላቃተው በደፈጣ ውጊያ ሲከላከል ኖሮ በመጨረሻ በ1535 ዓ.ም ግራኝን ድል አድርጎ መንግሥቱን አጠናከረ።

ቀጥሎም የግራኝ አሕመድ የእኅት ልጅ ኑር ሙሐመድ የግራኝን ሚስት ድል ወንበራን ለማግባት የንጉሡን ጭንቅላት ቆርጦ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ነበር። ቃል በገባው መሠረት የግራኝ አሕመድን ዓላማ ተከትሎ በ1549 ዓ.ም የሐረርን ግንብ በማሠራት ኃይሉን አጠናክሮ ተነሳ። ስለሆነም ኑር ሙሐመድ ዕድል ቀናውና አፄ ገላውዴዎስን ገድሎ ሠራዊቱንም ድል አደረገ። ኑር ሙሐመድ ለማገገምና እንደገና ተጠናክሮ ለመመለስ ወደ ሐረር በመሄድ ላይ እንዳለ መንገድ ላይ አድፍጦ ይጠብቅ የነበረው በምችሌ የሚመራው የኦሮሞ ጦር ወታደሩን ለወሬ ነጋሪ እንኳን ሳያስቀር ሙጥጥ አድርጎ ፈጀው። ከዚህ ወቅት በኋላ የግራኝ ንቅናቄ አበቃ።

ከአፄ ገላውዴዎስ በኋላ ወንድሙ አፄ ሚናስ በ1549 ዓ.ም ነግሦ ለአራት ዓመት ገዛ። ቀጥሎ የአፄ ሚናስ ልጅ አፄ ሠርፀ ድንግል በ1553 ዓ.ም ነግሦ ከተማውን ከደብረ ታቦር ወደ ጎንደር አዞረ። ኃይሉንም አጠናክሮ ቱርክን በ1570 ዓ.ም ድል አድርጎ ምፅዋን ስላስመለሰ ጃንሆይ በሚል የክብር ስም ይጠራ ጀመር።

የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች የንግሥተ ሳባን ሕገ ደንብ እየተከተሉ መንግሥቱን ይዘው ሲኖሩ በመሃሉ ለዕርዳታ የመጡት አበዛኛው

ፖርቱጋሎች ወደ አገራቸው ተመልሰው የኢትዮጵያውያንን ክርስቲያንነት በመናገራቸው ይኸንኑ ሰምተው የመጡ ኢየሱሳውያን (ጀስዊትስ) የካቶሊክ ዕምነት ተከታዮች ስብከት ጀምሩ። በዚህም ሳቢያ ንጉሥ ሱስንዮስ ወደ ካቶሊክ ዕምነት ስለተለወጠና ሕዝቡንም እንዲለወጥ ስላስገደደ፣ ሌላ የሃይማኖት ጦርነት ተቀስቅሶ ለስምንት ዓመት ብዙ ሰው ከተጎዳና መንግሥቱም ከተዳከመ በኋላ የአልጋው ወራሽ የኾነው ፋሲል በ1623 ዓ.ም ነገሠና አስተዳደሩን ወደ ጥንቱ ሃይማኖት መልሶ መንግሥቱን እንደገና አጠናክሮ ስመ ጥሩውን የጎንደርን ግንብ አሠራ።

ከጊዜ በኋላ የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት በጎንደር እየደከመ ሄዶ የንጉሡ እንደራሴ የነበረው ሥሑል ሚካኤል ንጉሥ ኢዮአስን በ1763 ዓ.ም ገድሎ በሥልጣን ከንጉሦቹ በላይ መሆን ስለቻለ ዘመነ መሳፍንት ተጀመረ። ሥሑል ሚካኤል ያልነገሠበት ምክንያት የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጅነት ስላልነበረው ነው። ለሰማኒያ ሦስት ዓመት እንደራሴዎች የመንግሥቱን ሥልጣን ይዘው ለስም ብቻ ንጉሦች እየሾሙ እየሻሩ ሲኖሩ በሸዋ ቀርቶ ከነበረው ከአፄ ልብነ ድንግል ልጆች መካከል የአቤቶ ያዕቆብ ተወላጆች የሆኑት ከባላባትነት ወደ ንጉሥነት አድገው እየጎለበቱ ሄዱ። በተለይ ራስ ወሰን ሰገድ


ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ወሰን ሰገድ

አስከትሎም ልጃቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (አባ ዲና) በዘመኑ የነበረውን እንደራሴ አሸንፈው አገሪቱን በንጉሡ ነገሥትነት ለመጠቅለል ያስቡ ነበር። ለዚህም ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በሚዘጋጁበት ወቅት የጦር አበጋዛቸው ለሆነው ባሻ መተኮ ቦርጂያ ልጃቸውን ለልጁ ለጃራ ሲድሩለት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገለጹ። በኋላ ላይ ሰዎች ስለ ባሻ መተኮ አጉድፈው ስለነገሯቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ መልሰው ልጃቸውን ቢከለክሉት ክፉኛ ተቆጥቶ በስለት ሊገድላቸው በመሞከሩ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ መጠነኛ ሽብር ተነስቶ ይኸንኑ በሚያስተካክሉበት ወቅት ታመው ሞቱና ዕቅዳቸው ተጨናገፈ።



በዚህ መካከል ቋረኛው ካሣ በጎንደር ያለውን የመንግሥት ኃይል በእጃቸው ካስገቡ በኋላ ወደ ሰሜን ተጉዘው አሁንም የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን ድል በመምታት አፄ ቴዎድሮስ (አባ ታጠቅ) - ገብሩ ለክርስቶስ ተብለው በ1845 ዓ.ም ነገሡ። አፄ ቴዎድሮስ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ወሎ ቀጥሎም ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ታመው ይሞቱና ሠራዊታቸው ተሸንፎ ቀጣይ የመንግሥቱን ወራሽ የ12 ዓመት ልጅ ምኒልክን ይዘው ወደ ጎንደር ተመለሱ። በ1860 ዓ.ም ከአፄ ቴዎድሮስ ህልፈተ ሕይወት በኋላ የስሜኑ ባላባት ዋግ ሹም ጎበዜ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ለሦስት ዓመት ነገሡ። ቀጥሎም የትግራዩ ደጃዝማች ካሣ ምርጫ በ1863 ዓ.ም አፄ ዮሐንስ አራተኛ ተብለው ለ18 ዓመት ዘውድ ጫኑ። በመጨረሻም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ በ1882 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ተብለው እስከ 1906 ዓ.ም ኢትዮጵያን በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር አስተዳደሩ።


ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ

በመሳፍንት ዘመን በጎንደር የነበሩት የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች ኃይላቸው በእንደራሴዎቹ ስለተወሰደና ማንሰራራት ስላቃታቸው አፄ

ቴዎድሮስ፣ አፄ ተክለ ጊዮርጊስና አፄ ዮሐንስ በተወላጅነት ሳይሆን በጦር ኃይላቸው ለመንገሥ ችለዋል። መጨረሻ ላይ ዳግማዊ ምኒልክ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅነት ወይም በቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት ተወላጅነት ነገሡ። ስለኾነም የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት በመሳፍንት ዘመንና ከዚያም ተከትሎ አጥቶት የነበረውን ኃይልና የተወሰደበትን ንግሥና በዳግማዊ ምኒልክ አስመልሷል።

አፄ ምኒልክ ወልደዋቸው የነበሩት ሁለት ወንዶች ልጆቻቸው አስቀድመው ስለሞቱ፡ ለሴት ልጃቸው ወንድ ልጅ ለአቤቶ ኢያሱ መንግሥታቸውን አወረሱ። አቤቶ ኢያሱም ተሻረና የምኒልክ ሌላዋ ሴት ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱ ነግሠው ከእሳቸው በኋላ የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ተፈሪ መኮንን ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነገሡ። ሁለቱም ክስተቶች የሚያረጋግጡልን ከዳግማዊ ምኒልክ ህልፈተ ሕይወት አስከትሎ የንግሥተ ሳባ ሕገ ደንብ ተጥሶ ዘውድ እንዳይሆን የተከለከለው የሴት ወገንን ማንገሥ መጀመሩን ነው። በንግሥተ ሳባ የተደነገገው የአነጋገሥ ሥነ ሥርዓት በቀዳማዊ ምኒልክ ተጀምሮ ለ2919 ዓመት የቆየው ሥርወ መንግሥት ከዳግማዊ ምኒልክ በኋላ ተዛባ።



ደጃች ወሰን ሰገድ ምኒልክ (በ14 ዓመት ለደ'ማ የሞተው)

የአፄ ልብነ ድንግል ልጆች በርካታ ሲሆኑ እሱን ተከትሎ የነገሡት አፄ ገላውዴዎስ ነ[ ]። ሆኖም ከብዙ ልጆቹ መካከል ሸዋ ቀርቶ የነበረው የአቤቶ ያዕቆብ የልጅ ልጆች እንደሚከተለው ተራ በተራ በባላባትነት በኋላም በንጉሥነት ሸዋን ሲያስተዳድሩ ኖረዋል።



## የአጼ ልብነ ድንግል ወናግ ሰገድ ትውልድ

አጼ ልብነድንግል
አቤቶ ያዕቆብ
አቤቶ ገራም ፋሲል
አቤቶ ስገወ ቃል
አቤቶ ወረደ ቃል
አቤቶ ልብሰ ቃል
አቤቶ ነጋሢ
መርዕድ አዝማች . ስብስትያኖስ
መርዕድ አዝማች. አብዬ
መርዕድ አዝማች. አምኃ ኢየሱስ
መርዕድ አዝማች. አስፋ ወሰን
ራስ ወሰን ሰገድ
ንጉሠ ሣህለ ሥላሴ

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከአባታቸው ከራስ ወሰን ሰገድና ከእናታቸው ከወይዘሮ ዘነበ ወርቅ በ1788 ሸዋ በሰላ ድንጋይ ከተማ ተወለዱ። ሸዋን 34 ዓመት ከአራት ወር በንጉሥነት አስተዳድረው ጥቅምት 12 ቀን 1840 ዓ.ም በደብረ ብርሃን ከተማ አርፈው በአንኮበር ተቀበሩ። በሸዋ የነበሩት ባላባቶች ዝነኛ መሆን ጀምረው ስለነበረ አማርኛ ቋንቋ ውስጥም የአንዳንዶቹ ስም መደባለቅ ጀምሮ በሸዋ አማርኛ የሚከተሉት ዘይቤዎች ተለመዱ።

| | | |
|---|---|---|
| ሩቅ | ለማለት | አንጨቆረር፣ |
| ታች | " | እንጦሮጦስ፣ |
| ጥንት | " | የስብስቴ ጊዜና |
| ድሮ | " | የአምኃየስ ጊዜ |

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከተለያዩ ሴቶች 15 ልጆች ሲኖራቸው አወላለዳቸውም እንደሚከተለው ነበር።

ሀ) ከሥልጢዋ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ወሪጋ
ራስ ዳርጌ (የበኵር ልጅ)

በ) ከሕግ ሚስታቸው ከወይዘሮ በዛብሽ ደጀን
1ኛ ኃይለ መለኮት
2ኛ ሠይፉ
3ኛ ወሰን የለሽ

ገ) ከሩሲያዊ አባት ከተወለደችው ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ይመኙሻል ቡንኝ
1ኛ ኃይሌ
2ኛ ተናኘ ወርቅ

ደ) ከቡልጋዋ ተወላጅ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ማለፊያ
1ኛ እያሀሉሽም
2ኛ ጠንፍ የለሽ

ጀ) ከወሎየዋ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ እቴነሽ
1ኛ ብርቅነሽን

ሀ) ከአርሲ ባላባት ከአርባ ጉጉ ተወላጅ ከኾነችው ዕቁባታቸው
1ኛ ካሡኝ


ወ) ከዕቁባታቸው ከወይዘሮ ማረፊያ
1ኛ ወርቅ አፈራሁ
2ኛ እቻምየለሽ

ዘ) ከአልዩ አምባ ተወላጅ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ብዝት
1ኛ ባሕርይ
2ኛ ሙላት ወርቅ
3ኛ በለጥሻቸው


ከዚህ በማስከተል የሴት ልጆችን የዘር ሐረግ አስፈላጊ ሲኾን ብቻ በመጥቀስ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።




## የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ትውልድ



## የንጉሥ ኃይለ መለኮት ትውልድ





## የመርዕድ አዝማች ኃይሌ ትውልድ







## የአቤቶ ሠይፉ ትውልድ




## የአቤቶ ባሕርይ ትውልድ

አቤቶ ባሕርይ ልጅ አልነበራቸውም።


## የራስ ዳርጌ ትውልድ





ወይዘሮ ትሰሜ ከንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ (ዋግ ሹም ጎበዜ) ታናሽ ወንድም ከደጃች ኃይሉ ራስ ካሣን ወልደዋል። በተጨማሪም ሌሎች ወንዶች ልጆችም አፍርተዋል።



## የአቤቶ ካሡኝ ትውልድ




## የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ትውልድ




አፄ ምኒልክ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው መንግሥታቸውን ማስተላለፍ የነበረባቸው ለአጎታቸው ልጅ ለመሸሻ ሠይፉ ወይም ከመሸሻ ልጆች ለአንዱ ወንድ ልጅ መሆን ሲገባው ለሴት ልጃቸው ለወይዘሮ ሸዋረጋ ምኒልክ ወንድ ልጅ ለአቤቶ ኢያሱ ማላለፋቸው በተለምዶው መሠረት ስህተት ነበር። የአፄ ምኒልክ ተወዳጅነት ከፍተኛ ስለነበርና በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንቶችም ኾነ መኳንንቶች ቃላቸውን ለማክበር ሲሉ አሜን ብለው በመቀበላቸው ይኸ ስህተት የነገሮች መዘበራረቅን አስከትሏል።

የዛጔ ነገሥታት ሃይማኖት አጥባቂዎችና በአንድ ሚስት ብቻ የተወሰኑ ነበሩ። ከእነሱ ቀጥሎ በተከታታይ ከነገሡት መካከል አፄ ልብነ ድንግል በአንድ ሚስት ብቻ የተወሰኑ ነበሩ። የተቀሩት ግን እንደ ልምድ አድርገውት ብዙ ዕቁባቶች በየቦታው ያስቀምጡ ነበር። እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ ንጉሦች ከዋና ሚስት ሌላ ዕቁባቶችም የማስቀመጥ ልምድ ነበራቸው። ስለሆነም ከተለያዩ እናቶች የሚወለዱ ልጆች እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው።

ንጉሦችም ኾኑ ሌሎች የበታች ሹሞች በየአገሩ እየሄዱ ብዙ ጊዜ ስለሚቀመጡ ዕቁባቶች በየቦታው ይኖራቸዋል። ልጅም ቢወለድ ከሚስት አልተወለደም ተብሎ ልጅነቱ አይናቅም ነበር። እንዲያውም ብዙ ልጆች በወለዱ ቁጥር የእግዚአሔር ፀጋ እንደሆነ ስለሚቆጥሩት ይደሰቱበታል እንጂ አያፍሩበትም። ስለኾነም ብዙዎቹ የዘመኑ ትላልቅ ሰዎች የልጆቻቸው ቁጥር በርካታ ነበር። ለምሳሌ ያህል የትግራዩ ሹም አጋሜ ወልዱ ሃምሳ ልጆች፣ የጎጃሙ ደጃች ተድላ ጓሉ አሥራ አራት ልጆች፣ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትም ሃያ ልጆችና የሼህ ሆጀሌ ልጆች ሰባ ሁለት እንደነበሩ ይነገራል።

## ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ምኒልክ ከአሥር ዓመት ግዞት በኋላ በ22 ዓመት ዕድሚያቸው ከአፄ ቴዎድሮስ አምልጠው ሸዋ ከገቡ በኋላ ነሐሴ 24 ቀን 1857 ዓ.ም አንኮበር ላይ የሸዋ ንጉሥ ኾነው ዘውድ ጫኑ። ከአፄ ዮሐንስ ህልፈተ ሕይወት በኋላም በ1882 ዓ.ም "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" ብለው አወጁ። ከአፄ ምኒልክ ቀጥሎ በዚሁ ተቀጽላ የነገሡት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በኋላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ። ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ልጅ ከቀዳማዊ ምኒልክ አንስቶ ሲቆጠር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ **225**ኛ ንጉሥ ናቸው። ይህንን ተቀጽላ ንጉሦቹ ያወጁበት ምክንያት የይሁዳ ዘር የንጉሥ ዳዊት ትውልድ ነን በማለት በሕዝብና በቀሳውስቶች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ስለሚፈልጉ ነው። በቀደሙት ጊዜያት በዚህ ተቀጽላ ራሱን የገለጸው አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ብቻ ነበር።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለ ንጉሠ ሲነግሥ የሌላ ተወዳዳሪን ቅስም ከመስበሩም በላይ በሰፊው የክርስትና ተከታይ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል። የዛሬ ዘመን ሰው ይህንን ይቀበለዋል ብሎ



ለማለት ያስቸግራል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ የይሁዳ አንበሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ ይህ ስያሜ ትርጉም አይሰጣቸውም።

ዛሬ ዴሞክራሲ የሚባለውን ቃል ዘመናዊ ፖለቲከኞች እንደሚጠቀሙበት ሁሉ ቀደም ብሎ የነበሩት ነገሥታት ሃይማኖትንና የዘር ግንድን ለሥልጣን መወጣጫነት ይጠቀሙበት ነበር። የቋንቋና የዘዴ ልዩነት እንጂ ዓላማውና ግቡ አንድ ነው። ሕዝብ ቀደሞም ኾነ አሁን የሚፈልገው ከወገኑ አንድ ሰው መርጦ እንዲያስተዳድረውና ሥራውንም መሥራት ባቃተው ጊዜ ወይም በሞት ሲለይ በሌላ ለመለወጥ ነው። ሥልጣኑን የጨበጠው ሰው ግን ከያዘው ስፍራ ላለመነቃነቅ እንዲያውም ሲሞት ልጁን ለመተካትና በሥልጣን እርካብ ላይ የዘር ዘሩ እንደተፈናጠጠ እንዲቆይ በሚሸርበውና በሚሠራው ተንኮል ሕዝቡ ለመሪዎቹ መገልገያ መሣሪያ እየሆነ እንዲኖር ይገደዳል። አልፎ ተርፎም ጥቅም ፈላጊዎች ሥልጣን ላይ ላሉት ሰዎች በምን ዓይነት ዘዴ በሥልጣን ለመቆየት እንደሚችሉ ብዙ መላ ይተልሙላቸዋል። የጥቅም ፈላጊዎች ተሳትፎ በመንግሥት ሥልጣን አያያዝና ቆይታ ላይ ቀላል አይደለም።

## የሴቶች እኩልነት

አንድ ነገር ብዙ ጊዜ ሲደጋገም ትክክል መስሎ ይታያል። አንድ ሰው በልምድ እየተበደለ ከበደሉ ነፃ የሚያወጣውን ሰው ራሱ ተበዳዩ እንደሚታገለው ይታወቃል። አንድ ሴት ልጅ ስትወልድ "ምን ወለደች" ሲባል "ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ" ከተባለ "እሰይ!" ይባላል። የወለደችው "ሴት" ነው ሲባል "ትሁን" ይባላል። እንደዚህ የሚሉት ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም ናቸው።

ንግሥተ ሳባ የመንግሥቱ ወራሾች በወንድ በኩል ያሉት ናቸው ስትል የሴቶችን መብት መርገጧ መሆኑ በተለይ በአሁኑ ዘመን ቁልጭ ብሎ ይታያል። ንግሥተ ሳባ ብቻ ሳትሆን እስከ ዘመናችን ድረስ ያለው የአነጋገሥ ሁኔታ በየትም ዓለም በወንድ ተወላጅ በኩል ነው የሚወሰነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያው ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ሲሆኑ አልጋ ወራሽ የተባሉት የመጀመሪያ ወንድ ልጃቸው ልዑል አስፋ ወሰን ናቸው። በሌሎችም አገሮች የሚደረገው እንዲሁ ነው። ለነገሩማ አሜሪካን አገር ላለፉት ሁለት

መቶ ዓመት ሴት ለፕሬዚዳንትነት ቀርቶ ለምክትልነት እንኳን አልተወዳደረችም። በዚህ ሁኔታ የእስያ አገሮች የተሻለ ወጤት በሴቶች በኩል አስመዝግበዋል።

ምንም እንኳን ንግሥተ ሳባ ያወጣችው ሕገ ደንብ ተከበረ ተብሎ ቢነገርም ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አንስቶ አሥራ ሦስት ሴቶች በኢትዮጵያ ነግሠዋል። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።


| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ | በ730 ከክር. ል. በፊት | ኒካንታ ቅንዳኬ |
| 2ኛ | በ333 " " " | ተካውላ ቅንዳኬ |
| 3ኛ | በ316 " " " | ኒኮውሲስ ቅንደኬ |
| 4ኛ | በ233 " " " | ኒኮሲስ ቅንዳኬ |
| 5ኛ | በ88 " " " | አወሲና ንግሥት |
| 6ኛ | በ24 " " " | ኒኮትሪስ ህንዳኬ |
| 7ኛ | በ42 ዓ.ም | ገርስሞት ንግሥት |
| 8ኛ | በ230 ዓ.ም | ዋከና ንግሥት |
| 9ኛ | በ299 ዓ.ም | አህየዋ ሶፍያ ንግሥት |
| 10ኛ | በ369 ዓ.ም | አድሃና ንግሥት 1ኛ |
| 11ኛ | በ412 ዓ.ም | አድሃና ንግሥት 2ኛ |
| 12ኛ | በ850 ዓ.ም | ዮዲት |
| 13ኛ | በ1909 ዓ.ም | ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥት |

ከሳባ ዘመነ መንግሥት ቀጥሎ 12 ያህል የሴት ነገሥታት እስከ ዮዲት ድረስ ነግሠዋል። ከዮዲት በኋላ ግን ለአንድ ሺ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ያህል ሴት ሳትነግሥ ቆይታ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በ1909 ዓ.ም ነገሡ። ይኼም ከዛጔ ሥርወ መንግሥት መውደቅ አንስቶ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ሴት አለመንገሧን ያመለክታል። የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት አስተሳሰብ ተፈጥሮና ኃይል አግኝቶ የንግሥተ ሳባ ሕገ ደንቡ ሥራ ላይ የዋለው ከዛግዌ ሥርወ መንግሥት መውደቅ በኋላ መሆኑን ፍንጭ ይሰጣል። ስለሆነም የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት አስተሳሰብ በግብጾች የተወጠነና የዛግዌ ሥርወ መንግሥትን ለመቃወም የተሸረበ የግብጾች የፈጠራ ታሪክ መሆኑ ይፈነጥቃል።



# ምዕራፍ ፪-
# የተለያዩ ግዛቶች

ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ጎሣ በየግዛቱ ባሉት ባላባቶች እየተዳደረ በአጠቃላይ ግን አገሩ በማዕከላዊው ንጉሠ ነገሥት ሥር ተማክሎ ይተዳደር ነበር። ግብርም ባላባቱ እንደ አካባቢው ሁኔታ እያስገበረ በተራው ደግሞ ራሱ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚጣልበትን ግብር ይከፍላል። አገር ስትወረር ግን ንጉሠ ነገሥቱ በሚመራው ዘመቻ ሁሉም ጎሣዎች በአንድነት ተባብረው ጠላትን ይወጋሉ። ሕዝቡም የዚህ አገር ተወላጅ አይደለህም ተብሎ ሳይለይ እፈለገበት ግዛት ውስጥ የመኖር መብቱ የተጠበቀ ነበር። ወታደርም፣ ዳኛም፣ ገበሬም ሆኖ በፈቀደበት ቦታ መኖር ይችላል። ነጋዴም እንደልቡ እየተዘዋወረ ሸቀጡን ከአንዱ ቦታ ገዝቶ ሌላ ቦታ ይሸጣል። በርሃማ ቦታዎች ላይ ከሚደቀኑበት ዘራፊዎች በስተቀር አስተዳደሮቹ እንዲያውም ይጠብቁታል እንጅ እንቅፋት አይሆኑበትም ነበር።



ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ

በዘመነ መሳፍንት ወቅት የማዕከላዊው መንግሥት ኃይል ተዳክሞ አብዛኛውን አገር መቆጣጠር አቅቶት ከኖረ በኋላ፣ አፄ ቴዎድሮስ ተነስተው አገሩን አንድ ለማድረግና ለመቆጣጠር ሦስት ዙር ጦርነት አድርገው ከፊል ኢትዮጵያን አንድ ካደረጉ በኋላ አልፈዋል።

አፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸው አትኩሮታቸው ሃይማኖት ላይ ነበር። ግራኝ በጉልበት ያሰለመውን እሳቸው ደግሞ በጉልበትም ጭምር ወደ ጥንት ሃይሞኖቱ ለመመለስ ሞከሩ። ይኸው ተግባራቸው

ሃይማኖት አጥባቂዎችን ከአገር አባሮ ወደ ጎረቤት አገር እንዲሰደዱ አደረጋቸው። በንጉሠ ነገሥቱ ሥር ሌሎች ንጉሦችና ባላባቶች ሲኖሩ እያንዳንዳቸው የአፄ ዮሐንስን የበላይነት በመቀበል አገሪቱን በደቡብ በኩል ከቅኝ ገዥዎች ለማዳን እየተዋጉና እሳቸውም በሰሜን በኩል ያለውን ወሰን እያስከበሩ አገር እያስተዳደሩ ኖረዋል።


ዳግማዊ አፄ ምኒልክ

አፄ ዮሐንስ በዘመናቸው ብዙ የመከላከል ፍልሚያ ቢያደርጉም ራስ አሉላን ከኤርትራ አገረ ገዥነት ማንሳታቸው ግን አካባቢውን ያለጠባቂ ስላስቀረው መጨረሻ ላይ በቅኝ ገዥዎች ከመቦርቦር ለመከላከል አልተቻለም። ዘመኑ የቅኝ ገዥዎች የመስፋፋት ፍልሚያቸውን ያፋፋሙበት ወቅት ስለነበረ አገሪቱን ከወራሪ ለማዳን ብዙ ጦርነቶች ላይ ተሳትፈው መጨረሻ ላይ ከደርቡሾች (ሱዳን) ጋር ባደረጉት ጦርነት ሕይወታቸውን ሰውተዋል።

ዳግማዊ ምኒልክ በተለይ የደቡቡንና የምሥራቅን ግዛቶች በመጠቅለልና ወሰን በመከለል ረገድ ከቅኝ ገዥዎች የአሁኒቱን ኢትዮጵያ ማትረፍ ችለዋል። በዚህም ወቅት አንዳንድ ባላባቶች ሲገብሩላቸው አንዳንዶች አልገብርም ይሉ ስለነበረ ብዙ ጦርነቶች አካሂደዋል። በጦርነት ከተሸነፉ ባላባቶች መካከል እንደገና ግዛታቸው እየተመለሰላቸው፣ ያልታመኑት ደግሞ ሌላ ባላባት እንዲተካቸው እየተደረገ ግዛቶቹ በሙሉ በአንድነት በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥር የሚተዳደሩ መሆን ሲችሉ ለመጠቅለል ያቃቱዋቸው የሶማሌና የባሕር ነጋሽ ግዛቶች ግን በቅኝ ገዥዎች ሥር ኾነው ቀርተዋል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ በይበልጥ አንድ የኾነችበት ጊዜ ቢሆንም ችግሩ በሥልጣን አወጣጣቸው ምክንያት በየቦታው ጥቃቅን ግጭቶች መካሄዳቸው ነው። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፊት የነበረው ሁኔታ ንጉሥ የነበረው በንጉሥ፣ ባላባት የነበረው በባላባት፣ እያንዳንዱ ክፍለ አገር ከጥንት ጀምሮ በነበረው



ሥርዓት ከሞላ ጎደል ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ራስ ገዝ ነበር። የአገሪቱ የበፊት ነገሥታት በጠቅላላው በአገር ጉዳይ ከየራስ ገዝ አስተዳዳሪዎቹ ጋር ይመካከራሉ እንጂ በውስጥ አስተዳደር ገብተው አይሾሙም አይሽሩም ነበር። በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ግን እያንዳንዱ ንጉሥ ወይም ባላባት ከግዛቱ በየምክንያቱ ተሽሮ አገሩ በሙሉ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ፍጹማዊ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ በተሾሙ አገረ ገዥዎችና ባላባቶች ብቻ ይተዳደር ጀመር። ግብር ሁሉ በቀጥታ ለማዕከላዊው መንግሥት እየገባ በፊት የፌዴራል ቅርጽ የነበረው አስተዳደር የአንድ ኃይለኛ ማዕከላዊ መንግሥት ግዛት ኾነ። ጥንት የነበረው አስተዳደር ምን መልክ እንደነበረውና በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ምን ሁኔታ ላይ እንደደረሰ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## አገው

አገው አግዐዚያን ከደቡብ አረቢያ ወደ ደጋው ኢትዮጵያ ከመፍለሳቸው በፊት አገሩ ላይ ነዋሪ የነበረ የኩሽ ጎሣ ነው። አግዐዚያን መንግሥት አቋቋሙና የአገውንም ሕዝብ በግዛታቸው ጨምረው ያስተዳድሩ ጀመር። በመራ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት አገዎች የመንግሥት ሥልጣን የያዙት ከ920 ዓ.ም እስከ 1255 ዓ.ም ነው። መንግሥታቸው ሲያበቃ በተደረገው ውል መሠረት የዛጔ ሥርወ መንግሥት ወራሾች በባላባትነት ዋግ ሹም እየሆኑ በዋግና ላስታ እንዲቀመጡ ተደረገ። በተገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት የመጀመሪያው ዋግሹም ተብሎ የተሾመው ዮናታን ነው።

ከዮናታን ጀምሮ በተከታታይ በዋግ ሹምነት ማዕረግ ሲኖሩ በ1860 ዓ.ም አፄ ቴዎድሮስ ሲሞቱ ዋግ ሹም ጎበዜ ኃይል ተሰምቷቸው ነበርና ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ በመባል ነግሠው ከሦስት ዓመት በኋላ በባለቤታቸው ወንድም በአፄ ዮሐንስ ተሸንፈው መንግሥታቸው ተወሰደባቸው። ቢሆንም በዋግ ሹምነት ባላባትነታቸው ዋግና ላስታን ማስተዳደር ቀጥለው በ1966 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወርዱ የመጨረሻው ዋግ ሹም ጌታነህ አድማሱ ወሰን ሲታሰሩ ሌላ ዋግ ሹም ስላልተተካ ሹመቱ በእሳቸው አበቃ።

አገው በኢትዮጵያ ምድር ቀደም ብሎ በመኖር የታወቀ ጎሣ ሲሆን የእሥራኤልን ሃይማኖት አስቀድሞ በመቀበሉና ከዮዲት ጋር

በመሠለፉ በኋላ ላይ ተጉላልቷል። የአገው ሕዝብ በብዛት ወደ ክርስትና ሃይማኖት ተለውጠው ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰራጭተው ይኖራሉ። በሰሜን የነበሩት የነገደ ዛጔ የአገው ዘሮች በዕምነታቸው የጸኑ ክርስቲያኖች ነበሩ። በአሁኑ ወቅት የአገው ምድር ሆኖ የሚታወቀው በጣና በስተምዕራብ ያለው የጎጃም ግዛት ነው። በኤርትራ ምዕራብ ከረን አካባቢ ብሊን በመባል፣ በሰሜን ትግራይ ኢሮብ በመባል በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰራጭተዋል። ብሊኖች በፊት ክርስቲያን የነበሩና በኋላ በኃይን እጦት ወደ እስልምና ዕምነት የዞሩ መሆናቸው ይነገራል።

የአገው ጎሣ ከዮዲት ጊዜ ጀምሮ በደረሰበት በርካታ ጦርነት ስለተበታተነ በተለያዩ ሰሞች እንደሚከተለው ይታወቃል።

1ኛ) በሰቆጣ .... ኽምራ
2ኛ) በጎንደር .... ቅማንትና ብሊና[3]
3ኛ) በጐጃም .... አውኚ
4ኛ) በከንባታ .... አገዋ
5ኛ) በትግራይ .... ኢሮብ
6ኛ) በኤርትራ .... ብሌና
7ኛ) በዋግ ...... ኽምጣና

በወሎም ውስጥ ከአፋር ጎሣ ጋር በጉርብትናና በባህል በመመሳሰል አብረው የሚኖሩ እንዳሉ ይነገራል። ሃይማኖታቸውም እስልምና ሆኗል። ምንም እንኳን ጎሣቸው እየተለወጠ ቢሄድም በአገው ሥርወ መንግሥት የጀመረውና የሚታመንበት የዋግ ሹም ተወላጅነት እንዳለ ነው።

በሃይማኖት ሳቢያ ሁሉም ዝርያውን ከሴም ዘር ጋር ለማያያዝ እንደሚጥረው ሁሉ አገዎችም በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን ከነበረውና ቀዳማዊ ምኒልክን አጅቦ ከመጣው ዛራክ እንወለዳለን ይላሉ።

[3] ኢሮቦች አገው አይደሉም የሚሉም አሉ። ብሌና ወይንም ቅማንት ጽላቱን ይዘው በጥቁር ዓባይ ሸለቆ በኩል የመጡ እሥራኤላውያኖች እንደሆኑ እንጂ የአገው ጎሣ እንዳልሆኑም The Sign and Seal የሚለው የግርሃም ሃንኮክ መጽሐፍ ላይ በሰፊው አትቷል።



ስለሆነም የሲራክ ሰባተኛ ትውልድ ዱዳው ሲራክ ሲባል አሁንም የእሱ ሰባተኛ ትውልድ የመጀመሪያው ዋግ ሹም ዮናታን ነበር። ይሁንና እነ መራ ተክለ ሃይማኖትና ቅዱስ ላሊበላ የዚሁ የመጀመሪያው ዋግ ሹም ዮናታን ግንድ ይሁኑ አይሁኑ የሚታወቅ ነገረ የለም።

ንጉሥ ይኩኖ አምላክ የመንግሥቱን ሥልጣን ከዛግዌ ሥርወ መንግሥት በኃይል መውሰዱ ባይካድም በሥልጣን ሽግግር ጊዜ የነበሩትን ውዝግቦች ለማብረድ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት የተካሄደው ድርድር የተቋጨው ይኩኖ አምላክ ተጉለት ናኩቶ ለአብ ላስታ እንደተቀምጡ ነበር። በተደረገው ድርድር የሚከተለው ስምምነት ላይ ተደርሷል።

1ኛ ዛጔዎች ያስ አገባብ የወሰዱትን ሥልጣን መንግሥት ለቀዳማዊ ምኒልክ ዘር መመለስ፣

2ኛ ይኩኖ አምላክ መንግሥቱን ከተረከበ በኋላ ከዛጔ ዘር አንዳንድ መሥፍን እየመረጠ በላስታ አልጋ እንዲሾምና የላስታ ግዛት ከዛጔ ዘር እንዳይወጣ፣

3ኛ ላስታን የሚገዛው መሥፍን የዛጔ ዘር ለመሆኑ ምልክት ሁለት የብር ነጋሪት እንዲያስጭን የዘበኞቹ ጦር በጫፉ የብር ሽቦ እንዲኖረው የዓላማው መያዣ የሰንደቁ ጫፍ የብር እንዲሆን፣

4ኛ የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የሆነው ንጉሥ በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የላስታው መሥፍን በትንሽ የብር ወንበር እንዲቀመጥ ከንጉሡ ጋር በሚገናኙበት ጊዜ ወንድም ከወንድሙ እንደሚገናኝ እንጂ እንደ ሌሎች መሣፍንቶች መሬት እንዳይስም፣


5ኛ በእገሩ ማናቸውንም ዓይነት ግብር እንዳይገብር ሌሎች መሣፍንቶች የሚያደርጉትን ሁሉ እንዳያደርግ፣

6ኛ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በሸዋና በላስታ መካከል እየተመላለሱ ስላስታረቁ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለችግራቸው ማስወገጃ እንዲሆን ከመንግሥቱ ሢሶ መሬት እንዲሰጣቸው የሚሉ ናቸው።[4]

ቃል በተገባው መሠረት የመጀመሪያው ዋግ ሹም ዮናታን ነበር። የዮናታንም ተወላጆች ዋግ ሹምነቱን ሲቀባበሉ ለብዙ መቶ ዓመት

[4] አቶ አረጋዊ ገብረየሱስ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ማስታወሻ ያገኙት

ኖረው ዋግሹም ክንፉ ላይ ደረሰ። የእሱም ልጆች ወንንና ወይዘሮ በተሓ ነበሩ። የወይዘሮ በተሓ የልጅ ልጅ ዋግ ሹም ኀበዜ በይኩኖ አምላክ ጊዜ የተገባውን ውለታ በማፍረስ ራሳቸውን ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ብለው መንገሣቸው የቆየውን ልምድ አዛባ።




በዚህ ምክንያት የዋግና ላስታ ተወላጅነት ሳይኖራቸው በንጉሠ ነገሥቱ በተሾሙ ዋግ ሹሞች መተዳደር ጀመረ። እነዚህም ዋግ ሹሞች የትግሬው ገብሩ፣ የየጁ ጓንጉል ዘገየ፣ የተንቤኑ ሳባጋዲስ፣ የሸዋው አባተ ቧ ያለው፣ የወሎው ገብረ ሕይወት ሚካኤል ነበሩ። በዚህ የተነሳ አገዎች ሹሙቱ ከዘራችን ወጣ ብለው ስለ አንገራገሩ ተመልሶ ለተወላጆቹ መሰጠት ተጀመረ። ስለሆነም የዋግሹም ወሰን የልጅ ልጆች በሹሙቱ ተተክተው የመጨረሻው ዋግ ሹም ጌታነህ አድማሱ ድረስ ቆይቶ በ1966 ዓ.ም. አቆመ።

የንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ እህት ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድህን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባለቤትና የራስ ኃይሉ እናት መሆናቸው ነው።



ዘንድሟቸው ደጃች ኃይሉ ገብረ መድህን ደግሞ የራስ ካሣ አባት ናቸው።



ደጃዝማች ከበደ ተፈሪ

## የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች


ኢትዮጵያ ውስጥ ከክርስትና ሃይማኖት አስቀድሞ የአይሁድን ሃይማኖት የተቀበሉ ጎሣዎች በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚኖሩ ይታወቃል። አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ጽላቱን ይዘው ከእሥራኤል የመጡ ናቸው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ጽላቱን ይዘው በግብጽ በኩል የጥቁር ዓባይን ወንዝ ተከትለው አገር ውስጥ የገቡ እሥራኤላዊያን ናቸው ይሏቸዋል። ሌሎች ደግሞ ከየመን ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አይሁዶች ጥንት ገና ታልሙድ ከመጻፉ በፊት በሃይማኖቱ የሰበኳቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው ይላሉ። ምንም ይሁን

ምን ሰዎቹ ከዘመን ብዛት ከነዋሪው ሕዝብ ጋር በመጋባት ተደባልቀው ጠይም ኢትዮጵያዊ ኾነው ነው የተገኙት። ነገር ግን ዕምነታቸው የአይሁድ ሃይማኖት ስለኾነ ብቻ ራሳቸውን ሁል ጊዜ እንደ እሥራኤላውያን ይቆጥራሉ።

በዮዲት ዘመን የዮዲትን መንግሥት በማገዛቸውና ክርስቲያኑን በማጉላላት ተግባር ላይ ተሠማርተው ስለነበረ መንግሥቱ በክርስቲያን ንጉሥ ሲተካ ተመልሰው የተጉላሉት እነሱ ሆኑ። አርሰው እንኳን እንዳይበሉ ከመሬታቸው ስለተነቀሉ የተፋለሰ ኑሮ በመጀመራቸው ፈላሻ ተባሉ። ጦርነትና እልቂት ስለበዛባቸው አንዳንዶቹ ሃይማኖታቸውን እየለወጡና ከሌላው ጎሣ ጋር እየተደባለቁ ሲኖሩ ሌሎቹ ደግሞ በመከላከል መቀጠሉን መርጠው ከጊዜ ብዛት በቡድን ተከፋፍለው መላ ኢትዮጵያ ውስጥ ተበትነው በተለያዩ የጎሣ ስም መታወቅ ጀመሩ። ቅማንት አንደኛው የሚታወቁበት ስም ነው። በፊት በሚኖሩበት አካባቢ የቀሩት በፈላሻነት ሲታወቁ ኑሯቸውን የሚገፉት በተናቀው የእጅ ሙያ ሥራ ነው። እሥራኤላውያኖች ነንና ወደ አገራችን እንመለስ በማለትና የእሥራኤልም መንግሥት ስለተቀበላቸው በአሁኑ ዘመን በብዛት መሄድ ጀምረዋል። እዚያም ከሄዱ በኋላ የዘር ሙቅናው አልቀረላቸውም። ያገኙት ጥቅም ቢኖር ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በኤኮኖሚ ኋላ ቀር ስለኾነች በተሻለ የኑሮ ደረጃ ለመኖር ችለዋል። የሚገርመው ግን አካባቢውን ሸሽተውት የመጡበት የፍልስጥኤም ምድር የሦስት ሺህ ዓመት የዘር ጥላቻ የተጠናወተው የእልቂት ቦታነቱ ስላልተሻሻለ ተመልሰው የችግሩ ተቋዳሽ መሆን መጀመራቸው ነው።



# ትግሬ



የቀድሞ ነገሥታት ዘውዶች በአክሱም

የንግሥተ ሳባ መሠረት ትግራይ (የሃማሴንን ግዛትም ጨምሮ) ዋና ከተማው አክሱም ነበር። በዚህም ምክንያት አክሱም ቀደም ብሎ የንግሥና ሥርዓት ይካሄድባት የነበረች ከተማ ነች። ንጉሦች አክሱም ሄደው መንገሥ ባይሳካላቸውም ቢያንስ ዘውዳቸውን ይልካሉ። ለምሳሌ አፄ ኃይለ ሥላሴ አንዱን ዘውዳቸውን ቀደም ብለው አክሱም ልከውት ስለነበረ አሁንም እዚያው ይገኛል።

የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት በዮዲት አማካይነት በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሲደመሰስ መንገሥ ያለበት ከአክሱም ተሰዶ ሸዋ ገብቶ ሲደበቅ ሌሎቹን ተወላጆች ዮዲት ደብረ ዳሞ ላይ ከተጋዙበት ይዛ ስለፈጀቻቸው ደብዛቸው ጠፍቷል። በዚህ ምክንያት ትግራይ የሃማሴን ግዛትን ጨምሮ የሚተዳደሩት በአካባቢ ሹሞች ሲሆን ትውልዳቸውን ከቀዳማዊ ምኒልክ በመቁጠር አልነበረም።

የአገሩ ስም ትግራይ ሲሆን በዚሁ የሚኖረው ጎሣ ትግሬ ይባላል። ትግሬ ማለት ነጋዴ ማለት ነው። የትግራይ መኳንንቶችም የንጉሠ ነገሥታቱም ሹማምንት እየሆኑ በማዕከላዊው መንግሥት እየተሾሙ ስም ያተረፉና በጋብቻም እየተዛመዱ ትላልቅ ባለሥልጣናትም ኾነው ነበር። ከትግራይ ሹሞች መካከል ወላይታ ሄደው የካዎን ሥርወ መንግሥት

እስከ መሙርስ ደርሰዋል። በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በእንደራሴነት የሚታወቁት የትግራይ ባላባት ሥሑል ሚካኤል በንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴነት ጎንደር ላይ ሲያገለግሉ ኖረው በተከፉ ጊዜ የእቴጌ ምንትዋብን የልጅ ልጅ ንጉሥ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቀው አስገደሉ። ሥሑል ሚካኤል ዝነኛ ስለነበሩ ከእሳቸው ሕ ኅወት በኋላ ተወላጆቻቸው በትግራይ ሹም በመሆን አገር ሲያስተዳድሩ ኖረዋል። ዳሩ ግን ከትግራይ ባላባቶች ውስጥ ከዚህ በተረፈ መንግሥ አለብኝ፣ የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጅነቴን እቆጥራለሁ የሚል አልተገኘም።

የዘመነ መሳፍንትን ሥርዓት የደመሰሱት አፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ከነገሡት የላስታው ዋግሹም ጎበዜ (አፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ሥልጣኑን በመቀማት ደጃዝማች ካሣ ምርጫ (አፄ ዮሐንስ) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኾነው አስተዳድረዋል። አፄ ዮሐንስ የአፋሯን ተወላጅ ወይዘሪት ዳቶን ክርስትና አስነስተውና ጥበበ ሥላሴ አሰኝተው አገቡና ራስ አርአያ ሥላሴን ወለዱ። ራስ አርአያ ሥላሴ ገና የ18 ዓመት ልጅ እንዳለ ሞተ። አጼ ዮሐንስ በእናታቸው በኩል የአጎታቸውን የትልቁ ራስ ጉግሣን ልጅ ራስ መንገሻን ወስደው እንደልጃቸው ያሳድጉት ስለነበረ የሚጠራውም በወላጅ አባቱ ስም ሳይሆን በአሳዳጊው በአፄ ዮሐንስ ነበር። አፄ ዮሐንስ ራስ መንገሻ ዮሐንስ መንግሥታቸውን እንዲወርሱ ቢናዘዙላቸውም አልነገሡም። ራስ መንገሻም በተራቸው ራስ ሥዩምን፣ ልዕልት ወለተ እሥራኤልን፣ ወይዘሮ አስቴርንና ወይዘሮ አልማዝን ወለዱ። የአጼ ዮሐንስ ልጅ ራስ አርአያ ሥላሴ ከወይዘሮ ዘውዲቱ ልጅ አልወለደም። ሆኖም በልጅነት ዕድሜው ከመሞቱ አስቀድሞ በምስጢር ከአንድ ወሎዬ ሴትና ከአንድ ሌላ ሴት የወለዳቸው ልጆች ነበሩት። ራስ ጉግሣ በምስጢር ከራስ አርአያ ሥላሴና ከወሎዬዋ ሴት የተወለዱ ልጅ ናቸው። ራስ ጉግሣ የደጃች ኃይለ ሥላሴ አባት መሆናቸው ነው። ራስ አርአያ ሥላሴ በምስጢር ሌላም ልጅ ነበራቸው። እሱም ተሰደ ወደሸዋ የመጣው ደስታ ሲሆን የእሱ ልጅም በሕይወት ያለው ታዋቂው ጋዜጠኛ አቶ ጌታቸው ደስታ ነው።





አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ከራስ አርአያ ሥላሴ ጋር

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ከባለቤታቸው ከልዕልት ዘነበ ወርቅ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ልዕልቲቱ በወሊድ ምክንያት ሞቱ። ሆኖም ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ባለቤታቸው ነፍሰጡር ሆነው ይደበድቡዋቸው ስለነበር የሞቱትም በዚሁ ጠንቅ ነው መባሉ በወላጆቻቸው ስለተሰማ የውስጥ ቅራኔ ተፈጠረ። በዚህም ምክንያት የሚችትን የወግ ዕቃ መልስ ተብለው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ መልሰዋል። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ቅምጥል የነበሩና ወደ አዲስ አበባ እንኳን የሚመጡት በኤርትራ በኩል በመርከብ ወደ ጅቡቲ ተሻግረው በባቡር እንጂ እንደ ሌሎቹ መኳንንቶች በበቅሎ ወይም በፈረስ አልነበረም።


የትግራይ ክፍለ አገር ምዕራቡ በራስ ሥዩም ምሥራቁ በደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ይተዳደር ነበር። ይሁንና ደጃች ኃይለ ሥላሴ ያስተዳድሩት የነበረው በፊት አባታቸው ራስ ጉግሣ ከሚያስተዳድሩት ተቀንሶ ስለነበረ ቅሬታ ነበራቸው። በመሃሉ ጣሊያን ኢትዮጵያን ሊወር ሲመጣ ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ መላው ትግራይ ላይ ጣሊያኖች ይሾሙኛል ብለው ከጠላት ጎን ተሰለፉ። በዚህም የተነሳ በማይጨው ጦርነት ብዙ ጉዳት ኢትዮጵያ ላይ እንዲደርስ ምክንያት ሆኑ። ወረራው ሲያበቃ በእንግሊዞች አግባቢነት ከታሰሩበት ከሲሼልስ ደሴት ምሕረት ጠይቀው ከተመለሱና ከብዙ ዓመት ግዞት በኋላ በደርግ ዘመነ መንግሥት ተለቀው ነበር።

የራስ ሥዩም ልጆች ተወላጅነታቸው ከአፄ ዮሐንስ አጎት ከትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ከራስ መንገሻ ነው። አፄ ዮሐንስ የነገሡት ደግሞ በጉልበት እንጂ በተወላጅነት ባይሆንም የሹም አጋሜ ምርጫ ልጅ መሆናቸው የታወቀ ነው። ከነገሡ በኋላ ግን ብዙ ጸሐፊዎች ዘር ቆጥረው ከአፄ ፋሲል ይወለዳሉ ይላሉ። የአባታቸው ወላጅ እናት ግን ወይዘሮ ውርቅውሃ ሲሆኑ እላቸውም የራስ ሥሑል ሚካኤል የልጅ ልጅ የቃለ ክርስቶስ ሴት ልጅ ናቸው። የአፄ ዮሐንስ እናት ወይዘሮ ሥላስ የሹም አጋሜ ወልዱ ሲት ልጅ የወይዘሮ ታቦቷ ልጅ ናቸው። ሹም አጋሜ ወልዱ የኢሮብ ተወላጅ ሲሆኑ የታወቁ ባላባትና ከሃምሳ ልጅ በላይ የነበራቸው ሰው ነበሩ። አጥብቆ ከተቆጠረ እንደማንኛውም የሰሜን ኢትዮጵያዊ ሰው ሁሉ በሴትም በኩል ቢሆን ከንጉሥ ውልደት ይጠፋል ብሎ ለመደምደም ግን ያስቸግራል።


ራስ መንገሻ ዮሐንስ

ከትግራይ ባላባቶች መካከል ጥንት ከዛጔ ሥርወ መንግሥት በፊት መንግሥቱ የእኛ ስለነበረ ለእኛ መመለስ አለበት የሚል አስተሳሰብ በብዙ ሰዎች ዘንድ አለ። በተለይ አፄ ዮሐንስ ከዘጠኝ መቶ ስልሳ ዓመት በኋላ ደህና የመለሱትን ንግሥና በቀላሉ እንደገና ወደ ሸዋ ስለዞረ ደስተኛ ያልሆኑ በርካታ ሰዎች ነበሩ። በመኾኑም አንዳንዶቹ ኢጋጣሚ ባገኙ ቁጥር የማዕከላዊውን መንግሥት ለመጣልና በእሱ ላይ ለመሸፈት ጥረዋል። ለምሳሌ የመጀመሪያው ወይን ጠርነት በባላባቶች የሹመት ቅራታ የተነሳ ቢሆንም መንግሥቱን የመውሰድ ስሜት ያላቸው በመካከላቸው እንደነበሩ አያጠራጥርም። ይህ ስሜት ባይኖር ኖሮ የትግራይ ልጆች ብዙዎቹ ሕብረ ብሔራዊ ከሆኑ ፓርቲዎች እየተለዩ በቀላሉ ወደ ጎጣ ፓርቲ ውስጥ አይደባለቁም ነበር።






## አማራ

አማራ የሚባለው ጎሣ ስያሜው እንዴት እንደመጣና ትርጉሙም ምን እንደኾነ ብዙ ሊቃውንቶች ይቸገሩበታል። አንዳንዶቹ ለስሙ ትርጉም በመስጠት የልብ ወለድ ታሪክ ለመናገር ይሞክራሉ። አምሐራ ምሕረት የጠየቀ እንደማለትም ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ በጥንት ዘመን ዓባይ ወንዝ ዳር ይመለክበት ከነበረ የጣዖት ስም የተገኘ ቃል ነው ይላሉ። ትግሬዎች አማሮችን ወደ ደቡብ የሄዱ ትግሬዎች ናቸው እስከ ማለትም ደርሰዋል። ሌሎች ደግሞ ሰሃራ ውሃ የሌለበት በረሃ ሲሆን አምሓራ ውኃ ያለበት ለምለም ቦታ ማለት ነው ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የአገሩን ታሪክ የሚመረምሩ የአማራ ጎሣ ምንጩ፣ አገው ነው ይላሉ። በወሎ አማራ ሳይንት የሚባል የአገር ስም እንዳለ ይታወቃል። እንዲያውም ከግራኝ አሕመድ ወረራት አስቀድሞ

አሁን ወሎ የሚባለው ግዛት አማራ ይባል ነበር። ሕዝቡም ሃይማኖቱ ክርስቲያን ስለ ነበረ ሃይማኖቱን ሳይለውጥ የቀረውን ሁሉ አማራ ማለት ተጀመረ። ይህ አማራ ተብሎ የሚታወቀው ጎሣ ራሱን አማራ እያለ ሲጠራ ሌሎች አምሓራ ለምን እንደሚሉት አይታወቅም። በተጨማሪም አማራን የጎሣ ስም አይደለም የሚሉት ከሌሎች ጎሣዎች መሥፈርት የአማራ በምን ተለይቶ እንደሆነ አልገለጹም። ይሁንና አማራ በሚል ስያሜ የሚታወቅ አንድ ግዙፍ ጎሣ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እንደሚገኝ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ብቻ ተወስኖ የሚገኝ መሆኑ ለፍጹም ኢትዮጵያዊነት ሥነ ልቡናው አስተዋጽኦ አድርጎለታል።

ይሁንና አማርኛ ቋንቋ ከዮዲት ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የሕዝብ መገናኛ ቋንቋ እንደነበረ ይታወቃል። ምንም እንኳን ግዕዝ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑ አማርኛ ተጨቁኖ ቢቆይም ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ በይፋ የጽሑፍ ቋንቋ ለመሆን በቅቷል። በሸዋ፣ በወሎ፣ በጎንደር፣ በጐጃም፣ ያለው ሕዝብ በብዛት አማራ ይባላል። ከኦሮሞ መስፋፋት በፊት ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ሊሙ፣ ሸዋ ውስጥና ወደ ሐረርጌ በሚወስደው ደጋ አገር ላይ ያለው ሕዝብ በብዛት አማራ እንደነበረ ይነገራል። በተለይ በሸዋ ሜዳ ሜዳው ላይ ነዋሪ የነበረው አማራ ሸሽቶ በየሸንተረሩ በመደበቅ ዘሩን ማትረፉን መልክአ ምድሩን በመመልከት ለመረዳት ይቻላል። ገደላ ገደሉ አማራ ሜዳ ሜዳው የኦሮሞ አገር የኾነው ኦሮሞው በፈረስ ኾኖ በጦር እየወጋ አማራውን አባሮት ነው ተብሎም ይነገራል። ከጊዜ ብዛት አማራውም ኃይል ሲያገኝ ተመልሶ ከገደላ ገደሉ ወጥቶ በጦር ድል አድርጎ በመውጣቱ በአሁኑ ወቅት በጋብቻ ጭምር ተሳሥሮ ከኦሮሞ ጋር የኦሮሞ አገር በተባለው ሁሉ በብዛት አብሮ በመኖር ላይ ይገኛል። የአማራ ጎሣ ለጋብቻ ጎሣ የመለየት ጠባይ ስለሌለው በተለይ ከኦሮሞ ጎሣ ጋር በብዛት በጋብቻ ተሳሥሯል።

የሸዋ፣ የወሎ፣ የጎንደርና የጐጃም አስተዳደር ብዙውን ጊዜ በማዕከላዊው መንግሥት ሥር ሆኖ በየክፍለ ግዛቱ የተለያዩ ባላባቶች አሏቸው። ከፊታውራሪና ደጃዝማች እስከ ራስና ንጉሥ ድረስ እንደ ጀብዷቸውና ውልደታቸው የማዕከላዊው ንጉሠ ነገሥት የተለያየ ማዕረግ ይሰጣቸዋል። በተረፈ የማዕከላዊው መንግሥት ባለሥልጣኖች እየሆኑ በሹመት በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ይዘዋወራሉ።



በጎንደር ቤተ መንግሥት በቋረኞችና በየጁ መኳንንቶች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በደከመበትና እንደራሴው ሥልጣኑን ካዘዘበት ጊዜ ጀምሮ እንደራሴነቱን ይዘው የቆዩት ውልደታቸው ከአማራም ከኦሮሞም የነበረው የየጁ ባላባቶች ነበሩ። ከሌሎቹ ፊንጠር ብሎ ጐጃምና ዳሞት የተለዩ ጠንካራ ባላባቶች ነበሯቸው። የጎንደሩ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በእንደራሴዎች ሥር በወደቀበት ወቅት በሸዋ ያለው የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች ኃይለኛ ባላባቶች ኾነው ስለነበረ የጎንደሩን መንግሥት ለመተካት ዕቅድ ነበራቸው። በተለይ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዝግጅት ጀምረው በድንገት ስለሞቱ ልጃቸው ኃይለ መለኮት በሸዋ ንጉሥነት ቆዩ።

## ጐጃም


ጐጃም ምንም የአማራ አንዱ ትልቅ ክፍል ቢሆንም የራሱ የሆኑ ተከታታይ ባላባቶች ነበሩት። ሆኖም ባላባቶቹ በጋብቻም በመተባበርም አንድ ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜ እርስ በርስ ጐጃምና ዳሞት ብለው እየተለያዩ በመዋጋት ግዛቱን ሲያስተዳድሩ ኖረዋል።

ቋረኛዋና ጥሩይቱ እቴጌ ምንትዋብ የአፄ በካፋ ባለቤት በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያን ለሠላሳ ዓመት አስተዳድረዋል። አፄ በካፋ በወጣትነታቸው ስለሞቱ ከሁለቱ የተወለደው ቀባዩ ዳግማዊ ኢያሱ ዓለም ሰገድ ነግሦ እቴጌ ምንትዋብ በሞግዚትነት መንግሥቱን ያስተዳድሩ ነበር። እቴጌ ምንትዋብ ወጣት ስለነበሩ ከምልምል ኢያሱ ሦስት የሚያማምሩ ሴቶች ልጆች ወለዱ። ኢያሱ ምልምል የተባሉበት ምክንያት የአፄ ኢያሱ ዓለም ሰገድ አባት የአፄ በካፋ እህት ልጅ ስለነበሩና ግንኙነቱም ድብቅ ስለነበረ ነው።

የእቴጌ ምንትዋብ ሦስቱ ውብ ሴት ልጆች አልጣሽ፣ አስቴርና ወለተ እሥራኤል (ዳግሚት) ናቸው። የተዳሩትም:-

| | |
|---|---|
| አልጣሽ | ለስሜኑ ባላባት |
| አስቴር | ለአዝማች ነሙ ቀጥሎ ለትግሬ |
| | ባላባት ለራስ ማርያም ባሪያው |
| | በመጨረሻም ለራስ ሥሑል ሚካኤል |
| ወለተ እሥራኤል | ለጎጃሙ ባላባት ለደጃች ዮሴዴቅ ነው። |

## የጐጃሙ ባላባት የደጃች ዮሴዴቅ ትውልድ




አፄ ኢያሱ ዓለም ሰገድ በሦስቱ እህቶቹ መወለድ ያፍር ስለነበረ ምልምል ኢያሱን አድብቶ ወደ ገደል አስገፍቶ አስገደለ። የሚች



እህትም አዘናግታ አፄ ኢያሱን በመርዝ በመግደል የወንድሟን ሞት ተበቀለች። ስለኸነም መንግሡቱን የአፄ ኢያሱ ዓለም ሰገድ ልጅ አፄ ኢዮአስ ወርሶ እቴጌ ምንትዋብ አሁንም በሞግዚትነት ማስተዳደር ቀጠሉ። የአፄ ኢዩአስ እናት የየጁ ባላባት ልጅ ስትሆን በትውልዷ ኦሮሞ ነበረች። ንጉሥ ኢዮአስ ወደ እናቱ ዘመዶች በማድላቱ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በቋረኞችና በየጁ ኦሮሞዎች አለመግባባት ስለተነሳ መንግሥቱ እየደከመ ሄዶ መጨረሻ ላይ እንደራሴው የትግራዩ ተወላጅ ራስ ሥሑል ሚካኤል አስገድሎት ሥልጣኑን ወሰደበት። የተለያዩ ጎሣዎች በጋብቻ የበለጠ ይቀራረባሉ ተብሎ ሲጠበቅ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ጋብቻ የጎሣ አለመግባባትን ሲፈጥር ይታያል።

ራስ መርዕድ የእህታቸውን ባል ደጃች ዘውዴን አስረው ጐጃምና ዳሞትን ሲያስተዳድሩ ኖረው ሲሞቱ ልጃቸው ደጃች ጓሉ ጐጃምን፣ የእህታቸው ልጅ ደጃች ጎሹ ዳሞትን ያስተዳድሩ ነበር። ደጃች ጓሉ ከሞቱ በኋላ ግን ደጃች ጎሹ ጐጃምን ከይመር ጓሉ ቀምተው ወደ ራሳቸው ግዛት ደረቡት:: አፄ ቴዎድሮስ የጐጃምን ገዥ ደጃች ጎሹን በ1845 ዓ.ም. ገድለው ልጃቸውን ብሩን ከማረኩና ከነገሡ ወዲህ ደጃች ተድላ ጓሉን በጐጃም ሾሙዋቸው::

በኋላ ግን ደጃች ተድላ ስለከዱዋቸው አፄ ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ ቢያሳድዱዋቸውም ለማግኘት አቃታቸው:: የሆኖ ሆኖ በጥር ወር በ1860 ዓ. ም. ደጃች ተድላ ሞተው በተክሉት የውሽ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስከሬናቸው አረፈ:: እሳቸውም ከሞቱ ከአራት ወር በኋላ በሚያዝያ ወር አፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ ራሳቸውን አጠፉ:: ደጃች ተድላ በጐጃም በጣም ተወዳጅ ስለነበሩ ብዙ ግጥም ተገጥሞላቸዋል ካህናት እንኳን የሚከተለውን እስካሁን ይዘምሩላቸዋል

ዘመኔ ዘመኔ ተድላ ዘመኔ
እሱ ተወልዶ ወልዶ ለኔ
እሱ ተወልዶ ወልዶ ለኔ ተድላ ዘመኔ

ራስ ዓዳል ተሰማ በልጅነታቸው ደጃች ተድላ ጓሉ ቤት ያድጉ በነበረበት ጊዜ ደጃች ተድላ አምነዋቸው ባለሟል አድርገዋቸው እያለ ከዕቁባታቸው ከወይዘሮ ጉዳዬ ልጅ ስለወለዱ ሸሽተው በርሃ ይኖሩ ነበር። ከአፄ ቴዎድሮስ ቀጥሎ ነግሠው የነበሩት የስሜኑ ዋግሹም ጎበዜ (አፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ጐጃምን ለማስገበር ዘምተው ለባላንባራስ ዓዳል እህታቸውን ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅንን ድረውላቸውና የራስነት ማዕረግ ሰጥተው ጐጃም ላይ ሾመዋቸው ተመለሱ።



ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው መንግሥታቸውን ስለ ወሰዱባቸው ራስ ዓዳል አልተደሰቱም ነበርና አልገብርም ስላሉ አፄ ዮሐንስ ለማስገበር ጎጃም ሲመጡ ራስ ዓዳል ሸሽተው በርሃ ገቡ። አፄ ዮሐንስ ለራስ ደስታ ተድላ ዘመዳቸውን ድረውላቸው ጐጃም ላይ አገረ ገዥ አድርገው ሾሙዋቸው። በተጨማሪም ሐጎስ የሚባል አስተዳዳሪ በሥራቸው ሾመው ተመለሱ። ራስ ደስታ ምንም ለአፄ ዮሐንስ ቢጋብቻ ቢዛመዱም የጐጃም ሰው ግብር በዝቶበታልና እኔ አልገብርም እያሉ ሲሉ ራስ አዳል ከበርሃ ተመልሰው ይወጓቸውና በጦርነቱ ራስ ደስታም ሐጎስም ይገደላሉጮጮ የራስ ደስታንና የሐጎስን አስከሬን ወደ መቃብር ሲወስዱ የራስ ደስታን በእንጨት አልጋ የሐጎስን በአጎበር በተከለለ አልጋ ሲወስዱ የጐጃም ሕዝብ ተመልክቶ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ገጠመ።

እኔስ ምንቸገረኝ ካንተም አልዋጋ
እሥራኤሉን ዘንጨት ወታደሩን ባልጋ



## የተድላ ጓሉ ትውልድ

ተድላ ጓሉ

- ራስ ደስታ
- ደጃች ንጉሤ
- ወይዘሮ ብዙነሽ
- ወይዘሮ ጥሩነሽ
- ባህታዊ ደስታ
- ልጅ አበሻ
- ወይዘሮ ጎብሪቱ
- ደጃዝማች እምሩ
- ፊታውራሪ መርዕድ
- ደጃዝማች ዓለማየሁ
- ፊታውራሪ ሣህለ
- ልጅ ዓለማየሁ
- ወ/ሮ ቀጠሮ

## የደጃች ተሰማ ጎሹ ትውልድ

- ደጃች ተሰማ ጎሹ
  - ራስ ዓዳል
    በኋላ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት
    - ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት
      - አቶ ተሰማ
      - ፊታውራሪ አድማሱ
      - ወይዘሮ ሰብለ ወንጌል
      - ወይዘሮ ሙሉነሽ
      - ወይዘሮ ድንቅነሽ
      - ወይዘሮ ኢትዮጵያ
      - አቶ ከበደ
      - አቶ ስለሺ
      - አቶ አረጋ



አፄ ዮሐንስ ምንም በድርጊቱ ቢቆጡም ከግዛጾች ጋር ጦርነት ማድረግ ስለነበረባቸው ሳይዘምቱባቸው ቀሩ። ከቀን በኋላ ግን ራስ ዓዳል ታዛዥ ስለ ሆኑላቸው እስከ ገበሩ ድረስ ጎጃምን ይዘው እንዲቆዩ ተስማሙ። በኋላም በሸዋና በጎጃም ያሉት መሳፍንት በላያቸው ላይ እንዳይነሱባቸው የሁለቱ ኃይል ተመዛዝኖ የእሳቸው የበላይነት ክብር እንዲያገኝ ስለፈለጉ አፄ ዮሐንስ የሸዋውን ንጉሥ ምኒልክን ንጉሥነት በ1870 ዓ.ም. አጽድቀው ራስ ዓዳልንም ስማቸውን ተክለ ሃይማኖት አሰኝተው በ1873 ዓ.ም. በጥር ወር የንጉሥነት ማዕረግ ሰጧቸው።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ራስ ኃይሉ አቤቶ ኢያሱ ስላሴ ከታሰረበት እንዲያመልጥ በማሤራቸው ጎጃምን ተሸረው ሌሎች አገረ ገዥዎች እየተሾሙበት ቀጥታ በማዕከላዊ መንግሥት ሥር ይተዳደር ጀመር።

## ወላይታ

ጋቶሎሚ የተባለ የወላይታ የሁለተኛው ማላ ሥርወ መንግሥት 11ኛ ንጉሥ ኃይለኛ ስለነበረ ቡልጋ ላይ ዘምቶ በምርኮ ብዙ ሰዎች ይዞ ሲሄድ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን እናት እግዚእሃርያን ይዞ ሄደ። በወላይቶች ዕምነት እግዚእሃርያ ከጋቶሎሜ ጸንሰው ከምርኮ መልስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቡልጋ ላይ ይወልዳሉ ብለው ይተርካሉ። እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል ደግሞ መማረካቸው እርግጥ ሲሆን እግዚእሃርያን ካዎ ጋቶሎሚ ለማግባት አስሞሽሮ ካስቀመጠበት ከጣኦት ቤት ቅዱስ ሚካኤል አውጥቷቸው ወደ ቡልጋ ከተመለሱ በኋላ ከባለቤታቸው ከካህኑ ከጸጋ ዘአብ መጸነሳቸውን ይገልጻል።

ካዎ ማለት በወላይትኛ ንጉሥ ማለት ሲሆን ቡሻሻ ማለት ደግሞ አልጋ ወራሽ ማለት ነው። ወጋ ማለት ደግሞ ትልቅ ወይም ኃይለኛ ማለት ነው። እንዲሁም ጦሶ ማለት እግዚአብሔር ማለት ነው።



ካዎ ጦና

ካዎ ጉቶሎሚ

ካዎ ታላሜ

ካዎ ሞስካ

ካዎ ሞታ

ካዎ ኦቼ

ካዎ ላቼ



የካዎ ላቼ መንግሥት ስለደከመ ከተንቤን ለመጣ ጦረኛ ለሹም አጋሜ በጋብቻ ከተሳሰሩ በኋላ መንግሥቱን በ1553 ዓ.ም. ለቀቀለት።

ካዎ ሹም አጋሜ (ሹማግብ)

ካዎ ሚካኤል

ካዎ ግርማ

ካዎ አዳዮ

ካዎ ኮቴ

ካዎ ኮቴ የትንቢት ንጉሥ ይባል ስለነበረ ከእኔ 10ኛው ትውልድ መንግሥት ከዘሬ ይወጣል ብሎ ተነበየ።


ካዎ ኮቴ

ካዎ ሊበን


ካዎ ቱቤ

ካዎ ሳና

ካዎ ሳና ጦረኛ ንጉሥ ስለነበረ የወላይታን ሰባት ወረዳዎች ያስገበረና የሃዲያን መንግሥት ወግቶ ያዳከመ ነበር። በዚያን ጊዜ የሃድያ መንግሥት አሁን አርሲ የሚባለው አገር ነበረ። ሕዝቡ በአሁኑ ዘመን አብዛኛው አርሲ ኦሮሞ ሆኖ የሚታየው ወላይታ ያዳከመውን የሃድያን ሕዝብ ኦሮሞ ወግቶና አባሮ ስለተካው ነው።





ካዎ ዳሞቴ በጦረኝነት የሚታወቅ ንጉሥ ሲሆን ተከታዩ ካዎ ኀቤ ግን ብልህና አስተዋይ ንጉሥ ከመሆኑም በላይ የአባ ጅፋር አማችም ነበር።






ቡሻሻ ጋጋ አባታቸው ላይ መፈንቅለ መንግሥት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረና አባትየውም በነገሩ ስለተናደዱ ረገሚቸውና በሳምንቱ በልብ ህመም ሳቢያ ሞቱ።




ፊታውራሪ ደስታ ፍስሐ

ከዚያም ካዎ ጦና ነግሠው ገና አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው በ1887 ዓ.ም በምኒልክ ስለተሸነፉ የመጨረሻው የወላይታ ንጉሥ ሆኑ። አፄ ምኒልክ ጦና ጀግና በመሆናቸው ስላከበሯቸው የክርስትና አባት ኾነው መልሰው የወላይታ አገረ ገዥ አድርገው ሾሚቸው። እሳቸውም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አዲስ አበባ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን አስከሬናቸው አርፎ በአሁኑ ወቅት መቃብራቸው በቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ በስተቀኝ በኩል ይገኛል።

ሕዝቡ የካዎ ጦናን ልጅ ቡሻሻ ሮቤ ወይም ፍስሐን ጦና ብሎ ይጥራቸው እንጂ አልነገሡም። የሳቸውም ልጅ ፊታውራሪ ደስታ ፍስሐ ናቸው። ፊታውራሪ ደስታ የሸዋ መኳንንት የአዛዥ ሽብሩን ልጅ ወይዘሮ አልታሽ ሽብሩን አግብተው አምስት ልጆች ወልደዋል።

ፊታውራሪ ደስታ ወይዘሪት እመቤት ደስታን ለሪር አድሚራል እስክንድር ደስታ በጋብቻ እንዲሰጡ ሽማግሌ ቢላክባቸው አልሰጥም ስላሉ ወጣቶቹ ሳይጋቡ ቀሩ። በኋላ ላይ ነገሮች ተለዋወጡና እመቤት ደስታ ነጭ አገባች። ፊታውራሪ ደስታ ፍሰሐን ሰዉ ደስታ ጦና በሚል ስም ይጠሯቸው ነበር። አሜሪካን አገር ሄደው ስለሞቱ አስከሬናቸው እዚያው ቨርጂንያና ዋሽንግተን ዲሲ መካከል በሚገኘው ግሬት ፓቶማክ ወንዝ አጠገብ ከቀድሞ ፕሬዜዴንት ዊድሮው ዊልሰን መቃብር ቁጥር 2176 አጠገብ አርፏል። ቁጥር 2146 መቃብራቸውም ላይ **SON OF WOLAITA'S KING** የሚል ጽሑፍ ተደርጎበታል።




## ከፋ

ከፋ ከወላይታ ቀጥሎ በአፄ ምኒልክ ጦር ላይ ኃይለኛ መከላከል ያደረገ ትልቅ የንጉሥ አገር ነበር። ንጉሡ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ከከባድ መከላከል በኋላ ተይዘውና ታስረው በምትኩ የማዕከላዊው መንግሥት ሹም በአገራቸው ተሾመበት።

መለኮታዊ ንጉሥ እንደነበረ የሚነገርለት ታቶ ጋኪ ሼሮቾ የከፋ ሥርወ መንግሥት 19ኛው ትውልድና የመጨረሻው ንጉሥ ሲሆኑ ሄኮ የሚባለው አምላክ በእሳቸው አድሮ የሚናገር መኾኑ ይታመን ነበር። የንጉሥ ሰሎሞንና የንግሥት ሳባም ዘር ናቸው ይባላል።

ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ለመዋጋት በሚሰናዱበት ጊዜ እንግሊዞች ዩጋንዳ ኾነው መሣሪያ እንላክልህ ቢሏቸው "አሁን የማካሂደው ጦርነት የወንድማማች ጦርነት ስለኾነ ዕርዳታ አያስፈልገኝም። እኔ ምኒልክን ካሸነፍኩት አገሩን በሙሉ አስተዳድራለሁ። እሱ ካሸነፈኝ



አገሩን በሙሉ ይግዛ። እርዳታ የምጠይቃቸሁ የውጭ ጠላት ሲመጣብኝ ብቻ ነው" ብለው መልሰዋል።


ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ

ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ በጣም ኩሩ ከመሆናቸው የተነሳ በጦርነት ተሸንፈው እጃቸው ሲያዝ በእግር ብረት ሊያስሯቸው ሲሉ "እኔን ያህል ንጉሥ በብረት እግረሙቅ ሳይሆን ከብር በተሠራ ነው የምታስረው" ብለው ራሳቸው ባቀረቡት የብር እግረሙቅ ታሰሩ።

ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ተይዘው ሲመጡ ጎጀብ ወንዝን ሲያቋርጡ ቀለበታቸውን አውልቀው ወንዙ ውስጥ ጥለው "የከፋ መንግሥት ከእንግዲህ አበቃ። ከእንግዲህ ወዲህ ሌላ ንጉሥ አይኖርም። የንጉሡ ቀለበትም በወንዙ ውስጥ ታርፋለች" ብለው ተናገሩ።

አፄ ምኒልክ ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾን እንደ አረመኔ አድርገው ስላዩዋቸው ምሕረት አድርገው መልሰው አገራቸው ላይ ሊሾሙዋቸው አልፈለጉም። ስለሆነም ወሎ ራስ ሚካኤል ዘንድ በእስር ተቀምጠው አቤቶ ኢያሱ በዘመኑ ስለፈታቸው አዲስ አበባ መጥተው ሲኖሩ በ1911 ዓ.ም ሞቱ።

## ጉራጌ

ከጊቤ እስከ አዋሽ መካከል ባለው አገር ይኖሩ ከነበሩ ሰዎች ጋር በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን ከባሕር ነጋሽ አዲ ኳላ አውራጃ ደቀ መሃሪ ወረዳ ጉራዓ ከሚባል ቦታ የመጡ ወታደሮች ተደባልቀዋቸው ጉራጌ በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ጎሣ ኾኑ ይባላል። በእርግጥ የወታደሮቹ ብዛት ይኼን ያህል በነበረው ኅብረተ ሰብ ላይ ለውጥ

አምጥቷል ለማለት ያስቸግራል። ከቀድሞ ጀምሮ ጉራጌ በማዕከላዊ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ጎሣ ሲሆን በተለይ በግራኝ ወረራና በኦሮሞ መስፋፋት የተደቆሰና በሚመርጣቸው የጦር አበጋዞች አማካይነት ራሱን ተከላክሎ እንደ ደሴት ሊቆይ የቻለና ያልተደመሰሰ ብርቱ ጎሣ ነው። በዘመነ መሳፍንት ወቅት ተረስቶ ያለምንም ድጋፊ ራሱን እየጠበቀ የኖረ ጎሣ ሲሆን ከሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የጦር ዕርዳታ ቢጠይቅም ከጉብኝት በስተቀር በወቅቱ ምንም ያገኘው ዕርዳታ አልነበረም።

በመሠረቱ ጉራጌ በሦስት ይከፈላል። በምዕራብ ሰባት ቤት ጉራጌ፣ በምሥራቅ ስልጤና ወለኔ ወይም አደሬ ሲባሉ በሰሜን ያሉት በአጠቃላይ ክስታኔ በሚል ስም ይታወቃሉ። ለምሳሌ ሰባት ቤት ጉራጌ፣ የሚባሉት ኤነር፣ ቸሃ፣ እነሞር፣ እንደጋኝ፣ ጉመር፣ እዣ፣ ጌቶ ናቸው። በክስታኔነት የሚታወቁት በሁለት ተከፍለው ሶዶ ጅዳና ሶዶ ጎርደና ተብለው ይታወቃሉ። ሶዶ፣ ጉራጌና ኦሮሞ በብዛት የተደባለቁበት አካባቢ ነው። የምስራቁ የሰልጤው ክፍል በብዛት ሙስሊም ሲሆን ራሱን "ቶቦ" ብሎ ሲጠራ ክርስቲያኑን "ጠመኛ" ይለዋል። አንዳንዶች ደግሞ ክርስቲያኖቹን በጠቅላላው ጉራጌ ብለው ሙስሊሞችን በተለያዩ ስሞች ይጠሯቸዋል። ይኸውም በወሎ እስላም ነህ አማራ ተብሎ ባልተማሩ ሰዎች ይጠየቅ እንደነበረው መሆኑ ነው።

በአፄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጉራጌ ትኩረት እየተሰጠው ቢሄድም በ1870ዎቹ ላይ በከፊል ጉራጌ ለብቻ መንግሥት እንመሠርታለን በሚሉ ባላባቶች መሪነት ችግር በመፍጠሩ የአፄ ምኒልክ ደጃዝማቾች በተከታታይ ብዙ ዘመቻዎች አድርገው የተሸነፉበትና የሞቱበትም ሁኔታ ነበር። ሆኖም መጨረሻ ላይ ከብዙ ድካም በኋላ ስለተሸነፉ ሁኔታው በርዶ እንደቀድሞው በመካከለኛው መንግሥት ሥር መተዳደር ጀመሩ። ጉራጌዎች በአሁኑ ስሙ እንደ ሜጫ ያሉት ቦታዎቻችን በኦሮሞዎች ተወስዶብናል ይዳኙን ብለው ለአፄ ምኒልክ አቤቱታ ሲያቀርቡ ከወሰንተኞቻቸው ጋር የነበረውን ችግር ለማጥፋት አዲስ አበባ ውስጥ ጌጃ ሰፈርን ለመስፈሪያነት ሰጧቸው። በዙሪያው ባሉት አገሮች ላይ ግሚሱንም አሸንፈው ነጥቀውት እንደ ሶዶ ባሉት ቦታዎች ላይ ደግሞ ተደባልቀውት ከሚኖሩ ኦሮሞ ጎረቤቶቹ ጋር በአሁኑ ሰዓት በጉርብትናና በጋብቻ እየተደባለቀ ይኖራል። ቀደም ብሎ አዲስ አበባ ውስጥ በየካ ሚካኤል አካባቢ የሶዶ ጃዳ



ሰዎች ከእንግሊዝ ሊጋሲዮን አንስቶ ያለው ቦታ ላይ ሰፍረው ስለነበረ ዳግማዊ ምኒልክ ወደ ዓድዋ ሲዘምቱና በድል ሲመለሱ በሞቀ አሸኛኘትና አቀባበል ስላስደሰቷቸው እስከ ሰንዳፋ ድረስ ያለውን ቦታ በርስትነት መርቀውላቸው አሁን አካባቢው ሶዶ ጃዳ ይባላል።

የጉራጌ ጎሣ በብዛት በመላው ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ እየሠራ የሚኖር ታታሪ ሕዝብ ስለሆነ በሄደበት ሁሉ ተመሳስሎ ይኖራል። በአዲስ አበባም ውስጥ በሕዝብ ብዛት ከአማራ ቀጥሎ ይመደባል። ለኢትዮጵያችን ሙያና ባህል መዳበር የጉራጌ ኅበረተ ሰብ ያበረከተው አስተዋጽዖ በምግብ በኩል ብርንዶ እያሉ የሚበሉትን በአማርኛ ክትፎ በመባል የታወቀውን ተወዳጅ ምግብና ቆጮ የሚባል የዳቦ ዓይነት ሲሆን በማኅበራዊ ሥነ ምግባር ደግሞ ዕድርን ለመላው ኢትዮጵያ አውርሰዋል። በገንዘብ ቁጠባ በኩል አበዛኛዎቹ በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ስለሆነ የዕቁብን አሠራር ከሌላው ሕብረተ ሰብ በበለጠ ይጠቀሙበታል።

## ኦሮሞ

አለቃ ታየ ኦሮሞ የፈለሰው ከማዳጋስካር ነው ብለው ያሉት መሠረቱ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ከመሆኑም በላይ የማዳጋስካር ሰዎች በአብዛኛው የእስያ የማላይ ዘር ሲሆኑ በአገሪቱ የቅርብ ሰፋሪዎች መሆናቸው ይታወቃል። ደሴት እንደመሆኑ መጠን በዙሪያው በተለይ በደቡብ ጥቂት አረቦች፣ በምሥራቅ የፖሊንኤዥያ ጥቁሮችና በምዕራብ የአፍሪካ ጥቁሮች በየወደቦቻቸው በቅርቡ እየተደባለቁዋቸው ነው። በተረፈ አብዛኞዎቹ በተለይ በመሃል አገር የሚኖሩት ጠጉራቸውም ቀጥ ያለና እንደ ኢንዶኔዥያንና ማሊዥያኖች ዓይነት ነው። በቋንቋቸውም የኢንዶኔዥያኖችና የማሌዥያኖች ቋንቋ ዓይነት ሲሆን ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት በብዛት ያሉበት ነው። የሚያመርቱትም በዓይነቱ አንደኛ የሆነ ሩዝ ሲሆን በዓለም ውስጥ በአማካይ በሰው ከፍተኛ ሩዝ የሚበሉ ሕዝብ ናቸው።

ደሴቱ የጥንት ሰዎች ትተውት ያለፉት ምልክት ሊገኝበት ስላልቻለ በቅርብ ሰዎች የሰፈሩበት አንድ ትልቅ ደሴት እንደሆነ ነው የሚገመተው። ደሴቷ ስም እንኳን የወጣለት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በቫስኮ ዳ ጋማ ሲሆን በዚያን ጊዜ የኦሮሞ ጎሣ በባሌ አካባቢ ሰፍሮና

ተበራክቶ እየኖረ ወደ ሰሜንና ምዕራብ መፍለስ የጀመረበት ወቅት ነበር። ከዚህም ሌላ የኦሮሞ ጎሣ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ጎሣዎች ሁሉ የካም ዘር ሲኾን በባህል ከህንድ አምልኮት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት የሚታይበት ነው። እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ጎሣ ሁሉ በተለይ እንደ ሶማሌ የደቡብ ሕንድ ደም ጥንት በመጠኑ ተደባልቆበት ሊሆን ይችላል። እንደ አጋጣሚ እኔ ጸሐፊው ማዳጋስካር ውስጥ ለሁለት ዓመት የኖርኩ ስለኾነና ይህንኑ አባባል አውቅ ስለነበር በትኩረት ተመሳሳይነት ብፈልግም ላገኝ ስላልቻልኩ አባባሉ ትክክል ለመሆኑ ፍንጭ አላገኘሁበትም።

የኦሮሞ ሕዝብ ከ10ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ጀምሮ አሁን የበርበራ ሱማሌ በምትባለው አካባቢ የሚኖር ሕዝብ የነበረና በ12ኛው ክፍለ ዘመን በሶማሌዎች ግፊት ወደ ደቡብ ሄዶ በባሌ አካባቢ ሲኖር ቆየ። ከዚያም ኑሮው ከቆለኛነት ወደ ደገኛነት ሲለወጥ ጤናማና ከበርቴ ስለኾነ የሕዝቡም ቁጥር እየበዛ ሄደ። በመሠረቱ የኦሮሞ ሕዝብ መብዛትን የሚወድ ስለነበረ ጦርነት ላይ ሴትና ልጅ ማርኮ በባህሉ ማግባትና ማሳደግ፣ በሠላሙም ጊዜ ከአራት ሚስት በላይ በማግባቱና በጉዲፈቻና በማደጎ የሌላ ሰው ልጅ እየወሰደ እንደራሱ ልጅ በሞጋሳ የሚያሳድግ ስለኾነ ቁጥሩ እየበዛ ሄደ። በአሁኑ ወቅት በሕዝብ ብዛት የሚወዳደረው አማራ እንጂ ሌላ የሚደርስበት ጎሣ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም። በቅርቡ በጉዲፈቻ ልጅነት ካደጉት ውስጥ ከሚታወቁ የአማራ ልጆች መካከል ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንጠቅሳለን።

1ኛ ደጃች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ - አማራ (መንዜ)
2ኛ አቶ ተስፋዬ ቀጀላ - አማራ (መንዜ)
3ኛ ደጃች. ክፍሌና ካፒቴን አክሊሉ ዳዲ - አማሮች (ጎንደሬዎች)
4ኛ ደጃች. ገሰታ ቆርቾ - አማራ (መርሐ ቤቴ)
5ኛ አፈ ንጉሥ መስፍን ገመቹ - አማራ (መንዜ)
6ኛ አበበ ቢቂላ (ተጉለትና ቡልጋ)

የተቸገረ አማራ፣ ትግሬ ወይም ጉራጌ ልጁን በጉዲፈቻ የመስጠቱ ልምድ አሁን ድረስ ይሠራበታል። በተጨማሪም ልጅ ከከተማ እየወሰዱ በባላገር ለሚኖሩ የሚያቀርቡላቸው ሰዎች እስከ ዘመናችን ድረስ አሉ። ከከተማ ከሚወሰዱ ልጆች መካከል ለምሳሌ ነጭ አሜሪካኖች የሆኑ ሁለት እህትማማቾችና አንድ ወንድማቸው ሰበታ አካባቢ ከመኪና ውስጥ በልጅነታቸው ተወስደው በኦሮሞነት



አድገዋል። ወንዱ አሁን አዲስ አበባ አንበሳ አውቶቡስ ኩባንያ ውስጥ ይሠራል። ከሴቶቹ አንደኛዋ ሰበታ ከተማ እንጨት በማቅረብ ንግድ ስትተዳደር ሌላዋ ትዳር ይዛ ባላገር ውስጥ ትኖር ነበር። በአሁኑ ጊዜ ሁለቱም ሴቶች አዲስ አበባ ነዋሪ ቢሆኑም ነጋዴዋ ግን ሰበታ በገበያ ቀን ብቅ ማለቷን አልተወችም። በልጅነት ስለተወሰዱ የእናት አባት ቋንቋቸውን ረስተው በምትኩ ኦሮምኛ ተናጋሪ ሆነዋል። ከአደጉ በኋላ ትምሕርት ቤት ገብተው አማርኛ ተምረው መናገር ችለዋል። የሦስቱ ኦሮሞ ነጭ አሜሪካኖች ስም

አቶ ኃይለ ማርያም (ቀልቤሳ) ጋዲሳ
ወይዘሮ ትዕግስት ጋዲሳ
ወይዘሮ ሌንሳ ጋዲሳ ነው።

አንድ ሌላም ተመሳሳይ ሁኔታ ያላት ነጭ አሜሪካዊት ነኝ የምትል በችግረኝነት በአምቦ መንገድ ላይ እንደምትኖር ይታወቃል። በትዳር ስትኖር ባልዋ ልጆች ከወለዱ በኋላ በመሞቱ ተቸግራ እርዳታ እስከመጠየቅ መድረሷንና ዜናውም በቴሌቪዥን መተላለፉን ሰዎች ይናገራሉ። ይሁንና በልማድ አንድ የጉዲፈቻ ልጅ መብቱ ከተፈጥሮ ልጅ ጋር እኩል ነው።

የግራኝ ጦርነት የደጋውን የክርስቲያን ንጉሥ አገር ስላዳከመው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በይበልጥ ለኦሮሞ መስፋፋት ቀላል ኾነለት። በየደረሱበት ቦታም በባላባታቸው ስምና በአገኙት ምክንያት ሁሉ ለሰፈሩበት ቦታ የኦሮምኛ መጠሪያ ስም በመስጠት የበፊት ስሙን ደመሰሱ። አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጎጃም ውስጥ ያሰፈራቸው ኦሮሞዎች አገሩን ሜጫ ብለውት በዚሁ ስም ይታወቃል። በሸዋም ሌላ ሜጫ የሚባል አገር አለ። የባላባቶቻቸውን ስሞች እንደ ሜጫና ወሎ ያሉትን በአገር መጠሪያነት ተኩ።

| | | |
|---|---|---|
| ለምሳሌ | ደዋሮ | ጨርጨር |
| | ጋፋት | ሆሮ ጉድሩ |
| | ግራርያ | ሰላሌ |
| | ዳሞት | ወለጋ |
| | እናሪያ | ሊሙ |
| | አበቤ | በቾ |

እንደዚሁም ስማቸው ሳይለወጥ እንዳለ አሁንም የሚጠሩበት ስሞች ያሉዋቸው አዋሽ፣ ዝቋላ፣ የረርና ዝዋይ ናቸው። እንዶጥና የአዲስ አበባ[5] የቀድሞ ስም ነው ተብሎም ተጽፏል። በሌላ በኩል ደግሞ በተለመዱና አሁንም ሸገር ብለው ከተማውን የሚጠሩት የኦሮሞ ተወላጆች ቁጥር ጥቂት አይደለም። የአዲስ አበባ ከተማ በ1879 ዓ.ም በእቴጌ ጣይቱ ከመሰየሙ በፊት አንድ አጠቃላይ ስም ነበረው ለማለት ግን ይቸግራል። አገሩ በተለያዩ ባላባቶችና ሌሎች ስሞች የሚታወቅ አንድ ሰፊ ደን ነበረ ብሎ መደምደሙ ትክክል ይመስላል። እነዚህም ስሞች እንደ ጉለሌ፣ ኮተቤ፣ ኮልፌ፣ ኢንዶዴ፣ ላፍቶ ወዘተ.. ናቸው።

የኦሮሞ ሕዝብ የሚተዳደረው በገዳ ሥርዓት ስለነበረ በ16ኛውና 17ኛው ክፍለ ዘመን አከታትሎ ወደ ሰሜንና ምዕራብ ኢትዮጵያ እንደውሃ ፍሰት ከፊቱ የሚያገኘውን ሁሉ እየተዋጋና እየደመሰሰ የተከላከለውንም አልፎ እየሄደ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ክፍለ አገሮች አዳረሰ። በገዳ ሥርዓት ቡታ የሚባል የመስፋፋት ጦርነት ስለነበረ ለጎረቤቶቻቸው መዋጥ ወይም መፈጀት ዋንኛ ምክንያት ነበር። የኦሮሞ ጎሣ ያደርገው በነበረው መስፋፋት ወደ ደቡብም በመፍለስ በአሁን ጊዜ ኬንያ ውስጥ ተወላጆቹ በብዛት ይገኛሉ። እነሱም በኦሮሞነታቸው የሚያምኑና ቋንቋቸውም ኦሮምኛ ነው። እንዲያውም ኬንያና ታንዛኒያ ውስጥ ያለው የማሳይ ጎሣ በሁኔታው ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር የሚመሳሰልበት ብዙ ነገር አለው።

ኦሮሞ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ጎሣዎች በአንድ ኃይለኛ ንጉሥ ወይም በታወቀ መሪ እየተመራ የሚዋጋ ጎሣ ስላልነበረ በግለ ሰብ ስም የሚተረክ ታሪክ እጅግም የለውም። ይሁንና ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ጎሣዎች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ በመሰለ የአሿሿም ዘዴ ሕዝባዊ (ሬፑብሊካዊ) በሆነ ሥርዓት የሚተዳደረው ኦሮሞ ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም። ምክንያቱም መሪዎቹን በየስምንት ዓመት እየመረጠ በራሱ ሥርዓት ያለመዛባት ሲተዳደር የነበረና ሥርዓቱንም በደንብ ለማራመድ የቻለ ጎሣ

[5] አዲስ አበባን ፊንፊኔ ብለው የሚጠሩ አሉ። ቃሉ ፊን ከሚለው አማርኛ ቃል የተወሰደ ይመስላል። ፊንፊኔ የባንትይቀጡ መንደር ስም ሲሆን ነጋድራስ አፈወርቅ አጤ ምኒልክ በሚለው መጽሐፍ የአ.አ. የጥንት ስም ፊንፊኔ ነበር በማለታቸው ይኸንኑ ወስደው ይጠቅሳሉ።



በመሆኑ ነው። ችግርም ሲገጥመው ነገሮችን በአፈርሳታ፣ በአገር ሽማግሌ፣ በጋሎ ዳኞች እያጠና ይወስናል። ይህም ሁኔታ በሕዝብ ፊት የመናገር ችሎታን ለተከታዩ ትውልድ አውርሶታል።

በመሠረቱ የአኗኗሩ ሁኔታ ከብት ማርባት ስለነበረ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ተመልሶ በጦርነት መሸነፍ ሲጀምር ስለመሬት እጅግም ደንታ ስላልነበረው እርሻ የለመደው የሰሜን ሰው የሚፈልገውን ያህል መሬት ለመያዝ ሲሽቀዳደም ኦሮሞ ግን ከብቱ የሚግጥበት ቦታ እስካለው ድረስ እጅግም አልተጨነቀበትም ነበር። በኋላ ግን እርሻ እየለመደ ሲሄድ አብዛኛው መሬት ስለተያዘና የሚያርሰው ስላነሰ ችግር እየተፈጠረ ሄደና አለመግባባት መጣ።

ኦሮሞ በሃይማኖት በኩል በአንድ ዋቅ ወይም ረቢ በሚለው አምላክ የሚያምን ሲሆን የሃይማኖቱን ሥነ ሥርዓት የሚያካሂደው በውጋዳርና በትልቅ ዛፍ ሥር ነው። ይኸንኑ የጥንቱን የአምልኮ ባህል ይከተል ስለነበረ በሚስፋፋበት ጊዜ እንደአሰፋፈሩ በአካባቢው ያሉትን ሃይሞኖቶች መተካት ጀመረ። በባሌ፣ አርሲና ሐረር እስልምናን ሲቀበል በሸዋና በአቅራቢያ የሠፈሩት የኦርቶዶክስ ክርስትናን ተቀበሉ። ራቅ ባሉ ቦታዎች የወንጌል መልዕክተኞች እየገቡ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን እንዲቀበሉ አድርገዋል። በተጨማሪም የወንጌል መልዕክተኞች በሐዝቡ ቋንቋ ሃይማኖትን ማስተማር ይመርጡ ስለነበረ በግዕዙ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ በየቋንቋው ማስተርጎም ሲጀምሩ የኦሮምኛውን መጽሐፍ ቅዱስ (መጽሐፈ ቁልቁሎ) ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በፊት የሳባውን ፊደል በመጠቀም አጽፈዋል።

በቅርቡ የሳባውን ፊደል በመተው ቁቤ ተብሎ የሚታወቀውን የላቲን ፊደል መጠቀም ጀምረዋል። እዚህ ላይ ሰዎቹ የተለያዩባቸው ሃሳቦች አሉዋቸው። በላቲን ፊደል መጠቀምን የሚደግፉት ወገኖች የሳባው ፊደል ቁጠሩ የበዛ ስለሆነ እንደላቲኑ ፊደል በአጭር ጊዜ ውስጥ በሕዝቡ ታውቆ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ሲሉ በተጨማሪም በኦሮምኛ ቋንቋ ባህሪ የመሳብና የመሰብሰብ ድምጸ ስላለበት ጽሑፉን ሲያነቡት አሻሚ አይሆንም የሚል ነው። የማይደግፉት ደግሞ በቁቤ መጻፍ የተጀመረው በግፊትና ሕዝብ በረጋ መንፈስ ሳይመክርበት ነው። ሁለተኛ ደግሞ የራሳችንን የሳባ ፊደል መተዉ ከሌሎች

ወገኖቻችን ያራርቀናልና ለምን እንተወዋለን የሚል ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ አንዳንድ ድምጾች በሮማው ፊደል የሌሉት በሳባው ፊደል ስለአሉ የጎደሉም ካሉ ማሟላት ይቻላል የሚል ነው። የሁንና በቁቤ በሚጻፍበት ጊዜ የተደጋገመ ፊደል በመጻፍ አለአስፈላጊ ፊደል መደርደር ነው ብለው የሚያስቡም አሉ።

የፊደል ነገር በጥሞናና በመግባባት ውሳኔ ከተደረሰበት ችግር ቢገጥምም ሊቃለል ይችላል። ለመሻሻል የሚረዳ ከሆነ የፊደሉ መለወጥ አሳሳቢ አይሆንም። ሶማሊያና ቱርክ የአረብኛውን ፊደል ትተው በላቲን እንደሚጠቀሙ እናውቃለን። በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸውን ፊደል ትተው በአረብኛ የሚጠቀሙ ሱዳኖችን አይተናል። አንዳንዶች ደግሞ ጥቂርም እንደነጭ በራሱ ፊደል የሚጽፍ መሆኑ ለማሳየት ፊደላችንን ማቆየቱ ኩራታችን ነው የሚል ነው። ስለሆነም ነው ህንዶች ጃፓኖችና ቻይናዎች በፊደላቸው ላይ ሙጭጭ ብለው የቀሩት።

ኦሮሞ ከጊዜ ብዛት በየሰፈረበት ቦታ ሲኖር በወለጋ አካባቢ የኩምሳ ሞረዳ ተወላጆችና የጆቴ ቱሉ ተወላጆች ቆሮዎች (ባላባቶች) ኾኑ። በሊሙ ጅማ ላይ የሚቀመጥ አንድ የቆሮ ባላባት ግንድ ተፈጠረ። በሸዋም የተለያዩ ባላባቶች ብቅ ማለት ጀመሩ።



አባ ጅፋር ጢቃ

## የጅማ ቆሮ (ባላባት)

በኦሮምኛ ጉዳ ማለት ትልቁ፣ ጢቃ ማለት ትንሹ፣ ለማለት የተጨመሩ ቃላቶች ናቸው። በሊሙ ኦሮሞ አባ ከመጠሪያ ስም ጋር ተጨምሮ የሚነገር የክብር ተቀጽላ ነው። አባ ጅፋር ጉዳ አባ ጎሞልን ይወልዳሉ፣ አባ ጎሞል አባ ሬቦን ይወልዳሉ። አባ ሬቦ በጣም ጦረኛ ነበሩ። አባ ሬቦ አባ ጅፋር ጢቃን ይወልዳሉ። አባ ጅፋር በአፄ ምኒልክ ዘመን የነበሩ የጅማ ባላባት ሲሁኑ ድል ኾነው ለመገበር ስለተስማሙ ተመልሰው በባላባትነታቸው አገር እንዲያስተዳድሩ ተሾመዋል።



አባ ጅፋር አባ ጆቢርን ይወልዳሉ። ሡልጣን አባ ጆቢር በጣሊያን ወረራ ጊዜ የጅማ ባላባት የነበሩ ሲሆን አክራሪ ሙስሊም ስለነበሩ ብዙ ክርስቲያኖች ላይ በደል ቢፈጽሙም ከወረራው በኋላ ግን ምሕረት ተደርጎላቸዋል። እንዲያውም የኦሮሞ መንግሥት ለመመሥረት የአካባቢ ባላባቶችን ሲያማክሩ የሚጫና ጅባት ባላባት አባ ዶዮ ነጭና ቀይ ጤፍ ደባልቀው እስከመለስ ድረስ ለዩና ጠብቁኝ ብለው ሄዱ ይባላል። ከዚያም ሲመለሱ ጤፉን መለየቱ የማይቻል መሆኑ ሲነገራቸው "በሉ አማራንና ኦሮሞን ለመለያየት ስለሚያስቸግር አገራችንን በኅብረት እንገንባ እንጂ መለያየቱ ይቅር" አሉና የተጀመረው ዕቅድ ሥራ ላይ ሳይውል ቀረ እየተባለ በሰፊው ይወሳል።

የአባ ጆቢር ልጅ አባ ቢያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ምሩቅ የሆኑ ሲሆኑ ለብዙ ቦታዎች የታጩና ለአገሪቱ ብዙ መሥራት የሚችሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው። ይሁንና አሁን የሚኖሩት አሜሪካን አገር ነው። ሌላዋ ልጅ ወይዘሮ ላጢፋ ከአቶ ጀሃድ አባቆያስ ጋር ተጋብተው አዲስ አበባ ውስጥ ነዋሪ ሆነዋል።

## አፋር



ፊታውራሪ ያሆ ሙሐመድ ሃንፍሬ

አፋር በአንድ የበላይ ባላባትና በንዑሳን ባላባቶች ይተዳደራሉ። በጠቅላላው የ16 ባላባት አገር ሲሆን ስድስቱ በጅቡቲ ሌላው በኢትዮጵያና በኤርትራ ውስጥ ይገኛል። የአፋር መሬት የዳህላክ ደሴቶችንም ይጨምራል። ይህ ጎሣ የሚኖርበት አካባቢ በረሃ ከመሆኑ ሌላ የኢትዮጵያ መውጫና መግቢያ ስለኾነ ኢትዮጵያን ለማጥቃት የፈለገ ሁሉ ከምዕዋ አንስቶ መጀመሪያ የሚያጠቃው የአፋርን መሬት ነው።

በዚሁም ምክንያት ባላባቶቹም ጠንካራና በሕዝባቸው የሚደገፉ ስለኾኑ የሚመጣውን ሁሉ ሲከላከሉ የኖሩ ጀግና ጎሣ ናቸው። ይሁን እንጂ ፈረንሳይ ጅቡቲን ስትለቅ በጅቡቲ ውስጥ በሕዝብ ብዛት

አፋሮች ብልጫ እያላቸው ሥልጣኑን አንድ ሦስተኛ ለሆኑት ሶማሊዎች አስረክባ በመሄዷ ለጭቆና ዳርጋቸዋለች። የሞቃድሾ ሶማሊ መንግሥት ሲፈራርስ በስደተኝነት ከሶማሊ እየመጡ ጂቡቲ ውስጥ መኖር ሲጀምሩ በአገሪቱ ውስጥ የሶማሌው ቁጥር እየጨመረ ሄደ።

በአፋር ሁሉ ነገር የባላባቱ ስለኾነ በባህሉ መሠረት የፈለገውን ማድረግ ይችላል። ሆኖም ባላባቱ ለንጉሠ ነገሥቱ በተራው ይገብራል። የደጃዝማች ያሆ ሞሐመድ አባት ሃንፍሬ ዳግማዊ ምኒልክ ወደ አድዋ ሲዘምቱ አብረው እንዲዘምቱ ቢነገራቸው አሻፈረኝ ብለው ሸፈቱ። በዚህም ምክንያት አዛዥ ወልደ ጻድቅ ታዘው ወግተዋቸዋል። ይሄንን ዘመቻ የሰሙት ደጃዝማች ጓንጉል በአፄ ምኒልክ ላይ ሸፈተው ከነበረበት ከአዳል በርሃ መልዕክተኛ ልከው አብሬ የአገሬን ጠላት እንድዋጋ ምሕረት ይደረግልኝ ብለው በመጠየቅ አፄ ምኒልክ ወዲያው ተስማምተው አብረው ዘመቱ። ተተኪው ዋናው የአፋር ባላባት ፊታውራሪ ያሆ በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ከማዕከላዊው መንግሥት በማፈንገጣቸው በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ከሞቱ በኋላ ቢትወደድ ዓሊ ሚራህ ሃንፍሬ በምትካቸው የበላይ ባላባት ኾነዋል።

ቢትወደድ ዓሊ ሚራህ ሃንፍሬ ዕድሜያቸው ረዥምና ዕድል ያልከዳቸው ሰው ናቸው። ደርግ ባንድ በኩል እየረገመ በአንድ በኩል እየመረቀ እጃቸውን ሊይዝ ባደረገው ሙከራ ብዙ ወታደር ከሁለቱም ወገን ካለቀ በኋላ አምልጠውት ወደ ጅቡቲ ገብተው ከዚያም በኋላ በስደት ኖረው ኢሕአዴግ ሲገባ እንደገና ወደ አገራቸው ተመለሱ። ኢሕአዴግ ባመቻቸው አንድ ትልቅ ስብሰባ ላይ ተካፍለው የባንዲራ ጉዳይ ተነስቶ "እንኳን እኛ አፋሮቹ ግመሎቻችን ሳይቀሩ የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቃሉ" ብለው ተናግረዋል። ምንም እንኳን አሁን አፋርን የተመረጡ አስተዳዳሪዎች ያስተዳድሩታል ቢባልም አሁንም በሕይወት ያሉ የተከበሩና የታመነባቸው የአፋር የባህል መሪ ቢትወደድ ዓሊሚራህ ሃንፍሬ ናቸው።

## ሶማሌ

በሶማሌ ጎሣ ውስጥ ብዙ ጎጦች (ክላኖች) ስላሉ እያንዳንዳቸው በየባላባታቸው ይተዳደራሉ። አገራቸውን ከኢትዮጵያ ነጥለው



የምዕራባውያን አገሮች ሲወስዱ ተደራጅተው መዋጋት የማይችሉ ገና በጦርና በፍላፃ የሚጠቀሙ ስለነበሩ አብዛኞዎቹ በቅኝ ግዛት ቀንበር ውስጥ ገብተዋል። ይሁንና የማዕከላዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ራሱ ደካማ ስለነበረ ከመሬት ዘረፋው ተከላክሎ ሊያድን የቻለው የኦጋዴንን ሶማሊ ብቻ ነበር። ስለኾነም ምሥራቁ በኢጣሊያን ሰሜኑ በእንግሊዝ ሲያዝ በከፊል ደግሞ እንግሊዝ ከኬንያ ጋር ደባልቆ ደበቡን ያስተዳድር ነበር። በኋላ ግን እንግሊዝ በጎነጎነችው ተንኮል ታላቅዋ ሶማሊያ የሚል አስተሳሰብ በመፍጠሯ በሞቃድሾ የተመሠረተው የሶማሊ መንግሥት ከጎረቤቱ ጋር ሁሉ ሲዋጋ ራሱ ደክሞ ማዕከላዊው የሶማሌ መንግሥት ስለፈረሰ እንደገና ሶማሊዎች በየጎሣቸው እየተዋጉ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ሶማሊዎችም አንዱ የኢትዮጵያ ጎሣ ስለሆኑ መብታቸው ተከብሮ ቢኖሩም የሞቃዲሾውን መንፈስ ይዘው የመጡ ስደተኞች አድራጊ ፈጣሪ እየሆኑ ችግር በመጠኑም ፈጥረዋል። ይሁንና በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ኦጋዴን ውስጥ ያሉት በየባላባታቸው ሥር ቢኖሩም የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት አንድ አውራጃ ስለነበረ የበላይ አስተዳዳሪ ነበረው። መጨረሻ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በደርግ ዘመነ መንግሥት ሲተካ 29 የአስተዳደር አካባቢዎች ራስ ገዝ ሲሆኑ ኦጋዴንም አንዱ የአስተዳደር አካባቢ በመሆን በሚሾም ባለሥልጣን ይተዳደር ጀመር።

የሞቃድሾው መንግሥት ፈራርሶ በስደት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሶማሊዎች በፊት ሲነገራቸው የነበረው ጥላቻ አለመኖሩንና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሠላም ስለተቀበላቸው ጥላቻው የመንግሥት ፖለቲካ እንጂ የሕዝቡ እንዳልነበረ ተረዱ።

## አደሬ

አደሬ በሐረር ከተማ ውስጥ ብቻ የሚኖር የአንድ የጎሣ ስም ነው። አደሬዎች ቀደም ባለው ዘመን ከሸዋ አይመለል ወደ ሐረርጌ የሄዱ ሲሆኑ በቅርበት የሚዛመዷቸው ስልጤዎች ናቸው። በግራኝ አሕመድ ንቅናቄ ጊዜ ከአረብና ከቱርክ አገሮች በቅጥርና በዕርዳታ የመጡ ወታደሮች ጦርነቱ ሲያበቃ ያልተመለሱት በሃይማኖት አንድነት ምክንያት ከአደሬዎች ጋር ተጋብተው ቀርተዋል። በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት ግብጾች አስገረው ገብተው ለአሥራ አንድ

ዓመት ስለቆዩ በዘመኑ የወለዱዋቸው ልጆች በጎሣው ውስጥ ተውጠዋል። ስለሆነም ከሌላው ኢትዮጵያዊ በአማካይ ቀላ ይላሉ።

በኦሮሞ መስፋፋትና በሌሎችም ምክንያቶች አደሬዎች በመጨረሻ የተገኙት በሐረር ከተማ ግንብ ውስጥ ብቻ ነበር። በ1940 ዎቹ ዓ.ም ውስጥ መንግሥት ለመመሥረት ሲያድሙና በመስጊዳቸው ውስጥ በድብቅ የጦር መሣሪያ ሲያከብቱ ተይዘው አድመኞቹ ከተፈረደባቸው በኋላ በመላ ኢትዮጵያ ስለተሰራጩ፣ ፖለቲካውን ትተው የንግድ ሥራቸውን በማስፋፋት ኑሯቸውን ቀጠሉ። አዲስ አበባ ውስጥ በመርካቶ አካባቢ በብዛት ይኖራሉ። በዚሁ ምክንያት አዲስ አበባ ውስጥ የአደሬ ሠፈር የሚባል መንደር አለ። በተጨማሪም በመካኒሳ መንገድ ከቫቲካን ኤምባሲ በታቸ የሚኖሩበት ሰፈር ከእነ መስጊዱ ጭምር አላቸው። በተጨማሪም በሰበታ መንገድ ዳለቲ በሚባል መንደር በከብት እርባታ፣ በአነስተኛ ኢንዱስትሪና እርሻ ተሠማርተው ይኖራሉ።

አደሬዎች ቋንቋቸው እንደ ግዕዝ፣ አማርኛ፣ ትግርኛና ጉራጊኛ የሴም ቋንቋ ሲሆን በብዛት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የተለየ የባህል ልብሳቸውም ቀለምና ጌጥ የበዛው ነው። ሴቶቻቸው የእጅ ሥራ አዋቂ ከመሆናቸውም በላይ በመኖሪያ ቤታቸው ግድግዳዎች ላይ የተጌጡ የምግብ ቤት ቁሳቁሶችን በመስቀል ቤታቸውን ያስውባሉ።

የአደሬዎች የሕዝብ ብዛት በአሁኑ ወቅት ወደ አርባ ሺህ ስለሆነና ከሌላው ጎሣ ጋር ሲወዳደር በጣም በማነሱ ምክንያት ዘራቸው እንዳይዋጥና እንዳይጠፋ በማለት ወታደርነት እጅግም አይገቡም፤ እንዲሁም ከሌላም ጎሣ ጋር በተቻለ መጠን አይጋቡም። ጋብቻቸው ብዙውን ጊዜ ከቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር (Inbreeding) ነው።

## ማጂ

በከፋ ግዛት ውስጥ የማጂ ጎልዲያ ጎሣ የሚገኘው በኢትዮጵያ የምዕራብ ጠረፍ ሲሆን የማጂ ከተማ የተቆረቆረው በ1879 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ጋር አንድ ዘመን መሆኑ ነው። ከተማው የተመሠረተው



በራስ ወልደ ጊዮርጊስ ነው። ማጂ ሱዳን ወሰን አጠገብ ያለ አውራጃ ሲሆን የራሱ ቋንቋና ባህል ያለው ጎሣ የሚኖርበት አገር ነው።

ማጂ አውራጃ ለሱዳን አገር የቀረበ ስለሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የእንግሊዝ መንግሥት በማጂ ከተማ ቆንስላ ጽሕፈት ቤቱን አቋቁሞ ነበር። በኢትዮጵያና ጣሊያን ጦርነት ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት በማጂ ተቋቁሞ የነበረውን የእንጨት መሰንጠቂያና የጡብ ፋብሪካ ነቅሎ ወደ ሱዳን አሻግሮታል። የማጂ ወረዳዎች ትርማና ጥዱ፣ ቲሻ ወይም ሜኢኒት በመባል ይታወቃሉ። የሕዝቡ ብዛት አናሳ ነው። እንደማንኛውም ጎሣ ማጂ ባላባቶች አሉት። ከነዚህም የሚታወቁት ፊታውራሪ ኩሪ፤ ፊታውራሪ ጋሲ፤ ፊታውራሪ አዲካስ፤ ፊታውራሪ አርቡርጂ ናቸው።

ጣሊያን ጀምሮት የሄደው የመኪና መንገድ ስላላለቀና ስላልተጠገነ ማጂ ከአዲስ አበባ ጋር ያለው ግንኙነት በአየር ብቻ ተወስኖ ቀረ። አገሩ ቀደም ሲል ጀምሮ ስልክ፣ የአይሮፕላን ማረፊያ፣ ትምሕርት ቤትና ጤና ጣቢያ አለው። በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ስልክ ሲገባ ከሐረር አዲስ አበባ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ጊዳሚና ማጂ ነበር።

## ማጠቃለያ

በዓለማችን በሚገኙት አብዛኞዎቹ አገሮች ውስጥ የተለያዩ ጎሣዎች እንዳሉ ይታወቃል። ከእነዚሁም መካከለ ጥቂቶቹ የጎሣቸው ሰው ብዛት ከፍ ያለ ሲሆን በርካታዎቹ ደግሞ አነስተኛ ቁጥር አሉዋቸው። ለምሳሌ ህንድ ከ 400 በላይ ጎሣዎች አሏት። ኢትዮጵያም ውስጥ ወደ 80 ጎሣዎች እንዳሉ የነገራል። በመግባባትና በዘዴ ከተጠቀሙበት ይህ ራሱ ትልቅ ሃብት ነው። መላው ኅብረተ ሰብ "ልዩነት በአንድነት" ብሎ ካመነና የእያንዳንዱን ኅብረተ ሰብ ባህል ካዳበረው ጥቅሙ ወደፊት ይታወቃል። አለበለዚያ ግን ጠላቶች እንደሚመኙት ለመፍረክረክ፣ አቅመቢስና ደካማ ለመሆን የጠላት መሣሪያ ሊሆን ይችላል። ይሁንና እላይ ከተጠቀሱት ጎሣዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ አነስተኛ የሰው ብዛት ያላቸው ጎሣዎች በየቦታው ይኖራሉ። አንዳንዶቹ ቁጥራቸው ከፍ ያሉ ሲሆኑ እንዲሁም ሌሎቹ አነስተኛ ናቸው። በመሠረቱ ሁሉም በየባላባታቸው የሚተዳደሩ የነበሩ ሲሆን በአፄ ምኒልክና በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን

መንግሥት የማዕከላዊው መንግሥት እየጠነከረ ስለሄደ በባህላቸው መሠረት በየባላባቶቻቸው ያለሥልጣን አንዳንዶቹም ያለባላባት ቢኖሩም ሁሉም በመንግሥት ሹሞች የሚተዳደሩ ኾነዋል።

ሥልጣን ባለው ባላባት በሚተዳደሩበት ጊዜ ምንም በመሠረቱ ዘመናዊነትን ያልተላበሰ አገዛዝ ቢሆንም በአጠቃላይ የሚጠቁመው የፌዴራል አስተዳደር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበረ ነው። ስለኾነም የፌዴራል አስተዳደር ቃሉ አዲስ ይሁን እንጂ በተግባር ግን በፊትም እንደነበረና ጥቅሙም ጉዳቱም የሚታወቅ መሆኑን ነው። በተጨማሪም አገራቱ የባህል ኃብታም እንደኾነች ማወቅ ይጠቅማል። ጥቅሙ ግን የሚታወቀው ጥሩ ጥሩውን ሁሉም እየተዋዋሱና እያራቡ ሊጠቀሙበት ሲችሉ ነው።





# ምዕራፍ ፫

## የአፄ ምኒልክ ፍጻሜ

ማይጨው ሲዘመት የጦር ሚኒስትር የነበሩት ራስ ሙሉጌታ በማይጨው ጦርነት ላይ በጥይት ተመተው ሲወድቁ ንስሐቸውን ለመናገር ሞክረው ሳይጨርሱት አልፈዋል። ከተናገሩት ውስጥ "አፄ ምኒልክን ሦስት ኾነን በቡና መርዝ አቅምሰናቸው ነው የሞቱት[6]" ብለው የሌሎቹን ስም ሳይጠሩ ማጥም ብለዋል። ሃሜቱ ግን እቴጌ ጣይቱ ጥቁር ድመት ሁፋናቸው ላይ አድርገው በመተት እንደገደሏቸው ሲሆን በዚህ አሉባልታ እቴጌይቱን በአካባቢያቸው የነበሩ ሁሉ ምንም አልፈረዱባቸውም። እንዲያውም በደንብ እንዳስታመሟቸው ነው የሚነገርላቸው።



አፄ ምኒልክ ኃይለ መለኮት

እንኳን በቤተ መንግሥት በቤተ ክህነትም ውስጥ በመርዝ መገዳደል በእኛ አገር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች የተለመደ ነገር ነው። ለምሳሌ ዮሐንስ ጳውሎስ 1ኛ በተሾሙ በስድስተኛው ወር ቫቲካን ውስጥ በመርዝ ተገድለዋል። በአገራችን በማይታወቅ በሽታ ሰው

[6] ቀይ አንበሳ .. ገጽ 190

በሞተ ቁጥር በመድሃኒት እንደተገደለ አድርገን እንቆጥረዋለን። የነርሱ መከመተር ጉንፋኑን ቢያጣምመው ሰይጣን በጥፊ መታው ብለን እናስባለን።

የአፄ ምኒልክ ህመም ትክክለኛ ሁኔታ የደም ግፊት በሽታ ስለነበረ ወደ አዲስ ዓለም በበቅሎ ለመሄድ መንገድ ጀምረው ሥጋ ሜዳ ሲደርሱ በሚያዝያ ወር 1900 ዓ.ም. ለአራተኛ ጊዜ በጠና ይታመሙና ወደ መናገሻ ከተማቸው ይመለሳሉ። ሕመሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰማቸው በሚያዚያ ወር 1896 ዓ.ም. ነበር። እያደር በጠና ስለታመሙ ደብረ ሊባኖስ ሄደው ጠበል ሲያጠምቋቸው ከብርዱ የተነሳ እንዲተዋቸው ቢማጸኑም ሰሚ አላገኙም። በሁለተኛው ወር ሕዝቡ ስላጉረመረመ ተመለሱ። "እባካችሁ አድኑኝ ብዙ የምሠራው አለኝ" እያሉ ቢማጸኑም በህክምና ሊድኑ አልቻሉም። እንዲያውም መናገርም እየቃታቸውና በሽታቸው እየባሰባቸው መሄዱን ሲገነዘቡና የውጭ አገር ቆንሲሎች ተተኪውን ሰው ለመለየት ጥያቄ ስላበዙ፣ ከልጃቸው ከወ/ሮ ሸዋ አረጋና ከወሎው ራስ ሚካኤል የተወለደውን የልጅ ልጃቸውን አቤቶ ኢያሱን በሰኔ ወር 1900 ዓ.ም. አልጋ ወራሽ አድርገው ሾሙት። ለሕዝቡ ግን ጉባዔው ጃንሜዳ ላይ የተነበበው በ1901 ዓ.ም. ነበር።

"እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተፈጠረበትና ፈቃዱ ሆኖ ልጄን ቢአቆምላችሁ ከልጄ ጋር ሁናችሁ አገራችሁን ጠብቁ፣ አደራ ብያችኋለሁ፣" ብለው አልጋ ወራሻቸው መሆኑን ይፋ አደረጉ። መኳንንቶቻቸውንም ሰብስበው "የልጄን ነገር አደራ፣ እርዱት፣ ተባበሩት፣ እሱን ግን የከዳ በሰማይ ነፍሱ በምድርም ሥጋው ከልጅ እስከልጅ የተረገመ ይሁን። የኢትዮጵያ ውቃቢ ያጥፋው" ብለው አወገዙ። አቤቶ ኢያሱም ገና ልጅ ስለነበረ የሸዋው ራስ ቢትወደድ ተሰማን ሞግዚት አድርገው ሾሙለት።



ግብጻዊው አቡነ ማቴዎስ

በተመሳሳይም ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ "የከዳውን ሰው እግዚአብሔር ስሙን ከዘመዱ ከርስቱ ያጥፋው።



ዘር አይውጣለት፣ የሚበላው እንጀራ፣ የሚጠጣው ውሃ የተረገመ ይሁን። የተከተለውም አሽከር እርጉም ይሁን። ከዚህ ቃል የሚወጣውን ሰው ገዝቻለሁ። እንኳን ቃሌ አጥንቴ በመቃብር አይፍታው" ብለው አወገዙ።



አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ

አፄ ምኒልክ በሽታቸው እየጠና ሄዶ የመንግሥቱን ሥራ መከታተል ስላቃታቸው እቴጌ ጣይቱ በምኒልክ ስም የመንግሥቱን ሥራ ማስፈጸም ጀመሩ። ይሁን እንጂ አፄ ምኒልክ በ1889 ዓ.ም ሚኒስትሮች ሾመው የመንግሥቱን ሥራ አከፋፍለው ማካሄድ ጀምረው ነበር። ታዲያ የእቴጌ ሥልጣን መያዝ የከነከናቸው መኳንንቶች ተሰብስበው መዶለት ጀመሩ። እቴጌ ጣይቱም አድማው የተጀመረው ከሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑን ተገንዝበው ሚኒስትሮቹን በተኑና ሜራውን ለጊዜው አፈናገፉ። ለቤተ ክህነት አለቆችና ለኤምባሲዎች ደብዳቤ ጽፈው በገጠማቸው ችግር ላይ እንዲረዱዋቸው ተማጸኑ። ይህ ጥረታቸው እንዲያውም ለአድመኞቹ መጠቀሚያ ሆኖ በአገር ጉዳይ የውጭ ሰዎችን ጣልቃ አስገቡ ተብለው ስለተወቀሱ አድማው እንደገና አገርሽቶበት እቴጌይቱን እቤት ቁጭ ብለው ባለቤታቸውን እንዲያስታምሙና የመንግሥቱን ሥልጣን ለአልጋ

ወራሹ ለአቤቶ ኢያሱ እንዲተላለፍ ስለተስማሙ ይኸው በመጋቢት ወር 1902 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን ተደረገ።



አፄ ምኒልክ ኃይለ መለኮት

የእቴጌ ጣይቱ ከሥልጣን መወገድ የብዙ ነገሮች ውጤት ነበረ። በአንድ በኩል የአድዋ ጦርነትና የድሉም መሳካት የእሳቸው ቆራጥነት ያስከተለው ስለነበረ ፈረንጆቹ እቴጌን ጥምድ አድርገው ስለ ያዙዋቸውና መኳንንቶቹን እንደቀሰቀሱባቸው ግልጽ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከግብጽ ጳጳስ ማስመጣቱን እንደማይደግፉ ይታወቅ ስለነበረና አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው የዴር ሡልጣን ባለቤትነት የኢትዮጵያ መሆኑን እያወቁ ለግብጽ አድልተው ስለመሰከሩ እቴጌ ጣይቱ ለአንድ ዓመት አዲስ ዓለም አግዘዋቸው ስለነበረ ሊቀ ጳጳሱ እቴጌን በማሻር ተበቀሉ። በመጨረሻው ደግሞ ዘውዱን ወደ ጎንደር ይመልሱታል የሚል የሸዋ መኳንንቶች ፍርሃትም ነበረ። በመሆኑም ራስ ቢትወደድ ተሰማ የልጅ ኢያሱ ሞግዚት የአልጋ ወራሹ አደራ በሳቸው ጫንቃ ላይ ስለነበረ የእቴጌ ሥልጣን መያዝ ያስፈራቸው ነበር። ይህ ሁሉ ተደማምሮ እቴጌ ጣይቱ ባለቤታቸውን እንዲያስታምሙ ስለተባለ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከእንጀራ ልጃቸው ከወይዘሮ ዘውዲቱ ጋር አርፈው ተቀመጡ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ማቴዎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በነበረ ጊዜ የኢትዮጵያ ገዳማት ርስት ሆኖ በቆየውና የሚካኤልና አርባዕቱ እንስሳት ታቦቶች በሚገኙበት ዴር ሡልጣን ገዳም ይዞታ ላይ ጥያቄ ተነስቶ ገዳሙ የግብጻውያን ስለመሆኑ እንደመሰከሩ በኢትዮጵያ ወሬው ደርሶ ነበር። ነገሩም ለኢትዮጵያ መንግሥት የደረሰው ከደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ጋር የአቡነ ማቴዎስ ተከታይ ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ተልከው የነበሩት አቶ ኃይለ ማርያም ሰራቢዮን ጋሻ ለእቴጌ ጣይቱ



ባቀረቡት ሪፖርት ነው። ይህን በተመለከተ በኢየሩሳሌም ሃያ አምስት ዓመት የተቀመጡት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ስለዴር ሡልጣን የተናገሩትን ገበታ ሐዋርያ የንባብ መማሪያ በ1928 ዓ.ም ከደስታ ተክለ ወልድ ከተጻፈው መጽሐፍ ገጽ 49 ላይ ይመልከቱ። ጉዳዩን ለማብራራት ያህል አቡነ ማቴዎስ የዴር ሡልጣን ገዳም ንብረትነቱ የግብጽ እንጂ የኢትዮጵያ እንዳልሆነ በማስመልከት የበሩ ቁልፍ ወደ ግብጻውያን መነኮሳት መዛወር እንዳለበት በሰጡት የጽሑፍ ማስታወሻ የተረጋገጠ ነው። በ1945 ዓ.ም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሆነው አዲስ የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ ጉዳዩን ተከታትለው ከቆዩ በኋላ አቡነ ማቴዎስ ትውልዳቸውም ሆነ ዜግነታቸው ግብጻዊ እንደመሆናቸውና ለእኛም ጳጳስነት የበቁት በግላችን በምንከፍላቸው ገንዘብ እንደመሆኑ ለግብጽ አድልተው በእኛ መመስከራቸው ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ መሆኑን አስረዱ። ውሳኔውንም በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ በወቅቱ የግብጽ ኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስ ይህንኑ ከመቃወም አልፈው አቡነ ፊልጶስን ከኢየሩሳሌም የጽጽስና ወንበር እስከነአካቴው እንዲነሱ በሰጡት ትዕዛዝ ጉዳዩ እንደተዘጋ ቆይቶ ነበር።


ቀድሞ ብሎ እቴጌ ጣይቱ ይህንኑ ጉዳይ ከሥረ መሠረቱ በማጤን ከተረዱት በኋላ ለአቡነ ማቴዎስ የነበራቸው ክብሬታና ስለታማኝነታቸው የነበራቸው አስተያየት እጅጉን ዝቅ ያለ ነበር። ይህም በመሆኑ አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያን ጥቅም የማይወክሉ መሆናቸውን በመገንዘብና እቴጌይቱ አቡኑን እንደ አደገኛ ሰው በማየት ተጻራሪ አቋም ይወስዱባቸው ነበር። በተለይም አፄ ምኒልክ በ1900 ዓም የተለያዩ ሚኒስትሮችን ሲሾሙ አቡነ ማቴዎስ የመጀመሪያውን የዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት በማቋቋም በኩል የነበራቸውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ የትምሕርት ሚኒስትርነትን ስፍራ ለእሳቸው እንደሚገባ ተጠቁሞ አፄ ምኒልክ ዘንድ ሲቀርቡ እቴጌ ጣይቱ "ጌታችን ለጥቂት ያልታመነ ለብዙ እንዴት ይታመናል ብሎ የለምን" ብለው በመከራከር ስለተቃወሟቸው ሥልጣኑ እንደማይገባቸው ታምኖበት ሳይሾሙ ቀሩ። እንዲያውም በየምክንያቱ ሳይሳካላቸው ቀርቶ ነው እንጂ እቴጌ ጣይቱ ከዚህ አልፈው በመሄድ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ በግብጽ ፋንታ ከሶርያ ኦርቶዶክስ

ቢተክርስቲያን እንዲመጣ መክረው እንደነበረ ይነገራል። አቡነ ማቴዎስም ከዚያን ጊዜ ወዲህ ቂም ይዘው ስለነበረ በእቴጌ ጣይቱ ላይ መኳንንቶቹ በጠነሰሱት የሥልጣን ማስወገድ አድማ ላይ ቀንደኛ በመሆን ቂማቸውን ለመወጣት የወሰዱት አቋም እንደሆነ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ከ1832 እስከ 1910 በሚለው መጽሐፍ ላይ ቀኛዝማች ታደለ ዘውዴ ገልጸውታል።

አፄ ምኒልክ ክትግራይ መሳፍንት ላይ መንግሥቱን በመውሰዳቸው መሳፍንቶቹ እየቀኑባቸው ታሪካቸውን ያጎድፋሉ። እንዲሁም የምሥራቅ የደቡብና የምዕራብ ግዛቶችን በዘዴና በኃይል ስለጠቀለሉት ጨካኝ እንደነበሩም በማስመሰል ለማቅረብ የሚሞክሩ ብዙ የሚጠሏቸው ሰዎች መኖራቸው ይታወቃል። ይሁንና አፄ ምኒልክ በዘመናቸው የነበረውን ውስብስብ ሁኔታ አልፈው ለአገራቸው ጠቃሚና አኩሪ ሥራ ሠርተው አልፈዋል። ብልህና ዘዴኛ ከመሆናቸውም በላይ ለኢትዮጵያ የሥልጣኔ ጮራ የፈነጠቀው በእሳቸው ዘመን ነው። አፄ ምኒልክ ንጉሥ ብቻ ሳይሆኑ ሃኪም፣ ሜካኒክ፣ የግል ጉዳይ አማካሪ፣ ገበሬ፣ ጠረኛና የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፎቶግራፍ አንሽ እንደነበሩ ከታሪካቸው ለመረዳት ይቻላል።

አፄ ምኒልክ ከህመማቸው በኋላ እያደር መናገርም እያቃታቸው ሄደ። ጀርመናዊ ሃኪሞቻቸው ተስፋ በመቁረጥ ይመስላል፣ ሀክምናውን ችላ እያሉ ፖለቲካ ውስጥ እየገቡ ስላስቸገሩ ተባረሩና ኢትዮጵያዊው ሃኪም ወርቅነህ እሸቴ ማከም ጀመሩ። እሳቸው አክመው ወደ ቤት ሲሄዱ፣ ሃኪሙ ያላዘዙትን፣ በሌሎች ሰዎች ምክር፣ አንዴ ፌጦ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ነጭ ሽንኩርት፣ እያበሏቸውና እያጠጧቸው ታማሚው ምኒልክ እየተጎዱ ሄዱና አለመግባባት ተፈጠረ። በመሃሉ አፄ ምኒልክ እየደከሙ ሄደው ታህሣሥ 3 ቀን 1906 ዓ.ም አረፉ። እረፍታቸው ግን በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ አልኾነም። ይህም የኾነበት ምክንያት ሕዝብ ያመነበትና ተወዳጅ የኾነ የሚተካቸው ንጉሥ በወቅቱ ስላልነበረ መሞታቸው ይፋ ከኾነ አገር ይሸበራል ተብሎ ስለተፈራ በገሃድ የተለቀሰላቸው እንኳን ከሦስት ዓመት በኋላ በ1909 ዓ.ም ነበር። እንዲያውም ሕዝቡ አፄ ምኒልክን ከ1902 ዓ.ም ጀምሮ አይቷቸው አያውቅም ነበርና "አጼ ምኒልክ ከሞቱ በኋላ ለሰባት ዓመት ገዝተዋል" እስከ መባል ተደረሰ።





አፄ ምኒልክ በግላቸው ቀርጸውት የነበረው ፊደል

የውጭ ጠላትን በጦርነት ድል አድርጎ ጥቁር ሕዝቦችን ሁሉ ያኮራውና የድል አድራጊ ምልክት የኾነውን ሎቱ ግራ ጀሮው ላይ ያደረገው የመጨረሻው የኢትዮጵያ ጀግና ንጉሠ ነገሥት በዚህ ሁኔታ ሕይወቱ ተፈጸመ።

መች ባንተ ይሆናል ምኒልክ ንጉሡ
አንተ አስበህ ነበር ልትሰጠው ለያሱ
እንኳን ሊነግሥና ይያዛል ለነፍሱ
በራስ መኮንን ልጅ ትጠፋለች ነፍሱ
ተጌታ ተፈርዷል ዘውዲቱ ሊነግሡ

ሼህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፬

## መናኙ ራስ መኮንን

የሸዋው ንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ ምንም ክርስቲያን ቢሆኑና በአንድ ሚስት መወሰን ቢኖርባቸውም የንጉሥ ኃይለ መለኮት እናት ከሆኑት ከእቴጌ በዛብሽ ሌላ ብዙ ዕቁባቶች እንደነበሯቸው ይታወቃል። በይፋ ሠነድ ላይ የተጠቀሱት ልጆች ስድስት ወንዶችና ዘጠኝ ሴቶች ልጆች ብቻ ቢሆኑም በጠቅላላው ሠላሳ ልጆች ነበሯቸው ይባላል።



ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በዘመናቸው ዘጠኙን ሴቶች ልጆቻቸውን ለየባላባቱ ድረው ነበር። ለምሳሌ አንኮበር ውስጥ የተመለከቷትን ቆንጆ የፈረንጅ ክልስ ሴት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በዕቁባትነት አስቀምጠዋት ነበር። ይህች ሴት የተወለደችው በሞያሌ በኩል በዛባ ከሩሲያዊ የወንጌል መልዕክተኛ ነው። እሷም ይመኙሻል ቡኙኝ በሚል ስም ትታወቅ ነበር። ይመኙሻል ቡኙኝ ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሚስት ያህል ሆና ተናኘ ወርቅንና መርዕድ አዝማች ኃይሌን ወልዳለች።

ሰሜን ሸዋ ውስጥ ዶባ የሚባል ቦታ ላይ ትልቅ እርሻ የነበረውን ወጣት ገበሬ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እርሻውን ዓይተው



በማድነቅ ሴት ልጃቸው ተናኘ ወርቅን ድረውለት ሹመትም ሰጡት። በዚሁ ጋብቻ ሦስት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ ተወልደዋል። ከወንድ ልጆቹም መካከል ራስ መኮንን አንዱ ስለነበሩ ለዳግማዊ ምኒልክ የአክስት ልጅ መሆናቸው ነው።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጃቸውን የዳሩለት ገበሬ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሳለሞት ይባላል። ውልደቱም መንዝ ነው። ሳለሞት በማደጎነትም ለኦሮሞው አቶ ጉዲሳ ተሰጥቶ ነበር። ከአደገ በኋላ የአካባቢው ሰው አባ ጉዲሳ የሚል የፈረስ ስም አወጣለት። ታሪክ መዝጋቢዎችም ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ ብለው ይጠሩት ነበር። የወልደ ሚካኤል አባት ሳለሞት በይፋ የሚታወቅበት ስም ወልደ መለኮት ሲሆን በመንገድና በድልድይ ሥራ ሙያ ታዋቂ ነበር። ጳንሆይ ሕይወቴና የኢትዮጵያ ርምጃ በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ወላጅ አባታቸው ሲገልጹ ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል ወልደ መለኮት ብለው ጠቅሰዋል። ወልደ መለኮት የሳለሞት የክርስትና ስምና በይፋ የሚታወቅበት ስም ነው። ችግሩ ታሪኩ በጊዜው በሥርዓት ስላልተገለጸ ምናልባትም የጉዲሳ ክርስትና ስም ሊሆን ይችላል። የአያታቸውን ውልደት ከየትኛው ጎሣ እንደ ነበረ ባለመግለጻቸው አንዱ ኦሮሞ ናቸው፣ ሌላው ትግሬ ናቸው፣ ሲል የተቀረው ደግሞ አማራ ናቸው በማለት የተዘበራረቀ ገለጻ ቀርቦበታል። ጳንሆይም ይህንን ሁኔታ በሥልጣን ዘመናቸው አንዴ ትግሬ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ኦሮሞ ነኝ እያሉ እንዳመቻቸው ተጠቅመውበታል።

ስለ ራስ መኮንን አያት ውልደት ኦሮሞ ናቸው የሚሉት ጉዲሳ የሚለውን ስም መሠረት በማድረግ ነው። ጳንሆይም ኦሮሞ ነኝ ለማለት የሚሔና ቱለማ ንቅናቄ መሪዎች ተከሰው ችሎት ላይ ሲቀርቡ ራሳቸው "ለጋልነቱ ከእኔ እናንተ በልጣችሁ ነው?" ብለው ጠየቁ ተብሎ በወቅቱ በስፊው ተወርቷል።

ወልደ መለኮት የሚለውን ስም ደግሞ ከትግሬ የመጣ የማደጎ ልጅ አድርገው በማቅረብ ከዚህ ጋር በማያያዝ የተንቤን ተወላጅ ነው የሚሉም ተገኝተዋል። እንዲያውም ሲያትቱ "የማን ክርስቶስ ሰው ገድለው ይሸሹና መንዝ ውስጥ ሲኖሩ የወለዱትን ልጅ በማደጎ ጉዲሳ ለሚባል የኦሮሞ ባላባት ሰጥተው ነበር። ልጁ አድጎ ቀልጣፋና ጀግና ስለሆነ ጉዲሳን ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ "ይህ ልጅ ጎበዝ ነው ይጠቅምዎታል! ብለው ይሰጧቸዋል። ልጁም በቤተ መንግሥት

ሲያገለግል የታወቀ ሰው ስለሆነ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ልጅ አግብቶ ራስ መኮንንን ይወልዳል። በዚህም ሳቢያ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተንቤን ትግራይ ውስጥ የሚገኘውን የዘር ርስታቸውን ፊታውራሪ አበበ ገብረ መድህንን ወክለው ተከራክረው ከረቱ በኋላ ተረክበዋል ይላሉ። ሆኖም ፊታውራሪ አበበ ገብረ መድህን "ይወክሉኝና የዘር ርስትዎን ላስመልስ" ብለው ስላመለከቱና ጃንሆይም "በል እስቲ ሞክር" ብለው ስለፈቀዱላቸው እንጂ በእርግጥ ውልደታቸው የተረጋገጠ ሆኖ አይደለም የሚሉም ብዙ ናቸው። ፊታውራሪ አበበ ገብረ መድህንንም ብዙ ሰው በዚህ ጉዳይ አምቷቸዋል። ከዚህም ጋር ለማያያዝ ጃንሆይ ትግራይ ሄደው ንግግር ሲያደርጉ "ትግሬ የተወለድንበትም የወለድንበትም ነው" ሲሉ ተናገሩ።

በሌላ በኩል ጃንሆይ የሞጃ ተወላጅ ናቸው በማለት መኳንንቶችና የጊዜው ሰዎች ቢወለዱም ባይወለዱም ሞጃ ነን በማለት እንደ ልዩ ፍጡር ራሳቸውን በመቁጠር አንድ ቡድን ፈጥረው ነበር። ድሃውን የሞጃ ተወላጅ እንኳን ሳያስጠጉ ራሳቸውን ብቻ በመካብ ያገኙትን ሁሉ "የድሃ ልጅ! ማን እንደሆንኩ ታውቃለህ?" እያሉ ሲመጻደቁና ሲንፈላሰሱ ምንም ሳይሠሩ ተበታተኑ። ቡድኑ ያተረፈው ነገር ቢኖር የአማራን ጎሣ በሌሎች ጎሣዎች እንዲጠላ ማድረግ ብቻ እንጂ የሠራው ፋይዳ ያለው ነገር አልነበረም። እንዲያውም ሞጃዎች ራሳቸውን ብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ አድርገው ስለተመለከቱ በጃንሆይ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 22 ሚሊዮን ደረሰ ሲባል አንዱ ከመካከላቸው "እኛ 500 እንኳን አንሞላም" እስከማለት ደርሳ ነበር። በተለይ የአማራ ጎሣ ነን የሚሉት ሞጃዎች አማራው ወዳጅና ጠላቱን እንዳይለይ፣ ራሱን እንዳይጠብቅና እንዳይዘጋጅ ከልለው ሜዳ ላይ ጥለውት ራሳቸውም ተበታትነዋል።

ራስ መኮንን በሕይወት ዘመናቸው ልዑል አልተባሉም። ሆኖም ጃንሆይ ስለ አባታቸው በሚናገሩበት ጊዜ ሁሉ "ልዑል አባቴ" እያሉ ስለሚናገሩ እሳቸውን በመፍራትና ደስ ለማሰኘት ሲሉ ብዙ ሰዎች ልዑል ራስ መኮንን እያሉ ይገልጹ ጀመር። ቢሆንም ራስ መኮንን በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከፍተኛው ባለሟል እንደነበሩ የታወቀ ነው።

ዳግማዊ ምኒልክ አራት ዓመት ከሚበልጡዋቸውና ሲጋቡም ፊት የነበሩና የ43 ዓመት ዕድሜ ከነበራቸው ባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ብጡል ኃይለ



ማርያም ልጅ አልወለዱም። ቀደም ብለው የወለዱዋቸው ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው ሞተውባቸው አልጋቸውን የሚወርስ ወንድ ልጅ አልነበራቸውም። ሆኖም ከሴት ልጃቸው ከወ/ሮ ሸዋ አረጋና ከወሎው ራስ ሚካኤል የተወለደ የልጅ ልጅ አቤቶ ኢያሱ ነበረ። ሌላ በሕይወት ያለች ሴት ልጅ ወ/ሮ ዘውዲቱ ብቻ ስለነበረች ሕዝቡ 'ዳግማዊ ምኒልክ አልጋውን የሚያወርሱት ለራስ መኮንን ነው' እያለ ያወራ ነበር።

እቴጌ ጣይቱ ደግሞ ከሳቸውም ባይሆን ከዘመዶቻቸው ንግሥና እንዳይወጣ ብዙ ጥረት አድርገዋል። የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛዋ ሴት ልጅ የዘውዲቱ ባል የጣይቱ ወንድም የደጃች ወሌ ብጡል ልጅ ራስ ጉግሳ ወሌ እንዲሆኑም አድርገዋል። እንዲሁም የተፈሪ ታላቅ ወንድም የደጃች ይልማ መኮንን ባለቤትም የእቴጌ ጣይቱ እህት ልጅ የነበረችው አሰለፈች ወንዴ ናት። ከልጅ ኢያሱ ቀጥሎ ለዘውዱ ቅርበት ያለውን ታየ ጉልላቴን ጣይቱ ከወንድማቸው የልጅ ልጅ ከአልማዝ መንገሻ ጋር አጋብተዋል። ሌሎቹንም እህቶቻቸውን ለተለያዩ መኳንንቶች፣ ወንዶች ዘመዶቻቸውንም ለወይዛዝርት ድረዋል።

እቴጌ ጣይቱ 'ከመኮንን የሚወለድ አልጋውን ይወርሳል' የሚባል ትንቢት ስለሰሙና ወ/ሮ የሺ እመቤትም ሞተው ራስ መኮንን ብቸኛ መሆናቸውን ስለተገነዘቡ፣ የወንድማቸውን የራስ ወሌን ሴት ልጅ ምንትዋብ ወሌን ሰጥተው እንዲያገቡ አዘዙ። ልጅቷ ዕድሜዋ በጣም ትንሽ ስለነበረ ራስ መኮንን ትደግ እያሉ ከተፈሪ፣ ከእምሩና ማሚት ጋር እየተጫወተች ተላምዳ ስድስት ወር ያህል ከቆየች በኋላ ልጆቹን ሰብስበው ከዘመዶቻቸው እንዲላመዱ በየጊዜው ወደ አዲስ አበባ ያመጡ ነበርና እሷንም ከሌሎቹ ጋር ይዘዋት መጡ። ታዲያ እቴጌ ጣይቱ 'ጸነሰች ወይ?' ብለው ቢጠይቋት 'ምንም ግንኙነት አልነበረም!' ብላ በመመለሷ እቴጌ ይናደዱና ሌሎቹ ልጆች ወደ ሐረር ሲመለሱ ምንትዋብን አስቀሯት።

ይህንን ሁኔታና የራስ መኮንንን ጸዋሚና ጸሎተኛነት በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ ራስ መኮንንን 'መነኩሴው!' ማለት ጀመሩ። በመሃሉ ራስ መኮንን ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ እንደተነሱ ታመሙና ወደ ቁልቢ ተመልሰው መታከም ጀመሩ። ለሁለት ወር ያህል ከታከሙ በኋላ በሽታው ይጠናባቸውና መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም ሲሞቱ ባለሚሎቻቸውና ዘመዶቻቸው አስከሬናቸውን ይዘው ወደ ሐረር ይሄዱና ሐረር ጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ባለቤታቸው ወይዘሮ የሺ እመቤት መቃብር አጠገብ ወዳጅ ዘመድ በተሰበሰበበት ተቀበሩ።

በሥነድ የተገኘው መረጃ እንደዚህ ሆኖ እያለ ሕዝቡ ግን መነኑ እንጅ አልሞቱም እያለ በሰፊው ያወራ ነበር። በዚህ በተጋነነ ወሬ ምክንያት ልጃቸው ደጃዝምች ይልማ ጥርጣሬ ላይ ስለወደቁ መቃብራቸውን አስከፍተው አስከሬናቸውን ለመመልከት ተገደዱ። በዚህን ጊዜ ሬሳውን ከተመለከቱት ሰዎች መካከል ብዙ ሰዎች ደጃች ይልማንም ጨምሮ ኦክሲጅን በማይፈልጉ በአ.ምንት ተሃዋስያን ጀርሞች (Anaerobic Decomposition) ምክንያት በመበከላቸው ተመርዘው ሞቱ። ቢሆንም ወሬው እየተጋነነ ሄዶ አንዳንድ ሰዎች ስለመመነናቸው ምስክርነታቸውን በሚከተለው መልኩ የሰጡም አሉ። ነገሩ አፈታሪክ ቢሆንም በወቅቱ ተፈጥሮ የነበረውን አባባል እኔም እንደ ልጃቸው እንደ ደጃች ይልማ መጠራጠር ጀምሬ መመራመሩን ገፍቼበት ያገኘሁትን ሁሉ እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ።

ራስ መኮንን እንደሞቱ አስመስለው እንደመነኑና የመነኑትም ሐረርጌ ውስጥ በሚገኘው አሰቦት ገዳም አጠገብ አንድ ተራራ ላይ ካለው መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን አካባቢ ካለ ዋሻ ውስጥ ነበረ። እንዲያውም ጃንሆይ ብዙ ጊዜ እዋሻው አጠገብ ከደረሱ በኋላ ሰው ሳያስከትሉ ራሳቸው በእግር አቀበቱን ወጥተው ለሦስትና አራት ሰዓት እየቆዩ ይመለሱ ነበር። የመነኑበትም ምክንያት ራስ መንገሻ ዮሐንስን ከአፄ ምኒልክ ጋር ለማስታረቅ ምለው ተገዝተው እጃቸውን ይዘው ካመጡ በኋላ አፄ ምኒልክ ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ከድቶኝ ስለነበረ አሁን አልለቀውም ብለው ስላሰሩባቸው በዚህ ተጸጽተው ነው ይባላል።

በኋላም ራስ መኮንን ኢየሩሳሌም በመሄድ እዚያ ከሚገኙት የኢትዮጵያ ገዳማት አንዱ ውስጥ መኖር ጀመሩ። በስመ ክርስትና በመጠራትና ማንነታቸውም እንዳይታወቅ ስላደረጉ ተፈሪ በስደት ወደ እሥራኤል አገር በሄዱበት ጊዜ የመነነ ሰው ከቤተሰብ ጋር ስለማይገናኝ እንደበፊቱ አልተገለጹላቸውም።

ዓለማየሁ የሚባል የቤተክህነት አገልጋይ የነበረ የጐጃም ሰው ሚስቱ ሞታ፣ እሱም የቅስና ሥርዓቱን ስላፈረሰ ለጣሊያን ወታደርነት ተቀጥሮ ሊቢያ ውስጥ ሲያገለግል ቆይቶ፣ የሚቀርብለትም ምግብ፣ የሚሠራውም ሥራ ስላላስደሰተው፣ በአንድ ምክንያት ከጣሊያኖች አለቆቹ ጋር ወደ እሥራኤል አገር ከሄደ በኋላ እዚያው ይቀርና የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ገብቶ ይጸልይ ጀመር። ከቀን ብዛት የሰውየውን ምግባርና ጸሎት መነኩሴው ራስ መኮንን ተመልክተው ስለወደዱት አስጠጉት። ከዕለታት



አንድ ቀን ማንነታቸውን ለዚሁ ሰው ይገልጹለትና መልዕክት ይሰጡታል። ከነገሩትም መልዕክት መካከል "ተፈሪ ተመልሶ አገሩ ይገባል" እኔም በ1934 ዓ.ም አገሬ ተመልሼ ጣና በሚገኝ ደሴት ውስጥ እመነናለሁ፣ እርሱም 1934 ዓ.ም ከማለቁ በፊት ከመጣ ያየኛል፣ አለበለዚያ ግን ድምጼን ብቻ ነው የሚሰማው" ብለው በጽሑፍም በቃልም መልዕክት ሰጥተውት ሸኙት። ዓለማየሁም አገሩ ጐጃም ከተመለሰ በኋላ ደብረማርቆስን አለፍ ብሎ ከሚገኘው ጃቢ ዲያቆ ሚካኤል አጠገብ ሲኖር ጃንሆይን በመፍራት መልዕክቱን ባለማድረሱ እያደር ነገሩ ይቆረቁረውና የእህቱን ልጅ ወይዘሮ እየሩሣሌም መኪታን ማማከር ይጀመራል። አህትየዋ መልዕክቱን ካላደረስክ ትቀሰፋለህ ብለው ያደፋፍሩትና ጥቅምት 30 ቀን 1935 ዓ.ም አራት ኪሎ አካባቢ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመኪና ሲዘዋወሩ አቤት ብሎ ስለሮጠ መኪናቸውን አስቁመው "ምንድነው ጉዳይህ" ቢሉት፣ "አይ! ከሁለት የሚያምኗቸው



ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል

ሰዎች ጋር ብቻ ያነጋግሩኝ፣ የኾነ መልዕክት አለኝ" አለ። ከዚያም በቃል የተነገረውንና ከመቀነቱ ጋር ተሰፍቶ የነበረውን በጽሑፍ የተሰጠውን መልዕክት ተርትሮ አወጣና አቀረበ። ጃንሆይም በዚህን ጊዜ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ካለቃቀሱ በኋላ ሰውየውን ለብዙ ጊዜ በአዲስ አበባ አቆይተው ሸልመው ወደ አገሩ ይሸኙታል። ይኸው ዓለማየሁ እንየው የሚባለው የቤተ ክህነት ሰውና የራስ መኮንን መልእክተኛ ከአንድ ዓመት በኋላ አገሩ ጐጃም ሲመለስ አምሮበት ገንዘብ ቋጥሮ ስለነበረ በደህና ሲኖር መጨረሻ ላይ በ1958 ዓ.ም ታሞ ሞተ። ይህንን ሁኔታ በሕይወት ያሉት የወይዘሮ እየሩሣሌም መኪታ ሴት ልጅ ወይዘሮ አያልነሽ ዓለማየሁ ታሪኩን በደንብ ተከታትለውት ስለነበረ አጫውተውኛል።

ራስ መኮንን ከእሥራኤል አገር በ1934 ዓ.ም ተመልሰው ከወዳጃቸው ከወርቁ ወልደ ማርያም ጋር ደብረ ታቦር አጠገብ በጉና ተራራ ሥር

በሚገኘው ሞክሽ ኪዳነ ምሕረት ከደረሱ በኋላ ጣና መካከል ወደሚገኘው ክብራን ገብርኤል ሄዱ። ሆኖም መናንያን በስመክርስትና ስለሚጠሩና ራስ መኮንንም እንዲታወቁ ስላልፈለጉ እሳቸውና ወዳጃቸው ወርቁ ወልደ ማርያም መጨረሻ ላይ የት እንደደረሱ በግልጽ ሊታወቅ አልተቻለም። ጥርጣሬው ግን ምናልባት የቀረውን ሕይወታቸውን ያሳለፉት እዚያው ጣና መካከል በሚገኘው ደቀ እስጢፋኖስ ገዳም ነው ይባላል።

የባሕር ዳር አውራጃ አስተዳዳሪ ደጃች አእምሮ ሥላሴ ደቀ እስጢፋኖስ ሄደው ባላንባራስ ጤናው ባለቤት ራስ መኮንንን አግኝተው እንዳነጋገሯቸው ለጃንሆይ ገልጸው ነበር። ግን በምንም መልኩ በተደረገው ሙከራ ሁሉ ራስ መኮንን ለልጃቸው ሊገለጡ አልፈለጉም። ይህንን ሁኔታ የባላንባራስ ጤናው ሴት ልጅ ባለቤት የሆኑትና በሕይወት ያሉት የባሕር ዳር ነዋሪ አቶ አብርሐም ዋለ ራሳቸው ከባላንባራስ ጤናው መስማታቸውን አረጋግጠውልኛል።

ንጉሠ ነገሥቱ ከ1935 ዓ.ም በኋላ በተለያየ ጊዜ አዘውትረው ወደ ባሕር ዳር ይመላለሱ ነበር። ደጃች አበረ ይማም በ1942 ዓ.ም. ባሕር ዳር ላይ ሸፍተው ስለነበረ ከዚህ ወቅት በኋላ ጃንሆይ ወደባሕር ዳር አዘውትረው መሄዱን ቢያቋርጡም አልፎ አልፎ ብቅ ማለቱን አልተውም። ሆኖም ይህ የንጉሠ ነገሥቱ ምልልስ በጣና ዙሪያ ካሉ ገዳሞች በአንዱ ውስጥ የመነኑትን አባታቸው ራስ መኮንንን ለማግኘት ነው በማለት አንዳንድ ሰዎች ይጠራጠሩ ነበር። ደቀ እስጢፋኖስ ደሴት ላይ አንድ ጊዜ በባላገሮችና በመነኮሳት መካከል ጠብ ተፈጥሮ ጃንሆይ ደሴቱን ጎብኝተው ነገሩን አብርደውና የመነኮሳቱን ይዞታ አጠናክረው ተመልሰዋል። ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ በአንድ ወቅት በዚሁ ደሴት ድንኳን ተክለው ለአሥር ቀን መቀመጣቸው ይህንኑ ጥርጣሬ አጠናክሮታል። በተለይ በደቡብ ጎንደርና በባሕር ዳር አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ራስ መኮንን መንነው እንደነበረ የሚያምኑ መሆናቸውን በጭውውት ለመረዳት ይቻላል።

በአሁኑ ወቅት የራስ መኮንን ወዳጅ ከነበሩት ከወርቁ ወልደ ማርያም ተወላጆች መካከል አቶ መኮንን አየለ የሙሉነሽ ወርቁ ልጅ ከሆኑት አንዱ ከአባታቸው ከአየለ ውቤ ህክምና ተምረው በአሁኑ ጊዜ ደብረ ታቦር በክምር ድንጋይ አካባቢ የታወቁ ሃኪም ናቸው።



ደብረ ታቦር ጉና ተራራ አካባቢ ብዙ መንፈሳዊ የሆኑ ሰዎች ይወጡበታል። ከነዚህም መካከል "የአናሲዋ እመቤት" ከጉና ሚካኤል አካባቢ ተነስተው አርሲ ከሄዱ በኋላ በመላው ኢትዮጵያ ስማቸው የገነነ አዋቂ ኾነው ነበር። የአናሲዋ እመቤት እሜቴ ሹባሽ በአባታቸው የደቡብ ጎንደር ተወላጅ ሲሆኑ በእናታቸው ወሎዬ ናቸው። ብዙ ሰዎች በሹባሽ መጀን! በአናሲዋ እመቤት! እያሉ የአናሲዋ እመቤትን ለመማለድ ከመላው ኢትዮጵያ ወደ አርሲ እሳቸው ዘንድ ይጓዙ ነበር። በዚህም ምክንያት አርሲ ካለው ቤታቸው አጠገብ ያለውም ተራራ ጉና ተባለ። እሳቸውን ብሎ ለሚመጣው ሕዝብ ጉና ሚካኤልንና አንድ መስጊድ እዛው አርሲ አሠርተዋል።


ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል

የኾነ ሆኖ የንጉሠ ነገሥቱ ወደ ጣና ዳርቻ መመላለስ አካባቢውን እንዲወዱ ስላደረጋቸው የባሕር ዳር ከተማ መቆርቆርን አስከተለ። ይህች ከተማ በጥሩ ዕቅድ የተሠራችና ውሃ ዳር ያለች ስለኾነች ለኢትዮጵያ ዋና ከተማነት ታጭታ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ቦታ ለመያዝ ይረባረቡ ነበር። በኋላ ግን ጣና ባሕር ውስጥ ቢልሃርዝያ ስለተገኘበትና በዘመኑ መድሃኒትም ስላልነበረው ሁለተኛ ደግሞ ጃንሆይ "ንጉሥ በነገሠ ቁጥር ዋና ከተማ መለወጡ ጥሩ አይሆንም" እሉና ሃሳቡ ተሰረዘ።

ቀኝጌታ ሽፈራው በርሄ የሚባሉ በልዕልት ተናኘ ወርቅ ቤተርስት ይሠሩ ከነበሩ የአዲስ አበባ ነዋሪ ጋር ስንወያይ "ራስ መኮንን መመነናቸውን ከእማማ ዘርጊ ሰማሁ" በማለት እርግጠኝነቱን የተቀበሉት መሆኑን ነግረውኛል። ቀጥለውም "እማማ ዘርጊ ራስ መኮንን ሞቱ የተባለ ዕለት ቁልቢ እንደነበሩና መለቀስ የተጀመረው እኩለ ሌሊት ላይ መሆኑን፣ ከዚያ በፊት ራስ መኮንን አለመታመማቸውን እንደሚያውቁም አጫውተውኛል። እማማ ዘርጊ አሁን በሕይወት የሉም ግን በወቅቱ ገና ኮረዳ የነበሩና ወጣ ገባ የሚሉ የራስ መኮንን የቤት ሠራተኛ ነበሩ" ብለዋል።

ከላይ የተጠቀሰውን የራስ መኮንንን መመነን ሕዝቡ በከፊል ሲቀበለው አንዳንድ ሰዎች ግን አያቶቻችን "ቆመን አስቀብረናል" ብለውናል ይላሉ። እንዲያውም ራስ መኮንን ሊሞቱ ሲሉ ለራስ እምሩ አባት ለፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ "ልጄን ተፈሪን አደራ ሰጥቼሃለሁ" ብለዋቸው እንደነበረ ጭምር ይነገራል። በሌላ በኩል ደግሞ የቀበረ ሁሉ አስከሬኑን አየ ለማለት ያስቸግራል። ጥቂቶች ደግሞ "አይ የቅዱስ ልጅ መስሎ ለመታየት በተፈሪ የተነዛ ወሬ ነው" ብለው ያጣጥሉታል። እንዲያውም ራሳቸው ጃንሆይ ሰዎች ይኽን ነገር ብዙ ጊዜ ሲያነሱባቸው ፈገግ ብለው ነገሩን ችላ ብለው ያልፉታል ይባላል።





# ምዕራፍ ፳

## መካኗ እቴጌ ጣይቱ ብጡል

እቴጌ ጣይቱ ብጡል ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም ደቡብ ጎንደር በደብረ ታቦር ከተማ ተወለዱ። እናታቸው ወ/ሮ የውብዳር አባታቸው የሰሜኑ ባላባት ደጃች ብጡል ኃይለ ማርያም ናቸው። ጣይቱ ውልደታቸው ከሸዋም፣ ከየጁም፣ ከጎንደርም መሳፍንቶች ሲሆን እንዲያውም ከአፄ ሱስንዮስ ሴት ልጅም ከሐመልማላዊት ዝርያ አላቸው።

ጣይቱ በልጅነታቸው እቤት አስተማሪ ተቀጠሮላቸውና በየአድባራቱም የሃይማኖት ትምሕርት በደንብ ተምረዋል። የግዕዝ ቋንቋ አጥርተው ያውቃሉ፣ በገናም ይደረድራሉ።

አፄ ምኒልክ የሚያፈቅሯቸው የመርሃቤቴዋ ተወላጅ ሚስታቸው ወይዘሮ ባፈና ከጠላቶቻቸው ጋር በባላቸው ላይ እየዶለቱባቸው ስላስቸገሯቸው ተፋቱ። ወዲያው ሚስት ፈልጉልኝ ብለው አዘው ከወላይታ ቆንጆ ተመርጣላቸው ስትመጣ፣ በድንገት ጣይቱ ብጡል መምጣታቸውን እንደሰሙ፣ አዲሷን ሚስት ይዘው ለመጡት የኮምቦልቻ የልጅ ልጅ ለሆኑት ለፊታውራሪ ዲቢሶ ጋሻ፣ አንተው አግባት ብለው መረቋቸው።

አፄ ምኒልክ በልጅነታቸው ጎንደር ስለነበሩ እንዲሁም ሸዋም ከተመለሱና ከነገሡ በኋላ የጣይቱ ብጡል ሁለት ወንድሞች ልጅ አሉላ ብጡልና ባላንባራስ ወሌ ብጡል አድረውላቸው ነበረና ስለጣይቱ አስቀድመው ብዙ ያውቁ ነበር። ስለኾነም በወቅቱ የጣይቱ

እሺ. ብላ ወደ ደብረ ብርሃን መምጣት ለአፄ ምኒልክ ትልቅ አስደሳች ዜና ነበር።

ጣይቱ ብጡል ከአፄ ምኒልክ ጋር በ1875 ዓ.ም በተክሊል ሲጋቡ ፊትና የ43 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ነበሩ። ጣይቱ አፄ ዮሐንስ መልክ ቀናም ስለሆኑና እሳቸውም ሥልጣን የሚመኙ ስለነበሩ ሊያገቧቸው ፈልገው ሁለተኛ ሚስት ለማግባት ስላልፈለጉ ምኞታቸው አልሰመረላቸውም። አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በሦስተኛው ቀን ወ/ሮ ጣይቱም "እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ" ተብለው ዘውድ ጫኑ።



እቴጌ ጣይቱ ብጡል ኃይለ ማርያም

ልክ እንደ ቋረኛዋ የአፄ በካፋ ባለቤት እንደ እቴጌ ምንትዋብ ሁሉ እቴጌ ጣይቱም ኃይለኛና ሥልጣን ወዳድ ነበሩ። እቴጌ ምንትዋብ ባለቤታቸው አፄ በካፋ በወጣትነታቸው ስለሞተና ልጃቸው ኢያሱ ሲነግሥ ልጅ ስለነበረ፣ እቴጌ ምንትዋብ ሞግዚት በመሆን ባለሥልጣን



ኸነው አገሩን ከማስተዳደራቸውም ኢያሱም በወጣትነቱ ሞቶ የልጅ ልጃቸው ኢዮአስ ሲነግሥም ማስተዳደሩን ቀጥለው ለሠላሳ ዓመት ከገዙ በኋላ መጨረሻ ላይ ተገደው ለቀቁ።

እቴጌ ጣይቱም ብልህ፣ የተማሩ፣ የተከበሩና ጀግና ስለነበሩ ከባልሁ አፄ ምኒልክ ጋር ተጣጥመው ብዙ ነገር አብረው ሠርተዋል፣ ጠላትንም አድዋ ላይ አብረው ተሰልፈው ድል አድርገዋል። በተለይ ጣሊያኖች ከአፄ ምኒልክ ይበልጥ እቴጌ ጣይቱን እንደሚጠሉ ይታውቅባቸው ነበር።

በአፄ ምኒልክ መታመም ምክንያት የመንግሥቱን አስተዳደር ማካሄድ በጀመሩ ጊዜ መኳንንቶቹ የእሳቸውን ሥልጣን መያዝ በመቃወም ሲሸረቸው ለሜራው መሪ በመሆን ውስጥ ውስጡን ሲጎተጉቱ የነበሩት የልጅ ኢያሱ ሞግዚት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ነበሩ። እንደዚሁም ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስና ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ግንባር ቀደም በመሆን ከሌሎች መኳንንቶች ጋር በተለይም በራስ ደምስ ይመራ የነበረውን የመሃል ሠፋሪ ጦር ኃይል ለሜራው አጋር በማድረግ ተሳትፈዋል[7]።



ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር

ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር የአድዋ ባላበት በነበሩ ጊዜ የሸዋ መንግሥት ፈርሷል ብለው ሌሎች የትግራይን ባላባቶችን ሲያስተባብሩ ራስ ስብሐት ሳይስማሙ ቀሩ። በዚህ ምክንያት አጋሜ ውስጥ አኮራ የሚባለው ቦታ ላይ በየካቲት ወር 1906 ዓ.ም. ጦርነት ተደርጎ ደጃች ስብሐት በደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ተንኮል ተገደሉ። ሰዎች ደጃች ገብረ ሥላሴን ያለ መብታቸው ባድመን ለመሸጥ ተስማምተው ከኤርትራ ሦስት ሺህ ጠብመንጃ አስመጡ ብለው አወሩባቸው።

[7] ጣይቱ ብጡል በቀኛዝማች ታደሰ ዘውዴ ገጽ 66

ይሁንና የበጌምድርና ስሜን አገረ ገዥ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ በትግራይ ወስጥ የተፈጠረውን አለመግባባትና ንጉሡ ሳያዙ በተደረገው ጦርነት አጥፊውን ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ ታዘው ሲሄዱ፣ ደጃች ገብረ ሥላሴ ሸሽተው ከነሠራዊታቸው ኤርትራ ውስጥ ገቡ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስ የኤርትራ ወሰን ላይ ከነሠራዊታቸው ሰፍረው ሲጠባበቁ በወቅቱ የጣሊያን ጦር ወደ ሊቢያ ተልኮ ነበረና የኤርትራ አስተዳዳሪ ጉዳዩ ስላስፈራው የራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጦር የሠፈረበትን ወንዝ በራስጌው መርዝ ስላደረገበት ወታደሩ ውሃውን እየጠጣ ስለታመመ ጦሩ ሊፈታ ቻለ።



ልዕልት ወለተ እሥራኤል ሥዩም

ደጃች ስብሐት የአጋሜ ገዥ ስለነበሩ በሳቸው መገደል የአድዋና የአጋሜ ሰዎች ቂም ተያይዘው እስከ አሁን አይጣጣሙም። ከአራት ዓመት በኋላ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ይቅርታ ተደርጎላቸው ወደ ሸዋ ከተመለሱ በኋላ ይህንን መቃቃር ለማጥፋት የራስ ሥዩም ልጅ የሆኑትን ልዕልት ወለተ እሥራኤልን እንዲያገቡ ተደርጎ ሸዋ ውስጥ ሜጫ ሲኖሩ ደጃዝማች ዶክተር ዘውዴ ገብረ ሥላሴን ወለዱ።

ከባለቤታቸው ዕረፍት በኋላ ልዕልት ወለተ እሥራኤል ወጣት ስለነበሩ የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን የመጀመሪያ ሚስት ኾነው ልዕልት እጅጋየሁ አስፋ ወሰንን ወለዱ። በጠላት ወረራ ጊዜ በስደት እሥራኤል አገር ሄደው በነበረበት ወቅት ባለቤታቸው ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን እሳቸውን ትተው ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅን ሲያገቡ በድርጊቱ ተናደው ልጃቸው ዘውዴን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ለጠላት እጅ ሰጡ። ልዕልት ወለተ እሥራኤል ሰዓሊ ስለ ነበሩ ለየቤተ ክርስቲያኑ የጻድቃንን ምስል እየሠሩ ያበረክቱ እንደ ነበረ ይታወቃል። በእርጅና ምክንያት በ1982 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።



ራስ ወሌ ብጡል እህታቸውን እቴጌ ጣይቱን በሥልጣን ለማቆናጠጥ እርምጃ መውሰድ ሲችሉ "ከምኒልክ ጋር የገነባሁትን አገር መልሼ አላፈራርስም" ብለው ሳይዋጉ ቀሩ።

እቴጌ በሥልጣን ለመቆየት ያደረጉት ጥረት በባለሥልጣኖች ተንኮል ተሰናከለ። ይሁንና እቴጌ ጣይቱን መኳንንቶቹ ከሥልጣን ካስወገዱዋቸው በኋላ አፄ ምኒልክን ሲያስታምሙ ቆይተው አፄ ምኒልክ ሲሞቱ ልጅ ኢያሱ ከቤተ መንግሥት አስወጥቶ እንጦጦ ላይ በግዞት አስቀምጧቸው ሲኖሩ፣ በመሃሉ በኩላሊት በሽታ እግራቸው አብጦ የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም ሞተው እንጦጦ ማርያም ተቀበሩ። በኋላ ግን አስከሬናቸው ወደ ባዕታ ማርያም ተዛውሮ ከባለቤታቸው ከአፄ ምኒልክ አስከሬን አጠገብ አርፏል።

እቴጌ ጣይቱ አድዋ ላይ ዘምተው በመልስ ላይ የጣሊያን ምርኮኞችን እንዳይርባቸው ጧት ጧት 30 ከረጢት ዳቦ እየተቆረሰ ለምርኮኞቹ ጣሊያኖች ሁሉ ያድሉ ስለነበረ እቴጌ ብቅ ሲሉ ጣሊያኖቹ "ኤኮ! ኤኮ! ሲኞሪና አል ዳቦ" እያሉ ወደ እሳቸው ይሮጡ ነበር። እንዲያውም ከአጀባቸው ከግማሽ በላይ የጣሊያን ምርኮኛ ወታደሮች ኾነው ነበር።

እቴጌ ጣይቱ ከአድዋ ጦርነት ታሪካቸው ሌላ ከሚታወሱባቸው ነገሮች ዘመናዊ ሆቴል መክፈት፣ የነጭ ጤፍ ዘር ከጎንደር አስመጥተው ሸዋ እንዲያበቅል አድርገው በቤተ መንግሥት ነጭ ጤፍ እንጀራ እንዲበላ ማድረጋቸው አንዳንዶቹ ሲሆኑ በተጨማሪም አዲስ አበባ ከተማንና ጽጌ ረዳ አበባን ስም ያወጡላቸው እሳቸው መሆናቸው ይታወቃል።